# አዲሱ የንግድ ህግ የያዛቸው መሰረታዊ ጉዳዮች

የንግድ ተላላኪዎች እና እንደራሴዎች በንግድ ስራ ያላቸው ሚና

አንድ ነጋዴ የተሰማራበትን የንግድ ስራ በውጤታማነት፣ በቅልጥፍናና በጥራት ለመስራት እንዲሁም የሚያመርተውን ምርት ወይም የሚሰጠዉን አገልግሎት ለሸማች/ለተጠቃሚዉ በአግባቡ ለማደረስ እንዲያስችለዉ የተለያየ ዘዴዎችን ይጠቀማል። በዚህ መሰረት የንግድ ሰራተኞችን በስራ ውል ቀጥሮ ማሰራት፣ የንግድ ወኪሎችን በየቦታዉ ማስቀመጥ እንዲሁም ከንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ጋር የሚሰራ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ በአዲሱ ንግድ ህጋችን እዉቅና ስላላቸዉ የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ምንነትና ስራዎቻቸው ተዳሰዋል።

1. የንግድ ተላላኪዎች፣ የንግድ እንደራሴዎች እና ያላቸው ሚና

1.1. የንግድ ተላላኪዎች

ከላይ እንደተጠቀሰው ነገዴዎች የተለያዩ ሰዎችን በመጠቀም ከሸማቹ ወይም ከአገልግሎት ፈላጊዉ ጋር ከሚገናኙባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ የንግድ ተላላኪዎችን በመጠቀም ነዉ። በንግድ ህጉ አንቀጽ 36(1) መሰረት የንግድ ተላላኪ ማለት መኖሪያው የንግድ መደብር ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት የሆነና ከነጋዴዉ ጋር በተዋዋሉት የሥራ ውል መሠረት ከነጋዴዉ ጋር የሚሠራ፤ ነጋዴዉ እያዘዘው የነጋዴዉ ደንበኞች በሚገኙበት ቦታ እየተዘዋወረ በነጋዴዉ ስምና ምትክ ሆኖ ዕቃ የሚያቀርብ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው። በህጉ አንቀጽ 36(2) መሰረት የንግድ ተላላኪዎች በነጋዴዉ ስምና ምትክ ሆነው ዕቃ ሲያቀርቡ ወይም አገልግሎት ሲሰጡ በመካከላቸዉ ሌላ የዉል ቃል ከሌለ በስተቀር የንግድ ተላላኪዎች የተዋዋሏቸዉ ውሎች ለነጋዴዉ ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል።

1.2. የንግድ እንድራሴዎች

በንግድ ህጉ አንቀጽ 37 ስር የንግድ እንድራሴዎች መኖሪያቸው የወካዩ ነጋዴ የንግድ ማህበር ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት ሥፍራ ያልሆነና ከነጋዴዉ ጋራ በተዋዋሉት የሥራ ውል መሠረት ነጋዴዉ እንዲሠሩ እያዘዛቸው በተወሰኑ ቦታዎች የነጋዴውን ምርቶች እና አገልግሎቶች የሚያስተዋውቁ፣ የገበያ ጥናትና ለነጋዴዉ ሥራ መስፋፋት የሚረዱ ተመሳሳይ ሥራዎች የሚሰሩ ሰዎች እንደሆኑ ትርጉም ተሰጥቷቸዋል።

የንግድ እንድራሴዎች ከንግድ ተላላኪዎች የሚለዩት የንግድ ተላላኪዎች መኖሪያቸው የንግድ መደብር ዋና መሥሪያ ቤት ባለበት በማድረግ በተዋዋሉት የሥራ ዉል መሠረት ከነጋዴዉ ጋር የሚሠሩ፤ ነጋዴዉ እያዘዛቸው የነጋዴዉ ደንበኞች በሚገኙበት ቦታ እየተዘዋወሩ በነጋዴዉ ስምና ምትክ ሆነው ዕቃ የሚያቀርቡ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ሲሆኑ የንግድ እንድራሴዎች ደግሞ የወካዩ ነጋዴ የንግድ ማህበር ዋና

መሥሪያ ቤት በሌለበት ቦታ ነጋዴዉ በሚያዛቸዉ መሰረት በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የነጋዴዉን ምርቶች እና አገልግሎቶች የሚያስተዋውቁ፣ የገበያ ጥናትና ለነጋዴዉ ሥራ መስፋፋት የሚረዱ ተመሳሳይ ሥራዎች የሚሰሩ ሰዎች ናቸዉ።

1.3. የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ነጋዴ ስላለመሆናቸው

በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 5 ሥር የተዘረዘሩትንና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች በቋሚነት ለትርፍ የሚሠሩ ሰዎች እንደ ነጋዴ እንደሚቆጠሩ በግልጽ ተቀምጧል። የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎችን በሚመለከት ህጉ በግልጽ በአንቀጽ 36(3) እና 37(2) ላይ ነጋዴዎች እንዳልሆኑ አስቀምጧል። በመሆኑም የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ነጋዴ ሳይሆኑ በስራ ዉል ስምምነት በደመወዝ ወይም በኮሚሽን ወይም ሁለቱንም በማጣመር በሚደረግ ክፍያ በነጋዴዉ በሚታዘዙት መሰረት የሚሰሩ ሰዎች ናቸዉ።

2. በንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ላይ የተጣሉ ክልከላዎች

2.1. የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች የግል ንግድ እንዳይፈጽሙ ስለመከልከላቸዉ

የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ለመከላከል በማሰብ ህጉ በአንቀጽ 38 ላይ ነጋዴዉና የንግድ ተላላኪዎች ወይም እንድራሴዎች በስራ ውላቸዉ ዉስጥ በግልጽ ካልተስማሙ በስተቀር የንግድ ተላላኪዎችና የንግድ እንድራሴዎች ስለ ራሳቸውም ሆነ ስለ ሌላ ሦስተኛ ወገን ሆነው እነሱን የቀጠራቸው ነጋዴ ከሚሠራው የንግድ ሥራ ጋራ ተመሳሳይ የሆነ የግል ንግድ እንዳይነግዱ ከልክሏል። ይህንን ክልከላ በመተላለፍ የግል ንግድ ሲነግዱ በተገኙ ጊዜ የሚከተሉት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ በአንቀጽ 38(1) እና (2) ተቀምጧል።

- የሚከፈላቸዉን ደመወዝ ወይም ኮሚሽን ወይም ሁለቱንም የመከፈል መብታቸዉን ያጣሉ።
- ዉል እንዳይቀጥል በተሰረዘ ጊዜ ሊያገኙ የሚችሉ ካሳ የመከፈል መብታቸዉን ያጣሉ።
- ቀጣሪዉ አካል/ነጋዴዉ ኪሳራ መጠየቅ ይችላል፣ የስራዉንም ዉል ለመሰረዝ ወይም ዉሉን አላድስም ለማለትም በቂ ምክንያት ይሆናል።

2.2. ለሌሎች ነጋዴዎች ተተክቶ አለመስራት

ተቃራኒ የዉል ስምምነት ከሌለ በስተቀር የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች በውል ግዴታ ለገቡለት ነጋዴ ብቻ እንጂ ስለሌሎች ነጋዴዎች ተተክተው መሥራት የማይችሉ ሲሆን ለሌሎች ነጋዴዎች ተተክተው ሲሠሩ በተገኙ ጊዜ የሚከፈላቸዉን ደመወዝ ወይም ኮሚሽን ወይም ሁለቱንም እንዲሁም ካሳ የመከፈል መብታቸዉን እንደሚያጡ የህጉ አንቀጽ 39 ይደነግጋል።

በውላቸዉ ላይ ለሌሎች ነጋዴዎች ተተክቶ መሥራት እንደሚቻል ከተስማሙ ስለሌሎች ነጋዴዎች ተተክተው መሥራት የሚችሉ መሆኑን ህጉ የፈቀደ ቢሆንም ነገር ግን በምንም አኳኋን ቢሆን ግዴታ የገቡለት ነጋዴ ከሚሸጠው ዕቃ ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዕቃ ለመሸጥ ወይም አገልግሎት ለመስጠት ለሌላ ነጋዴ ተተክቶ ለመሥራት እንደማይፈቀድ በአንቀጽ 39(2) ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡

3. የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ስላለባቸዉ ሃላፊነትና ተጠያቂነት

በኢትዮጵያ የፍትሃብሄር ሕግ አንቀጽ 2179 ውክልና ወይም እንደራሴነት አንድም ከሕግ በሌላ መልኩ ደግሞ ከውል ሊመነጭ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የንግድ ተላላኪዎችና እንድራሴዎች ከነጋዴዉ ጋር በሚገቡት የስራ ዉል መሰረት በነጋዴዉ የሚታዘዙትን ስራዎች ለመስራት የሚስማሙ በመሆኑ ከውል የሚመነጭ የውክልና ወይም የእንደራሴነት ባህሪያት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም ከነጋዴዉ ጋርና ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ያላቸዉን ግኙነት በተመለከተ ስለ ውክልና/እንድራሴነት የተመለከቱት የፍትሃብሄር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለአብነት የፍትሐብሐር ህጉ በአንቀጽ 2189(1) ስር እንደራሴዉ ከወኪልነቱ ስልጣን ሳያልፍ በሌላ ሰዉ ስም የመዋዋል ተግባሮችን የፈጸመ እንደሆነ በእርሱ የተፈጸሙት ተግባሮች በቀጥታ በሾመዉ ሰዉ እንደተፈጸመ ይቆጠራል የሚል በመሆኑ አሁን በያዝነዉ ጉዳይ ላይ የንግድ ተላላኪዉ ወይም እንድራሴዉ በነጋዴዉ ስም የሚሰሩ እንደመሆናቸዉ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት ወይም በታዘዙት መሰረት የሚፈጽሙት ዉል በነጋዴዉ እንደተፈጸመ የሚቆጠር ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ግን ከተሰጣቸዉ ስልጣን ወሰን ዉጪ በማለፍ የሰሩት ስራ ካለ ነጋዴዉ የተፈጸመዉን ተግባር ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ እንደሚችል የፍትሐብሐር ህጉ አንቀጽ 2190(1) ይደንጋገል፡፡

የፍትሐብሐር ህጉ አንቀጽ 2208(1) እንዳስቀመጠው ተወካዩ ከወካዩ ጋር በሚያስተሳስረው ግንኙነት ውስጥ ጥብቅ የሆነ ቅን ልቦና ሊኖረው እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ የንግድ ተላላኪዉ ወይም እንድራሴዉ ከነጋዴ ትዕዛዝ በመዉሰድ በሚሠራቸው በማንኛውም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለለጋዴዉ የተሻለ ጥቅም ሲል በቅንነት ሊሠራ ይገባዋል፡፡ የሚሠሯቸው ድርጊቶች ሁሉ ነጋዴውን ተጠያቂ የሚያደርጉ ስለሆነ በማን አለብኝነት ስሜት ሥራውን መሥራት የለባቸዉም፡፡ የንግድ ተላላኪዉ ወይም እንድራሴዉ የራሱን ጉዳይ ሲሰራ ሊወስደው የሚችለውን ጥንቃቄና ጭንቀት ለነጋዴዉ በሚሠራበት ጊዜ ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፍትሐብሐር ህጉ አንቀጽ 2209(1) እና 2211(1) እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የንግድ ተላላኪዉ

ወይም እንድራሴዉ ለሚሰራዉ ስራ ታማኝነት/ታማኝ የመሆን ግዴታ/ ታታሪነት /ትጉህ የመሆን ግዴታ ይኖርበታል።

The role of business ambassadors and individuals in business

A merchant uses different methods to ensure that his business is established efficiently, intelligently and to deliver the product or service he produces to the consumers/users. In this article, employing business employees on contract, placing business agents everywhere, and working with business agents and myself. About the business agents who are aware of our new trade law. The identity of the people and their w...

## 2. የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ጥበቃ በአዲሱ የንግድ ሕግ

በንግድ ማኅበራት አስተዳደር ውስጥ ከሚጠቀሱት ጉዳዮች አንዱ የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብት ጥበቃ ነዉ። ሕግ በተለይም የንግድ ሕግ የባለአክሲዮኖችን መብትና ግዴታ ማስፈፀሚያ መሳሪያ እንደሆነ ሁሉ የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብትንም የሚጠብቅ መሆን አለበት። ሀገራት ለአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብት ማስጠበቂያ ደንቦችን በንግድ ሕጎቻቸዉ ያካትታሉ። በሀገራችን አዲሱ የንግድ ሕግ ከተካተቱ አዳዲስ ጉዳዮች አንዱ የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ጥበቃ ነው። በዚህ ጽሑፍ የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች ምንነት እና በንግድ ማህበራት እንቅስቃሴ ውስጥ ለእነዚህ ባለአክሲዮች የሚጠበቁ መብቶች ተዳሰዋል።

## 1. የአነስተኛ ባለአክስዮኖች ምንነት

በንግድ ማኅበራት አስተዳደር ዉስጥ አነስተኛ ባለአክሲዮኖች የሚለዉ ሐረግ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም የለዉም። አንድ ባለአክሲዮን ብቻዉን አነስተኛ ባለአክሲዮን ሊሆን ይችላል። ብቻዉን የንግድ ማኅበር ከግማሽ በላይ አክሲዮኖች የያዘ አንድ ባለ አክሲዮን ደግሞ ከፍተኛ (አብላጫ) ባለአክሰዮን ይሆናል። በተቃራኒዉ ደግሞ ከግማሽ በታች ያላቸዉ ብዙኃን ባለአክሲዮኖች በድምፅ ከተበለጡ አነስተኛ ባለአክሲዮኖች ሊሆኑ ይችላሉ።

የሀገራችን የንግድ ህግ ሲታይ በተለያዩ ክፍሎች ዉስጥ አነስተኛ ባለ አክሲዮኖች የሚለዉን ሀሳብ እንደ አዉዱ በተለያየ መንገድ ይፈታዋል። በአብዛኛዎቹ ክፍሎች ዉስጥ ከጠቅላላ ካፒታል አሥር በመቶ (10%) ያላቸዉን እንደ አነስተኛ ባለአክሲዮኖች ሲወስድ በአንዳንድ ክፍሎች ቢያንስ ሃያ በመቶ (20%) ያላቸዉን እንደ አነስተኛ ባለአክሲዮን በመዉሰድ ለሙብት ማስጠበቂያ ድንጋጌዎች መፈጸም እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል። በሌሎች ድንጋጌዎች የአክስዮን መጠን ሳይጠይቅ ማንኛዉም ባለአክስዮን እንደ አነስተኛ ባለአክሲዮን የሚበቅባቸዉ ሁኔታዎች አሉ። በአጠቃላይ ሲታይ አነስተኛ ባለአክሲዮን ማለት በማኅበሩ ያላቸዉ የአክሲዮን ድርሻ ከግምሽ በታች የሆነ ወይም ዝቅተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ማለት ነዉ።

2. አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች የሚደረግ የሕግ ጥበቃ እና የጥበቃው መነሻ

እንደ ሀገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሰዎች ለኢንቨስትመንት የሚሆን ተቀማጭ ገንዘብ ስለማይኖራቸው ዜጎች ያላቸውን ውስን ሀብት አስተባብሮ ወደ ሥራ ማስገባት ያስፈልጋቸዋል። ይህ እንዲሳካ ደግሞ ዜጎች የቆጠቡትን ትንሽ ገንዘብ በንግድ ማኅበር ውስጥ ካስገቡ በኋላ ለምዝበራ እንዳይዳረጉ የሚከላከል ስርዓት መኖር አለበት።

የቀድሞዉ የንግድ ሕጋችን በማኅበራት ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ይዘው የሚገቡትን ባለሀብቶች ከዘረፋ፣ ካልተገባ ጫና ወይም በደል ለመታደግ ያለሙ ድንጋጌዎች በበቂ ሁኔታ አላካተተም። አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 364 ይህን ሁኔታ ለመለወጥ እና አነስተኛ ድርሻ ያላቸውን የኩባንያ አባላት ከምዝበራ እና ኢፍትሃዊ አሰራር ለመጠበቅ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን አካቷል። በዚህ ረገድ ሕጉ ያደረጋቸው ለውጦች በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህም፡-

1. ግልጽነትን ማስፈን፡- አንድ ኩባንያ ከኩባንያው ጋር ዝምድና ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች አነስተኛ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የተሟላ መረጃ እንዲያገኙ እና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ የሚረዱ በርካታ ድንጋጌዎች በህጉ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን አንቀጽ 323፣ 324፣ 325፣ 406፣ 392፣ 393፣ 396፣ 503 እና 504 ን መጥቀስ ይቻላል።

2. ተጠያቂነትን ማስፈን፡- የንግድ ማኅበር ሥራ አመራር በተለይ የዳይሬክተሮችን ኃላፊነት በማያሻማ መልክ የሚያስቀምጡ እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ አሰራሮችን ለመዘርጋት ያለሙ በርካታ ድንጋጌዎች በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ተካተዋል። በዚህ ረገድ አዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 308፣ 326፣ 327፣ 329፣ 339፣ 366(1)(2)፣ 367(2) 400 እና 406 ተጠቃሽ ናቸው።

3. በሥራ አመራር ውስጥ የማኅበርተኞችን ተሳትፎ ማጎልበት፡- አዲሱ የንግድ ሕግ ማኅበርተኞች በንግድ ድርጅታቸው አመራር ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚደነግጉ በርካታ ድንጋጌዎችን ተካተዋል። በዚህ ረገድ አዲሱ ሕግ አንቀጽ 312(3)፣ 316፣ 354፣ 362፣ 405፣ 406፣ 453፣ 520 እና 529 ን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እያንዳንዱ የአክሲዮን ማኅበር ድረ-ገጽ እንዲኖረው እና በድረ-ገጹም ላይ የማኅበርተኞችን ንቁ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚረዱ መረጃዎች እንዲሰጥ የሚደነግጉት አንቀጽ 492-494 ይህን ያሳያሉ።

3. የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ማስጠበቂያ መንገዶች

የንግድ ሕጉ ያስቀመጣቸዉ የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ማስጠበቂያ ድንጋጌዎች በሁለት ዓይነት ሊታዩ የሚችሉ ሲሆኑ እነዚህም ጉዳትን ተከላካይ /Preventive/ እና የማስተካከያ /restorative/ ናቸዉ። ጉዳት ተከላካይ ድንጋጌዎች አነስተኛ ባለአክስዮኖች ላይ የመጨቆን ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ውሳኔዎችን ከመወሰናቸዉ በፊት አነስተኛ ባለአክስዮኖች እንዲሰማሙ በመደንገግ ዉሳኔዉን ከመፈፀም እንዲያግዱት ያስችላቸዋል። በሌላ በኩል የማስተካካያ ድንጋጌዎች ጉዳት ከደረሰ በኋላ የማስተካከያ መንገዶችን ይደነግጋሉ። ለምሰሌ በፍርድ ቤት ከሶ ካሳ የማስከፈል መብት ከእነዚህ የሚመደብ ነዉ። ከጉዳት በኋላ በፍርድ ቤትም ይሆን በአስተዳደራዊ መንገድ ማስተካከል ከባድ ስለሚሆን ችግሮችን አስቀድሞ መከላከል ከማስተካከል የተሻለ ይሆናል።

ማንኛዉም የድምፅ የበላይነትን በመጠቀም ከፍተኛ ባለአክስዮኖች አነስተኛ ባለአክስዮኖችን አግልለዉ የማኅበሩን ሀብት ለግላቸዉ የሚጠቀሙበት አሰራር በአነስተኞች ላይ በደል ማድረስ ነዉ። አነስተኛ ባለአክስዮኖች በኩባንያዉ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፉ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚያገል አሰራር የባለአክስዮኖችን መብት የሚጥስ ነዉ። ለአነሰተኛ ባለአክስዮኖች የመብት ጥሰቶች ህጎች የተለያዩ ዓይነት መፍትሔዎች የሚሰጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በቀጥታ የመክሰስ (የማስተካከያ እርምጃ የመዉሰድ) መብት ሲሰጡ ሌሎች ደግሞ በተዘዋዋሪ ይከለክላሉ። የኢትዮጵያ ሕግ በአብዛኛዉ ለእንደነዚህ ያሉ የመብት ጥሰቶች የሚሰጠዉ ከአሁን በፊት ያለዉ ተዘዋዋሪ ነበር። በአዲሱ የንግድ ሕግ ግን በቀጥታ የመክሰስ (የማስተካከያ እርምጃ የመዉሰድ) መብትን ሰጥቶ እናገኘዋለን። በአብዛኛዉ ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ በጉባዔዉ የመብት ጥሰት ያስከተሉ ዉሰኔዎችን ዉድቅ ማስደረግ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ አማካኝነት ጉዳት በማኅበሩ ላይ ደርሶም ከሆነ እንዲከሰሱ በጠቅላላ ጉባዔዉ አሰወስኖ መክሰስ ነዉ።

4. የጉባዔ አካሄድ እና የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት

በጠቅላላ ጉባዔ አካሄድ ድንጋጌዎች ዉስጥ የአነስተኛ ባለአክስዮኖችን መብት የሚያስጠብቁት አሰራሮች በብዙ ሕጎች ሰፍረዉ ይገኛሉ። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ በደብዳቤ በድምፅ የመስጠት መብት፣ ጉባዔ በሚደረግበት ጊዜ አክስዮንን በማኅበሩ የማስቀመጥ ግዴታ አለመኖር፣ የድምር ድምፅ /Commulative Voting/ አሰራር እና አንድ አክስዮን አንድ ድምፅ የሚለዉ አሰራር በንግድ ህጋችን በቁጥር 383 (2) ስር ተመልክቷል። ይህ ንዑስ ቁጥር እያንዳንዱ አክስዮን አንድ ድምፅን ይሰጣል ይላል። የዚህ ድንጋጌ ዓላማ የተወሰኑ አክስዮኖች እጥፍ ድምፅ የሚያስገኙ፣ የሌሎች ደግሞ አንድ፣ የከፊሎቹ ግማሽ ወዘተ... በሚል ዓይነት ልዩነት እንዳይፈጠር ለመከላከል ነዉ። ስለዚህ በአንዳንድ አባላት የተለየ ድምፅ የሚያስገኝ ልዩ አክስዮን ሊኖራቸዉ አይችልም። በቦርድ አባላት ምርጫ ወቅት የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ማስጠበቂያ አሰራር የድምር ድምፅ አሰራር ነዉ። ይህ ግን በሕጋችን በግልፅ የተቀመጠ ደንብ አይደለም። ነባሩ ንግድ ሕግ ቀጥር 352 ስለተመጣጣኝ ዉክልና የሚናገር ሲሆን በግልፅ የድምር ድምፅ አሰራር ግን አይደነገግም።

ሌላዉ ከጠቅላላ ጉባዔዉ ዉሳኔ ጋር በተዘዋዋሪ የሚያያዘዉ እና የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ጉዳይ አዳዲስ አክስዮኖች ሲወጡ እያንዳንዱ አባል ባለዉ ድርሻ መጠን የመግዛት መብት ነዉ። ይህ በቁጥር 345 (4) እና በቁጥር 470(1) ላይ የተቀመጠ መርህ ነዉ። የዚህ መርህ ዓላማ በማኅበሩ ዉስጥ ያለዉን የይዞታ ስብጥር ማስጠበቅ ሲሆን ጠቃሚነቱ በማኅበሩ ዉስጥ ያለዉ የኃይል ሚዛን እንዲጠበቅ ያደርጋል።

5. አነስተኛ ባለአክስዮኖች ከኦዲትና ቁጥጥር አንፃር ያላቸዉ መብቶች

ከኦዲት ሥራ ጋር የተያያዘ የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብቶች በአዲሱ የንግድ ሕግ ዉስጥ ተካተዋል። እነዚህም በቁጥር 343(2) እና በቁጥር 355 ላይ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ናቸዉ። "ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ዉስጥ ቢያንስ 20% ያለዉ ባለአክስዮን (ባለአክስዮኖች) ራሳቸዉ የመረጡትን የውጭ ኦዲተር መሾም ይችላሉ" በማለት የአነስተኛ ባለአክስዮኖች የራሳቸዉን ኦዲተር የመሾም መብት እንዳላቸዉ ይናገራል። ይህን መብት አነስተኛ ባለአክስዮኖች ከተጠቀሙበት በማኅበሩ ዉስጥ ቢያንስ ሁለት ኦዲተሮች (በጠቅላላ ጉባዔዉ የሚሾምና በአነስተኛ ባለአክስዮኖች የሚሾም) ይኖራሉ ማለት ነዉ። ይህ ኦዲተሮች ለዳይሬክተሮች ወይም ለአብላጫ ባለአክስዮኖች በመወገን ሊፈጠሩ የሚችሉትን አደጋ ይቀርፋል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በተጨማሪ ቁጥር 355 ላይ ነፃ ኦዲተር እንዲሾም ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለዉ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ማመልከቻ ስለማቅረብ ይናገራል። የማኅበሩ ሥራ አመራር አነስተኛ የአክስዮን ድርሻ ያላቸዉን ማኅበርተኞች ወይም ማኅበሩን በሚጎዳ አኳኋን መከናወንና

አለመከናወኑን መርምረዉ ሪፖርት የሚያቀርቡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ኤክስፐርቶች መሾም አለበት። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከማኀበሩ ካፒታል አስር በመቶ (10%) ያለዉ (ያላቸዉ) ባለአክስዮኖች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴሩ አቤቱታ ማቅረብና ማኀበሩ ኦዲት እንዲረግ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ከኦዲት ስራ ጋር የተያያዙ የአነስተኛ ባለአክስዮኖች መብት ቀላል አይደሉም። በማኀበሩ አስተዳዳሪዎች ወይም በከፍተኛ ባለ አክስዮኖች የሚደርስባቸውን የመብት ጥሰት ለመግታት እና መብታቸውን ለማስከበር እጅግ ጠቃሚ ናቸዉ።

6. አክስዮን ሸጦ የመውጣት የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብት

በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 292 መሰረት የማህበሩን ዋና ገንዘብ ዘጠና በመቶ የሚወክለ አክስዮኖች በአንድ ጊዜ በማህበርተኛ የተያዙ እንደሆነ አነስተኛ ባለአክስዮኖች ማህበርተኛው አክስዮኖቻቸውን እንዲገዛቸው የመጠየቅ መብት አላቸው። ጥያቄ አቅራቢው ባአክስዮን አክስዮኖቹ ስለሚገዙበት ሁኔታ በተለይም የአክስዮኖቹን ዋጋ የንግድ ሕግ ስለወሰነበት መንገድ መረጃ ከጥያቄው ጋር ማቅረብ አለበት። ጥያቄ የቀረበለት ማህበርተኛ የቀረበለትን ዋጋ ያልተቀበለ እንደሆነ ማህበሩ በተመዘገበበት ቦታ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የአክስዮኖቹን ዋጋ የሚወስን ባለሞያ መሾም አለበት። አክስዮኖቹን ለመሸጥ ጥያቄ ያቀረበው ባለአክሲዮን የአክሲዮኖቹን ዋጋ ለመወሰን የወጣውን ወጪ መሸፈን አለበት። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አክስዮን እንዲገዛ ጥያቄ የቀረበለት ማህበርተኛ የሰጠው ዋጋ ተማኙ ባለሞያ ከወሰነው ያነሰ እንደሆነ ወጪውን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሸፍን ፍርድ ቤቱ ሊያዘው ይችላል።

በአጠቃላይ የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብት መጠበቅ የማኀበሩን ህልውና መጠበቅ ነዉ። ይህም የማኀበሩን መልካም አስተዳደር የተሳካና የንግድ አላማውን ዉጤታማ ያደርገዋል። በዚህ የተነሳ አነስተኛ ባለአክስዮኖች ከሌሎች ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው ባለአክስዮኖች፣ ከዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ከጠቅላላ ጉባዔዉ እና በኦዲተሮች አማካኝነት ከሚሰነዘሩ ያልተገቡ ጫናዎችና የመብት ጥሰቶች መጠበቂያ መንገዶች በአዲሱ የንግድ ሕግ ተደንግገዉ ይገኛሉ።

## 3. የእሽሙር ማህበር (JOINT VENTURE)

### የእሽሙር ማህበር ምንነት

የእሽሙር ማህበር በአዲሱ የንግድ ህግ ከተካተቱ ሰባት የንግድ ማህበር አይነቶች አንዱ ሲሆን ማህበሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በመካከላቸው በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት የሚያቋቁሙት በሦስተኛ ወገኖች የማይታወቅና የሕግ ሰውነት የሌለው የንግድ ማህበር እንደሆነ በንግድ ህጉ አንቀፅ 234 ስር

ተደንግጓል። ይሁንና የማህበሩ መኖር በሦስተኛ ወገኖች ከታወቀ ጊዜ አንስቶ ማህበሩ ከእነዚህ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንደ ህብረት ሽርክና ማህበር ይቆጠራል። የእሽሙር ማህበር ከሌሎች የንግድ ማህበራት ከሚለዩት ባህርያት የንግድ ማህበሮች የማስመዝገብ ሥርዓቶች በዚህ ማህበር ላይ ተፈጻሚ የማይሆን መሆኑ ነው።

የእሽሙር ማህበር ባህርያት

የእሽሙር ማህበር መመስረት አንደኛ ሽሪክ ያለው ነገር ግን ሌላኛው ሽሪክ የሌለውን ጠንካራ ጎን ለመጋራት ያስችላል። ለምሳሌ እውቅና እና መልካም ስም ያለው የንግድ ስም (Brand Name ) ካለው የንግድ ማህበር ጋር ሽርክና የገባ ካንፓኒ ከመልካም ስሙ ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ማለት ሁለት ሽሪኮች ያሏቸውን ጠንካራ ሀብት (የገንዘብ፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ እና የመሳሰሉትን) በማቀናጀት የተሻለ ውጤታማ የሆነ ማህበር ይመሰርታሉ። የሚከተሉት የእሽሙር ማኅበር ልዩ ባህሪያት ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ፡-

1. ህጋዊ ሰዉነት የሌለዉ ስለመሆኑ

የእሽሙር የሽርክና ማኅበር ህጋዊ ሰዉነት የለዉም ሲባል በሽሪኮች መካከል ያለዉ ግንኙነት ተራ ዉል ግንኙነት ነዉ ማለት ነዉ። በመሆኑም ሽሪኮቹ የአንድ ተቋም አባላት ሳይሆኑ ተራ ዉል ተዋዋይ ወገኖች ናቸዉ። ይልቁን ህጋዊ ሰዉነት ስለሌለዉ የንግዱ ስራ የሚሰራዉ በሽሪኮቹ ስም ነዉ። ስለሆነም እያንዳንዱ ሽሪክ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ሲዋዋል፣ ዉሉን ሲፈጽም ወዘተ... በራሱ ስም ነዉ። ይህም የሚሆነዉ የሽርክና ማኅበሩ ለሶስተኛ ወገኖች ስውር ስለሆነ ነዉ። የእሽሙር ማኅበር ህጋዊ ሰዉነት ስለሌለዉ ሽሪኮቹ የሚያዋጡት ገንዘብ እና ሀብት የማኅበሩ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም በንግድ ህጉ ቁጥር 236/2 ስር እንደተደነገገው ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እያንዳንዱ ሽሪክ ያዋጣው ንብረት ባለቤት ነዉ።

2. ለሶስተኛ ወገኖች የማይታወቅ መሆኑ

ለሶስተኛ ወገኖች አለመታወቁ (ድብቅ መሆኑ) ያለመመዝገቡ ውጤት ነዉ። የሕግ ሰዉነት ስለማይኖረዉ እንዲመዘገብ አይደረግም። ካልተመዘገበ ደግሞ ለህዝብ የሚታወቅበት መንገድ አይኖርም ማለት ነዉ። እዚህ ላይ የእሽሙር ሽርክና ማኅበር ድብቅነት የመመዝገብ ግዴታ ካለመኖሩ ብቻ የመነጨ ሳይሆን ይልቁንም በህጉ ታዉቆ እና ታስቦበት የተደነገገ ነዉ። አሰራሩም ያልተለመደ እና ግራ አጋቢ ቢመስልም በሌሎችም አገሮች የተለመደ እንጂ ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ ያለ አይደለም።

3. ቅንጅት መፍጠር (Creates Synergy)

የእሽሙር ማህበር በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ማህበራት መካከል ሲመሰረት አንደኛው ሸሪክ የሌላኛውን ባህርይ ለመጠቀም ያስችለዋል (extract the qualities of each other)። እንዲሁም አንዳቸው ያንዳቸውን ጥቅም ለመጋራት ይችላሉ። በመሆኑም ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው ቅንጅት መፍጠር ይችላሉ ማለት ነው( a joint venture to generate synergies between them for a greater good)።ይህም በተዘዋዋሪ ትልቅ ካፒታልን ለመፍጠር የሚያስችላቸው ሲሆን ወጪያቸውንም እንዲቀንሱ ይረዳቸዋል።

4. ስጋት/አደጋን መጋራት (Risk and Rewards can be Shared)

የእሽሙር ማህበር በአንድ ሀገር ውስጥ ባሉ ድርጅቶች ወይም በተለያዩ ሀገሮች ባሉ ድርጅቶች መካከል ሊደረግ የሚችል ሽርክና በመሆኑ በእነዚህ ሀገሮች ሊኖሩ የሚችሉ የባህል ልዩነቶች (diversifications in culture)፣ የቴክኖሊጂ፣ የመልከዓ መድር አቀማመጥ ጥቅምና ጉዳት (geographical advantage and disadvantage)፣ የተደራሽ ደንበኛ (target audience) ሁኔታዎች በማህበሩ ላይ ሊፈጥር የሚችለው ተፅዕኖ ትኩረት የሚሻ ነው። በመሆኑም በሽሪኮች መካከል የሚደረግ ስምምነት የአደጋ ስጋቶችን እና ጥቅሞች ለመጋራት ያስችላቸዋል።

5. የተለየ ህግ አለመኖር (No Separate Laws)

የእሽሙር ማህበር የሕግ ሰውነት የሌለው የንግድ ማህበር በመሆኑ ማህበሩን የሚያስተዳድር የተለየ ሕግ አይኖርም። እንዲሁም ይህን ማህበር በተለየ ሁኔታ የሚያስተዳድር አካልም የለም(no separate governing body which regulates the activities of the joint venture.)።

የእሽሙር ማህበር ጥቅሞች (advantages of a Joint Venture)

1. የምጣኔ ሀብትን ማሳደግ (Economies of Scale)

የእሽሙር ማህበር ሽሪኮች ወይም ድርጅቶች ሀብታቸውን ወይም ካፒታላቸውን በማጣመር ስለሚቋቋሙ ህብረት መመስረታቸው ውስን አቅማቸውን ለማሳደግ ይረዳቸዋል።

2. አዲስ ገበያ መድረስ እና የአውታረ መረቦችን ስርጭት (Access to New Markets and Distribution Networks)

አንድ ድርጅት ከሌላ ድርጅት ጋር የእሽሙር ማህበር ስምምነት ሲያደርግ አንደኛው የሌላኛውን የገበያ እድል የመጠቀም እና የማሳደግ አጋጣሚን ይፈጥርለታል። ለምሳሌ አንድ የአሜሪካ ካንፓኒ ከህንድ ካንፓኒ ጋር

የእሽሙር ማህበር ስምምነት ቢያደርግ በህንድ ውስጥ የሚኖርን ሰራ፣ የተለያየ የመግዛት ፍላጎት እና አቀም ያለውን ገበያ የመድረስ ጥቅም ያገኛል ማለት ነው። በተመሳሳይ መልኩ የህንድ ካንፓኒም በአሜሪካ ውስጥ የሚገኝን ጥሩ የመክፈል አቅም ያለውን ገበያ መቀላቀል ይችላል ማለት ነው።

3. ፈጠራን ማሳደግ (Innovation)

የእሽሙር ማህበር ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ከቴክኖሎጂ አንጻር ለማሻሻል እድልን ይፈጥራል። በመሆኑም የቴክኖሎጂ መሻሻል እና የፈጠራ ስራዎች ማደግ የተሻሉ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ውጤታማ በሆነ ዋጋ( efficient cost) ለማቅረብ ያስችላል። አለም አቀፍ ድርጅቶች አዳዲስ ምርቶችን በቅናሽ ዋጋ በተሻለ ጥራት እንዲያቀርቡ ያደርጋል ማለት ነው።

4. የማምረቻ ወጪን ማሳነስ (Low Cost of Production)

ሁለት እና ከሁለት በላይ ሽሪኮች ሲጣመሩ ውጤታማ በሆነ ዋጋ ምርትን ለደንበኞች ማድረስ አንዱ አላማቸው ነው። ይህም የሚሆነው የማምረቻ ዋጋን መቀነስ ሲቻል ነው። በመሆኑም የማምረቻ ዋጋን በጋራ በመቀነስ የተሻለ ምርት እና አገልግሎትን ለደንበኞች ያቀርባሉ።

የእሽሙር ማህበር ጉዳት (Disadvantages of a Joint Venture)

1. ግልፅ ያለሆነ አላማ፡- ሽሪኮች በእሽሙር ማኅበር ሲጣመሩ አላማቸውን በጣም ግልፅ በሆነ ሁኔታ የማያስቀምጡበት አጋጣሚ በርካታ ነው። እንዲሁም የማህበሩ አላማ ለሁሉም የማህበሩ አባላት በአግባቡ ላይገለፅላቸው ይችላል።

2. ተለዋዋጭነት ሊገደብ ይችላል (Flexibility can be restricted)፡- እንደየሁኔታው መስራት ወይም ተለዋዋጭነት ሲገደብ አባላቱ የግል ቢዝነሳቸውን ቸል በማለት ወደ እሽሙር ማኅበሩ የበለጠ ትኩረት ሊሰጡ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የግል ቢዝነሳቸውን ሊጎዳው ስለሚችል ለማህበሩ የሚያበረክቱት አስተዋፆ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

3. እኩል ተሳትፎ ያለማድረግ፡- በመርህ ደረጃ የማህበሩ ሽሪኮች እኩል ሀላፊነት እና ደረሻ ያላቸው ቢሆንም በተግባር ግን ሁሉም አባለት እኩል አስተዋፆ ላያደርጉ ይችላሉ።

4. ያለመመጣጠን፡- የእሽሙር ማህበር ሽርክና የሚመሰርቱት በተለያየ የባለሞያ ብቃት እና ብዛት፣ የሀብት እና የኢንቨስትመንት ደረጃ ባላቸው ሁለት እና ከሁለት በላይ ካንፓኒዎች ስለሆነ ይህ ደግሞ ያለመመጣጠን ሊያስከትል ይችላል። ይህ መሆኑ ደግሞ በማህበሩ ውጤታማነት አሉታዊ ተፅኖ ሊያሳድር ይችላል።

የእሽሙር ማህበር የመዋጮ ዓይነትና መጠን

የመዋጮ ዓይነትና መጠን በተመለከተ ለሽርክና ማህበር የተደነገገው ለእሽሙር ማኅበር ተፈጻሚ እንደሚሆን የንግድ ህጉ አንቀፅ 236 ያመለክታል። በዚሁ መሰረት በንግድ ህጉ አንቀፅ 186 ስር እንደተቀመጠው እያንዳንዱ ሽሪክ ጥሬ ገንዘብ፣ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ የሞያ አገልግሎት፣ የንግድ ምልክት፣ መልካም ስም፣ ፓተንት፣ ኮፒ ራይት፣ የሊዝ መብት፣ የአላባ ጥቅም ወይም ሌላ የዓይነት መዋጮ መክፈል አለበት። መዋጮው የማህበሩ ሀብት እንዲሆን ወይም ማህበሩ እንዲጠቀምበት ሆኖ ሊከፈል ይችላል። ሽሪኮች ለማህበሩ የሚያስገቡት መዋጮ የማህበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስፈልገው ዓይነትና መጠን እንዲሁም ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መጠኑ እኩል መሆን አለበት።

የዓይነት መዋጮ ግምት በሽሪኮች ስምምነት የሚወሰን ሆኖ በዓይነት የተከፈለ መዋጮ ግምት የተጋነነ ሆኖ ከተገኘ ያዋጣው ሽሪክ በግምቱና በትክክለኛው ዋጋው መካከል ያለውን ልዩነት በጥሬ ገንዘብ መክፈል አለበት። ልዩነቱን በጥሬ ገንዘብ መክፈል ካልቻለ ድርሻው በትክክለኛው ግምት መሠረት ይሆናል።በተጨማሪ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እያንዳንዱ ሽሪክ ለከፈለው መዋጮ ባለቤትነቱን እንደያዘ ይቆያል። እንዲሁም ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በማህበሩ ውስጥ ያለን ድርሻ ማስተላለፍ የሚቻለው ሁሉም ሽሪኮች ሲስማሙ ብቻ ነው።

የማህበሩ ሥራ አመራር

የእሽሙር ማህበር ሽሪክ ወይም ሽሪክ ባልሆነ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሥራ አስኪያጆች ሊመራ የሚችል ሆኖ ሥራ አስኪያጅ ያልተሾመ እንደሆነ ሁሉም ሽሪኮች የሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን ይኖራቸዋል። የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በማህበረተኞች መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል። ሆኖም ይህ ስምምነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።ሥራ አስኪያጁ የማህበሩን ሥራዎች ለሽሪኮቹ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህን ግዴታ የሚያስቀር ማንኛውም ስምምነት ዋጋ አይኖረውም። የማህበሩ ሽሪኮች ደግሞ የሥራ አስኪያጁን ሥራ መቆጣጠር ይችላሉ። እንዲሁም የማህበሩ ሽሪክ የሆነ ሥራ አስኪያጅ በበቂ ምክንያት ሊሻር ይችላል።

ማህበሩ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ስላለው ግንኙነት

በንግድ ህጉ እንደተደነገገው የእሽሙር ማህበር ለሶስተኛ ወገኖች የማይታወቅ በመሆኑ ለሦስተኛ ወገኖች የሚታወቀው የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ብቻ ነው። ለማህበሩ ዕዳዎች እና ግዴታዎች ኃላፊና ተጠያቂ የሚሆነውም እሱ ብቻ ነው። የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ያልሆነ ሽሪክ ለማህበሩ ዕዳዎች ለሥራ አስኪያጁ ተጠያቂ የሚሆነው በማህበርተኞች መካከል በተደረገው የውል ጽሁፍ በተወሰነው መጠን ብቻ ነው። ሥራ

አስኪያጅ ያልሆነ ሸሪክ በማህበሩ ሥራ አመራር ተካፊይ ከሆነ ለሦስተኛ ወገኖች ከሥራ አስኪያጁ ጋራ በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል። ማንኛውም የማህበሩ ሸሪክ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችለው በራሱ ስም ብቻ ነው።

ሸሪክን ከማህበሩ ስለማስወጣት

በአንድ ሸሪክ ጥፋት ምክንያት የእሽሙር ማህበር እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲቀርብና ሌሎች ሸሪኮች ማህበሩ እንዳይፈርስ ሲያመለክቱ ፍርድ ቤቱ ማህበሩ እንዲፈርስ በመወሰን ፈንታ ጥፋተኛ የሆነውን ሸሪክ ከማህበሩ እንዲወጣና ማህበሩ እንዲቀጥል ለማዘዝ ይችላል።ይሁንና ከማህበሩ እንዲወጣ የተደረገ ሸሪክ በወጣበት ጊዜ የነበረው ድርሻ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት አለው። በተጨማሪ አንድ ሸሪክ ከማህበሩ የሚወጣበት ምክንያት በማህበርተኞች መካከል በሚደረግ ውል ሊወሰን ይችላል።

የማህበሩ ማፍረሻ ምክንያቶች

የንግድ ማህበራት የሚፈርሱበትን ሁኔታ የሚመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማህበሩ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ሲሆን የእነዚህን ምክንያቶች ተፈፃሚነት የሚያስቀር ማንኛውም ስምምነት ተቀባይነት እንደማይኖረው የንግድ ህጉ አንቀፅ 242/2 ያስቀምጣል።ምክንያቶቹም፡-

- ሸሪኮች ማህበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ ሲስማሙ፤
- ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሲሆን ከሸሪኮች አንዱ እንዲፈርስ ለማህበሩ ጥያቄ ያቀረበ እንደ ሆነ፤
- ሁሉም የማህበሩ ድርሻዎች በአንድ አባል የተያዙ እንደሆነ፤
- ማህበሩ እንዲቀጥል የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ከማህበሩ ሸሪኮች አንዱ የሞተ ወይም የከሠረ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ፤
- በማህበርተኞች መካከል በሚደረግ ውል ለሥራ አስኪያጁ ማህበሩን ለማፍረስ ሥልጣን ተሰጥቶት ከሆነ ሥራ አስኪያጁ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን።

በመጨረሻ በንግድ ህጉ ስለእሽሙር ማህበር የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ስለህብረት ሽርክና ማህበር የወጡት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በእሽሙር ማህበር ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በንግድ ህጉ አንቀፅ 244 ስር ሰፍሮ ይገኛል።

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲሱ የንግድ ህግ

የንግድ ማህበራት አንድና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን አዋጥተው በጋራ ለመስራት ተስማምተው የሚመሰርቱት የንግድ ድርጅት ነው። የተለያዩ የንግድ ማህበራት የሚመሰረቱ

ሲሆን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በኢትዮጵያ ህግ ስርአት እውቅና ከተሰጣቸው የንግድ ማኅበራት አንዱ ነው። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ምንነት፣ አመሰራረት፣ ሲፈርስ ያለው ውጤት እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

1. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ምንነት

በአዲሱ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 495 መሰረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማለት ዋና ገንዘቡ በሙሉ አስቀድሞ የተከፈለ፣ በአክስዮን የተከፋፈለ እና ባለአክስዮኖች መዋጮቸውን ገቢ እስካደረጉ ድረስ ለማኅበሩ ዕዳ ኃላፊ የማይሆኑበት የንግድ ማኅበር ነው። ማናቸውም ማህበርተኛ ካስገባው መዋጮ በላይ ሀላፊ የማይሆንበት ማህበር ማለት ነው።

2. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባህሪያት

- የማኅበሩ አነስተኛ ዋና ገንዘብ ከአስራ አምስት ሺህ ብር ያነሰ መሆን አይችልም።
- እያንዳንዱ አክስዮን ላይ የሚገፈዉ ዋጋ ከአንድ መቶ ብር በታች መሆን አይችልም፣
- በሁሉም አክስዮኖች ላይ የተገፈ ዋጋ እኩል መሆን አለበት።
- ኃላፊነተ የተወሰነ መሆኑ፡- እንደ አክሲዮን ማህበራት ሁሉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ላይ ካላቸው ድርሻ በላይ በእዳ ሊጠየቁ አይችሉም ወይም የማህበር አባላት የዕዳ ተጠያቂነት በማኅበሩ ውስጥ ባላቸው አክስዮኖች ዋጋ የተወሰነ ነው። ይህ ማለት የማኅበሩ ዕዳ ከማኅበሩ ሀብት ላይ ሊከፈል ካልቻለ የማኅበሩ አባላት በማኅበሩ ውስጥ ካላቸው አክስዮን በላይ ኃላፊ የማይሆንበት ነው። አንድ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ድርጅቱ በሚሰራው ማንኛውም የንግድ ስራ ምክንያት ለሚመጣ ኪሳራ፣ ጉዳት ካሳ የመሳሰሉት ፍትሐብሄራዊ ተጠያቂነት የማህበሩ አባል በማህበሩ ውስጥ ካዋጣው ድርሻ በላይ ቢሆንም እንኳን ወደ የግል ንብረት የማይተላለፍ መሆኑን የሚያመለክት ነው። አባላቱም በቤተ ዘመዶች እና በሚተዋወቁ ሰዎች መካከል የተወሰኑ እንጂ ለህዝብ የሚወጣ አክሲዮን የላቸውም። የአክሲዮን ዝውውሩም እንዲሁ በአባላቱ ፈቃድ ላይ የተወሰነ ነው።

3. የማኅበሩ አቋቋምና አመሰራረት

ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመሰራረት ዋና ገንዘቡ በሙሉ ሲከፈል እና የመመስረቻ ፅሁፉ በንግድ መዝገብ ሲገባ ነው። በጥሬ ገንዘብ በተሸጡ አክሲዮኖች ላይ የተገፈው ዋጋ ማህበሩ ከመመዝገቡ በፊት በመመስረት ላይ ባለው ማህበር ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት። በንግድ መዝገብ የሚገባው የመመስረቻ ፅሁፍ የሚይዘው የባለአክሲዮኖች ስም፣ ዜግነትና አድራሻ የማህበሩን ስም፣ ዋና

መስሪያ ቤት፣ እንዲሁም ቅርንጫፎች፣ የማህበሩን የንግድ አላማ፣ ዋና ገንዘቡ መከፈሉም ማሳየት፣ የባለአክሲዮን በአይነት ወይም በገንዘብ የተከፈለውን መጠን፣ የትርፍ አከፋፈል ስርአቱን፣ የዳይሬክተሮች ስራ አስኪያጅ ኦዲተሮች ብዛት እና ስልጣን የመሳሰሉትን ማካተት አለበት። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ዓላማውን የሚገልጽ ስም ይኖረዋል። የማኅበሩ ዓላማ ማንኛውም ዓይነት ቢሆን ሁልጊዜ የንግድ ማኅበር ነው።

4. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተመራጭ የሚያደርጉ ጉዳዮች

- ማህበሩን ለመመስረት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ የማይጠይቅ መሆኑ፣
- ያልተገደበ የጊዜ ቆይታ ያላቸው መሆኑ፡- ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተወሰኑ አባላት የግል ሁኔታ ህልውና በቀላሉ አደጋ ላይ ሊወድቅ አይችልም። ስለዚህ በገበያው ውስጥ ረጅም ጊዜ የመቆየት እድል አለው።
- ካፒታሉን ለማሳደግ ቀላል መሆኑ፡- ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ በመሆኑና ከፋይናንስ ተቋማት በቀላሉ ብድር ማግኘት የሚችል በመሆኑ ካፒታሉን ለማሳደግና ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

5. የማኅበሩ ሥራ አመራር

ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲመራ በመመስረቻ ፅሁፍ ሊወሰን ይችላል። በአስገዳጅነት ባይሆንም የዳይሬክተሮች ቦርድ የአባላቱ ቁጥር ከሶስት እስከ ሰባት ይሆናል። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አባላት የዳየሬክተሮች ቦርድ የመምረጥ መብት እውቅና ስለተሰጣቸው ቦርዱን ይመርጣሉ።

በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማኅበር ወይም ሌላ ተቋም አስተዳዳሪ (ዳይሬክተር) ሆኖ ሊሾም ይችላል፤ ይህ የሆነ እንደሆነ ተመራጩ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማኅበር ለተመረጠባቸው ዓመታት የሚያገለግል ቋሚ ተወካይ ወዲያውኑ መመደብ አለበት። ቋሚ ተወካዩ የለቀቀ እንደሆነ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ያልቻለ እንደሆነ ምትክ ተወካይ በተቻለ ፍጥነት መመደብ አለበት። ቦርድ ለመሆን የእድሜ ክልል፣ ስነ-ምግባር እንዲሁም ከማህበሩ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ተግባር አለመፈፀም ከግምት መግባት አለበት።

በአዲሱ ንግድ ህግ አንቀፅ 296 (2) መሰረት የማኅበር አባል ያልሆነ ሰው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆን ይችላል። የዳሬክተሮች ቦርድ የመጀመሪያ ሹመት ከሆነ በመመስረቻ ፅሁፍ ተሹመው ለፈራሚዎች ጉባኤ ይቀርባል። ቦርዱ ሲመረጥ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና እንዲያሲዙ በመመስረቻ ፅሁፍ ሊወሰን ይችላል፣ በመመስረቻ ጽሑፉ የዋስትናውን አይነት፣ መጠን እና እንዲካተት ይደረጋል። ኀላፊነቱ የተወሰነ

የግል ማህበር ስራ አስኪያጅን በባለአክሲዮን የሆነ ወይም ያልሆነ በጠቅላላ ጉባኤ ወይም ማህበሩ በዳሬክተሮች ቦርድ እንዲመራ በመመስረቻ ፅሁፍ የተወሰነ ከሆነ ቦረዱ ስራ አስኪያጁን በተቀጣሪነት የሚሾም ይሆናል።

6. ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል የማህበር የሚፈርስባቸው ምክንያቶች

የንግድ ማኅበር በሚከተሉት ጠቅላላ ምክንያቶች ይፈርሳል፡-

- የተቋቋመበትን ዓላማ ሲፈጽም ወይም ለመፈጸም ሳይችል ሲቀር፣
- የማኅበሩ አባላት እንዲቀጥል ካልተስማሙ በስተቀር የማኅበሩ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ፣
- ማኅበርተኞች የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲስማሙ፣
- በማኅበሩ አባላት መካከል ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን በማኅበሩ አባላት ጥያቄ ፍርድ ቤት በበቂ ምክንያት ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን ማለትም ፍርድ ቤት ማህበሩ የሚፈርስበትን በቂ ምክንያት ሊለው የሚችለው አባላት መካከል ብርቱ አለመግባባት ኖሮ አለመግባባቱ የማህበሩ አላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስተጓጉል ሲሆን ነው። የማህበሩ አለመግባባት ምክንያት እንዲፈርስ ፍርድ ቤት ቢወስንም ከመወሰኑ በፊት የተወሰኑትን የማህበሩ አባላት ድርሻቸውን ይዘው ከማህበሩ እንዲወጡ በማድረግ በቀሪ አባላት ማህበሩ አላማውን ለማሳካት በሚችልበት ሁኔታ ማስቀጠል የሚቻል በሆነ ጊዜ አለመግባባቱ ማህበሩን ለማፍረስ እንደ በቂ ምክንያት ተደርጎ አይወሰድም።
- የማኅበሩ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን።

ከላይ የተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአክሲዮን ማኅበር በሚከተሉት ምክንያቶች ይፈርሳል:-

- የባለአክሲዮኖች ቁጥር በሕግ ከተፈቀደው ዝቅ ሲልና በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ አባል መተካት ባለመቻሉ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው በቀረበ ማመልከቻ መሰረት የንግድ ማኅበራትን የሚመዘግበው አካል ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤
- የአስተዳደር አካላት የሌሉት በመሆኑ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤
- እነዚህ ሁለት ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው የንግድ ማኅበራት መዝጋቢው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጊዜ ገደቡን ለተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ወይም ማኅበሩ የአስተዳደር አካላትን አሟልቶ ሥራ እንዲቀጥል ሊፈቅድ ይችላል፤

• የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ካለ የተቆጣጣሪ ቦርድ ወይም ኦዲተሮች ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት ያልቻሉ እንደሆነ ጥቅም ባለው ሰው አመልካችነት ፍርድ ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል። በዚህ መሠረት የንግድ ማኅበር መዝጋቢውን አካል ሳያስፈቅዱ ከስድስት ወራት በኋላ ባለአክሲዮኞች እያወቁ ማኅበሩ ሥራውን እንዲቀጥል ያደረጉ ከሆነ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ማኅበሩ ለሚገባው ማንኛውም ዕዳ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ።

• የባለአክስዮኖቹ ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለ እና በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ሌላ ሰዉ ካልገባ ማኅበሩ ይፈርሳል። ይህ ካልሆነ የባለአክስዮኖቹ ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ዉስጥ የመመስረቻ ጽሁፉን በማሻሻል ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አድርጎ ማስመዝገብ ይቻላል።

• የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሶስት አራተኛ መጥፋት፦ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሶስት አራተኛ ከጎደለ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ከሌለ ስራ አስኪያጁ ስለ ማኅበሩ መፍረስ አለመፍረስ በባለአክሲዮኖች እንዲወሰን ማድረግ አለበት። ማኅበርተኞች ማኅበሩ እንዳይፈርስ ከወሰኑ ተጨማሪ መዋጮ በማድረግ የጎደለውን የማኅበሩን ዋና ገንዘብ መተካት አለባቸው። ማኅበሩ የዋና ገንዘቡን በሶስት አራተኛ መጉደሉ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በዘጠና ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቦርዱ ወይም ስራ አስኪያጅ የማህበሩን መፍረስ አለመፍረስ ካልወሰኑ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።

7. የማህበሩ መፍረስ ውጤቶች

i. ከንግድ መዝገብ ስለመሰረዝ

• አንድ የንግድ ማኅበር ሲፈርስና ሒሳቡ ተጣርቶ እንዳበቃ የሒሳብ አጣሪዎች ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ለንግድ ማኅበር መዝጋቢው አካል ማመልከት አለባቸው። ማህበሩ ከንግድ መዝገብ ከተሰረዘበት እለት በሚቀጥለው ቀን ጀምሮ ህጋዊ ሰውነት አይኖረውም። የንግድ መዝገብ ማህበር የሚመዘግብ እና ህጋዊ ሰውነት የሚሰጥ እስከሆነ ድረስ መዝጋቢው ማህበሩን ከመዝገቡ ሰረዘው ማለት ህጋዊ ሰውነት አይኖረውም ማለት ነው።

• የንግድ ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ መሰረዝ የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት ባለበት አካባቢ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ መገለፅ አለበት።

ii. የማኅበሩን መዝገቦች ጠብቆ ስለመያዝ

ϖ የፈረሰው ማኅበር የሒሳብ መዛግብት ለ10 ዓመታት አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተጠብቀው መቀመጥ አለባቸው፤

፹ ማንኛውም ሰው የሂሳብ መዝገቦችን ለመመርመር ይችላል።

---

ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽርክና ማኅበር በአዲሱ የንግድ ሕግ

አዲሱ የሀገራችን የንግድ ህግ የተለያዩ ጉዳዮችን በአዲስ መልክ አካቶ ወጥቷል። በህጉ ለውጥ ከተደረገባቸው ጉዳዮች መካከል ከንግድ ማህበራት አንፃር ያለው ለውጥ አንዱ ሲሆን ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር /Limited liability partnership/ በአዲስ መልክ እውቅና ተሰጥቶት በህጉ ተደንግጎ ይገኛል። በዚህ ጽሁፍ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽርክና ማኅበር ምንነት እና አመሠራረት፣ የሽርክና ማህበራትና ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽርክና ማህበር ባህርያት፤ ስለኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ሥራ አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ኃላፊነት፤ የማህበሩ ሽሪክ ስለሚወጣበት መንገድ፤ ስለማህበሩ መፍረስ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ተደሰዋል።

1. ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽርክና ማህበር ምንነት እና አመሠራረት

በአዲሱ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 221 መሰረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሙያና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት (professional and complementary service) ለመስጠት የሚያቋቁሙት የማህበርተኞቹ ኃላፊነት በመዋጮዋቸው የተወሰነ የንግድ ማኅበር ነው። ይህ ማለት ሰዎች በተለይም የሙያ ስራዎችን ለመስራት በሙያ ከሚመስሏቸው ሌሎች ሰዎችና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ አጋሮቻቸው ጋር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው የሚያቋቁሙት የሽርክና ማኅበር ነው።

ማህበሩ ስም ለማውጣት የተቀመጡት ማለትም ከሌላ ነጋዴ ወይም ጥቅም ጋር የማይጋጭ፣ የሦስተኛ ወገኖችን መብት የማይነካ እና የተቋሙን ዓላማ የሚገልጽ ማኅበርተኞች የፈቀዱት የመጠሪያ ስም ይኖረዋል። ከማህበሩ ስም በስተመጨረሻ ላይ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር" የሚል ሐረግ መጨመር አለበት። ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ጠበቆች፣ ኦዲተሮች፣ የሒሳብ ባለሙያዎች፣ አርክቴክቶች፣ የሥራ አመራር

አማካሪዎች እና የመሳሰሉት ባለሙያዎች (የተፈጥሮ ሰዎች አለያም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበራት) ሙያቸውን መሠረት በማድረግ የሚያቋቁሙት፣ ለባለሙያዎች ሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ይዘው ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ የሽርክና የሙያ ማኅበራት እንዲስፋፉ ያስችላል። ይህ አይነቱ የሽርክና ማኅበር የህግ አገልግሎትን፣ የሂሳብ መዝገትና ኦዲት ወይም ሌላ አይነት ቴክኒካዊ እውቀትን በሚጠይቁና የሙያ ፈቃድ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የስራ ዘርፎች ላይ በቅንጅት መስራት ለሚሹ ሙያተኞች አይነተኛ ምርጫ እንደሚሆን ይገመታል።

## 2. የሽርክና ማኅበራት አጠቃላይ ባህሪያት

የሽርክና ማኅበራት የሚጋሩት የጋራ ባህሪ ያላቸዉ ሲሆን ፡-

- የሸሪኮች አነስተኛ ቁጥር ሁለት ብቻ ሲሆን ከፍተኛ ቁጥር ግን ያለተገደ በመሆኑ፣
- የአንስተኛ ካፒታል መጠን በህግ ያልተደነገገ መሆኑ፣
- ማህበሩ የሚመሰረተው በአባላት መዋጮ መሆኑ፣
- አስተዳደራዊ ሥራዎችን በሚመለከት አባላቱ የሚወስኑ መሆኑ፣
- የሙያ ወይም የአገልግሎት መዋጮ የተፈቀደ መሆኑ፣
- የሥራ አስኪያጅ ብዛት አንድና ከአንድ በላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ የተፈቀደ መሆኑ፣
- ከሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር በስተቀር ሥራ አስኪያጆች ከአባላቱ መካከል ወይም ከውጭ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 3. ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽርክና ማኅበር ልዩ ባህርያት

ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር እንደ ሌሎቹ የሽርክና ማህበራት ሁሉ የራሱ የሆነ ባህሪያት አሉት። በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀፅ 222 መሰረት ይህ ማህበር ከአባላቱ የተለየ ህግ ሰውነት ያለው፣ እንደ መክሰስ መከሰስ እና በራሱ ስም ውል መዋዋል የመሳሰሉ ህጋዊ ድርጊቶች በራሱ ስም መፈፀም የሚችል ሲሆን የሸሪኮቹ መሞት፣ መክሰር፣ ከማህበሩ መውጣት ወይም በሽርኮቹ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ በማህበሩ ሕልውና፣ መብት ወይም ግዴታ ላይ ተፅዕኖ አይኖረውም።

ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እንደሌሎቹ ማህበራት (ከባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውጪ) የሚቋቋመው በመመስረቻ ፅሁፍ ብቻ ነው። ከዚህ በፊት በቀድሞ ሕግ የነበረው መተዳደሪያ ደንብ

በአዲሱ ሕግ ቀሪ ተደርጓል። የዚህን ዓይነት ማኅበራት መመስረት የሚችሉት የሙያ ፈቃድ ባላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የሽርክና ማኅበራት ነው።

4. ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ተመራጭ የሚያደርጉ ጉዳዮች

በቀላሉ ለመመስረት የሚቻል መሆኑ፡- ከሌሎች ማህበራት ጋር ሲነፃፀር የሽርክና ማህበርን ለመመስረት የሚወስደው ጊዜና ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ በቀላሉ ህጋዊነትን በማግኘት ወደ ሥራ ለመግባት ያስችላል።

በአነስተኛ ካፒታል መመስረት የሚቻል መሆኑ፡- ከግለሰብ ነጋዴ ቀጥሎ በአነስተኛ ካፒታል ሊመሰረት የሚችለው የንግድ ማህበር የሽርክና ማህበር ነው።

የተሻለ ካፒታል ለማሰባሰብ የሚያስችል መሆኑ፡- የሽርክና ማህበራት ከግለሰብ ነጋዴ የሚለዩት ሁለትና ከሁለት በላይ ሆነው የሚመሰርቱት በመሆኑ እያንዳንዳቸው ሸሪኮች ከግለሰብ ነጋዴ የተሻለ በዓይነትና በገንዘብ በማዋጣት ካፒታላቸውን የተሻለ ማድረግ መቻላቸው ነው። የተሻለ ካፒታል ማዋጣት ከቻሉ ደግሞ የተሻለ የንግድ ሥራ ላይ የተሻለ አቅም ኢንቨስት ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው።

የሽርክና ማህበራት አባላት ድርጅታቸውን በራሳቸው ማስተዳደርና መምራት መቻላቸውም ይህን አይነት ማህበር ተመራጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው።

5. ስለማህበሩ ሥራ አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ኃላፊነት

ማህበሩ ምንም እንኳን ከተፈጥሮ ሰው በተጨማሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበርን በአባልነት መያዝ የሚችል ቢሆንም ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ መሾም የሚችለው የተፈጥሮ ሰው የሆነ እና ማህበሩ አገልግሎት በሚሰጥበት ሞያ ፈቃድ ያለው ሸሪክ ብቻ ነው። የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የማህበሩን ዓላማ ለማሳካት በማህበሩ ስም ማንኛውንም ሕጋዊ ተግባር ለማከናወን የሚችል ሲሆን ይህን ሥልጣን የሚገድቡ ስምምነቶች ሶስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ የሚሆኑት በንግድ መዝገብ የተመዘገቡ ወይም ሦስተኛ ወገኖች የሥራ ኃላፊነቱን የሚያውቁ መሆናቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።

የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር የሚደነገገው የማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ ሲሆን ይህም መመስረቻ ፅሁፍ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በአባላት ሁለት ሶስተኛ (2/3) ድምፅ በሚሰጥ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል። ሌላ ማንኛውም ውሳኔ በአብዛኛዎቹ አባላት የድምፅ ድጋፍ ማለትም (50+1) ሊፀድቅ ይችላል። የማህበሩ ዜግነት ወይም የሥራ መስክ ለመለወጥ የሚሰጥ ውሳኔ የሚፀናው በ3/4ኛ (ሶስት አራተኛ) ድጋፍ ድምፅ ነው።

የማህበሩ እና የአባላት ኃላፊነት ሌላኛው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ ነው። በመሠረቱ ህጋዊ ሰውነት እና የማህበሩ ኃላፊነት ውስንነት የማይነጣጠሉ ሀሳቦች ናቸው (corporate existence and limited liability are inseparable):: ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር የሚለው ስም ሲታይ ኃላፊነቱ የተወሰነው የማህበሩ ቢመስልም ዝርዝሩ ሲታይ ኃላፊነቱ የተወሰነው የሽሪኮች መሆኑን ማየት ይቻላል። ምክንያቱም የሽሪኮች ኃላፊነት በመዋጮዋቸው የተወሰነ ነው። በእርግጥ የማህበሩ ኃላፊነትም ቢሆን በግልፅ አልተጠቀሰም እንጂ የኃላፊነቱ መጠን በማህበሩ ሀብት /capital/ ልክ ነው። ሥራ አስኪያጅ ወይም ሽሪክ ከመዋጮ ባለፈ ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ አለ። ሥራ አስኪያጁ ከሥልጣኑ በላይ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ኃላፊነቱ የማህበሩ ሳይሆን የሥራ አስኪያጁ ብቻ ነው። በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 228 እንደሚደነግገው ሽሪኩ ወይም ሠራተኛው የማህበሩን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት ሆን ብሎ ወይም የማታለል ተግባር በመፈፀም ወይም በቸልተኝነት ለሚፈፅመው ጥፋት ወይም ለሚያደርሰው ጉዳት ጥፋቱን ካደረሰው ሽሪክ ወይም ሠራተኛ ጋር ማኅበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል። ማህበሩ ጉዳት የደረሰበት አካል ጉዳት አድራሹ ሥልጣን ያልተሠጠው መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከኃላፊነት ነፃ ይሆናል። ማህበሩ ይህን መሰል ዕዳዎች ለመሸፈን የመድን ሽፋን እንዲኖረው በህግ ይገደዳል።

6. የማህበሩ ሽሪክ ከማህበሩ የሚወጣበት መንገድ

አንድ ሽሪክ ከማህበሩ ሊወጣ የሚችለው የሶስት ወር ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት (ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ)፣ ሲሞት ወይም ህጋዊ ሰውነት ሲያጣ፣ ድርሻው በገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ ሲወሰድ፣ በፍርድ ሲሸጥበት ወይም በሽሪኩ ላይ የኪሳራ ውሳኔ ሲወሰንበት፣ የሞያ ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም ለረጅም ጊዜ ሲታገድ፣ በሕመም ወይም አካል ጉድለት ወይም ሌሎች ምክንያቶች ግዴታውን ለመወጣት የማያስችለው ሲሆን ወይም ፍርድ ቤት በበቂ ምክንያት ከማህበሩ እንዲወጣ ሲወስን መሆኑ በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 229 ላይ ሰፍሮ ይገኛል። አንድ ሽሪክ ከማህበሩ ከመውጣቱ በፊት ለሶስተኛ ወገኖች የነበረበት ዕዳ ኃላፊነት ከማህበሩ በመውጣቱ ቀሪ አይሆንም። አንድ ሽሪክ ድርሻውን በሌሎች ማህበርተኞች ተቀባይነት ላገኘ ሌላ ማህበርተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሳያስተላልፍ የወጣ እንደሆነ ህጋዊ መብት ያለው ወራሽ ወይም ባለመብት ድርሻው ተሰልቶ እንዲሰጠው ከመጠየቅ ውጪ አባል ለመሆን የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም።

7. ስለማህበሩ መፍረስ እና የማፍረሻ ምክንያቶች

አንድ የንግድ ማኅበር በመመስረቱ ህልውና ያለው ሆኖ ከቆየ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል። ማኅበሩ ፈረሰ የሚባለዉም መኖር ሲያቆም (ህልውናውን ሲያጣ) ነዉ። ማኅበሩ የሚፈርሰው ግን በአንድ

ጀንበር አይደለም። አፈራረሱ ራሱን የቻለ ሂደት እና ሥነ-ሥርዓት አለው። የማፍረስ ሂደት ማጣራት ይባላል። የንግድ ማኅበር የሚፈርሰው የማጣራቱ ሂደት ሲያበቃ ነው። የንግድ ማኅበር የሚቋቋመው በህግ እንደመሆኑ ሁሉ የሚፈርሰዉም በህግ በተቀመጠ ሥነ-ሥርዓት (ሂደት) ነው።

በንግድ ሕግ አንቀጽ 181 ንግድ ማህበራት ከሚፈርሱበት ሁኔታ በተጨማሪ የሸሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ያለ እንደሆነ እና በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሌላ ሽሪክ መተካት ሳይቻል ሲቀር ማኅበሩ እንዲፈርስና ሒሳቡ እንዲጣራ መደረግ አለበት። የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ ከማለፋ በፊት በማኅበሩ የቀረዉ ሽሪክ ጥያቄ ሲቀርብና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የንግድ መዝጋቢው አካል የስድስት ወራቱ የጊዜ ገደብ በሦስት ወራት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል። በዚህ መሰረት ካልሆነ በስተቀር የሼሪኮች ቁጥር ከሁለት በታች መቀነሱን የሚያውቅ ሽሪክ ማኅበሩ በዚህ ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ሥራውን እንዲቀጥል ካደረገ የማኅበሩ ዕዳና ግዴታዎች ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል።

**ሆልዲንግ ካምፓኒ በአዲሱ የንግድ ህግ**

*መግቢያ*

እስከቅርብ ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የሀገራችን የንግድ ህግ (ኮድ) አዋጅ ቁጥር 166/1952 ስድስት መጽሐፍት የነበሩት ሲሆን ስለነጋዴዎችና ስለንግድ መደብሮች፣ ስለ ንግድ ማህበሮች፣ ስለማጓጓዝ ስራና ስለ ኢንሹራንስ፣ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና የባንክ ስራዎች፣ የኪሳራና መጠበቂያ ስምምነት እና መሻገሪያ ህግን ያካተተ ነበር። አዲሱ የንግድ ህግ/ኮድ በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 ሆኖ ሚያዝያ 4 ቀን 2013 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ስራ ላይ ውሏል። ይህ የንግድ ህግ በይዘቱ በሶስት መጽሐፍት የተከፋፈለ ሲሆን እነዚህም መጽሐፍ አንድ ስለነጋዴዎች፣ የንግድ ስራዎችና ስለ ንግድ መደብሮች፣ መጽሐፍ ሁለት ስለ ንግድ ማህበራት፣ እና መጽሐፍ ሶስት ስለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር፣ መልሶ የማደራጀት እና የመክሰር ህግ ናቸው።

በኩባንያዎች መካከል የሚፈጠረው ዝምድና አንዱ ኩባንያ በሌላው ኩባንያ ከፍያለ የአክሲዮን ድርሻ በሚኖረው ጊዜ ወይም አንድ ባለሀብት በተለያዩ ኩባንያዎች ትልልቅ የአክሲዮን ድርሻ በሚኖረው ጊዜ የሚፈጠር ነው። ይህም የኩባንያዎች ቡድን የሚፈጥር እና ግንኙነቱም የእናት እና የተቀጥላ ኩባንያ ወይም የእህት ኩባንያ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህን መሰል ግንኙነት በተለይም ከፍያለ የአክሲዮን ድርሻ የሚይዝ ሆልዲንግ ኩባንያ በተመለከተ በዚህ ፅሁፍ ለማብራራት ተሞክሯል።

ትርጓሜዎች

በንግድ ህጉ የተሰጡ ትርጓሜዎች መሰረት የንግድ ማህበራት ቡድን ማለት የእናት ኩባንያ እና ተቃራኒ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የተመዘገቡ የሁሉም ተቀጥላዎች ማህበራት ስብስብ ነው። ሆልዲንግ ካምፓኒ ማለት ደግሞ በቀጥታ ራሱ ምርትና አገልግሎት ባያቀርብም በዚህ ተግባር በተሰማሩ ሌሎች የንግድ ማህበራት ውስጥ መዋእለ ንዋይ በማፍሰስ ድርሻ የሚይዝ ኩባንያ ማለት እንደሆነ በንግድ ህጉ አንቀፅ 9 ተመልክቷል።

በሌላ በኩል እናት ኩባንያ ማለት በቀጥታም ሆነ በሌላ ኩባንያ አማካኝነት በተዘዋዋሪ ሌላ ኩባንያን በቁጥጥር ስር ያደረገ ኩባንያ እንደሆነ በህጉ አንቀፅ 550 ደንግጓል። ተቀጥላ የንግድ ማህበር ማለት ደግሞ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በሌላ ኩባንያ አማካኝነት በእናት ኩባንያ ቁጥጥር ስር የወደቀ ኩባንያ ነው። ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የተያዘ ኩባንያ ማለት ኩባንያው እና ከእናት ኩባንያው ሌላ ተቀጥላ ኩባንያ ወይም በእናት ኩባንያው ስም ከሚሰሩ ሰዎች ወይም በእናት ኩባንያው ተቀጥላዎች ስም ከሚሰሩ ሰዎች በስተቀር ሌላ የውጭ ባለአክሲዮኖች የሌሉበት ኩባንያ ማለት እንደሆነ በአንቀፅ 551 ላይ ተገልፆል።

በህጉ አንቀፅ 552 መሰረት ቁጥጥር አለ የሚባለው እናት ኩባንያው ብቻውን ወይም ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ጋር በመሆን የተቀጥላ ኩባንያውን የፋይናንስ እና የአሰራር ፖሊሲዎችን የመንደፍ እና የመምራት ስልጣን ሲኖረው ወይም ከግማሽ በላይ የሆነውን ድምፅ የመስጠት መብት ካለው ነው። ቁጥጥር የሚኖረው ወይም ሆልዲንግ ኩባንያ ግንኙነት አለ የሚባለው በሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አክሲዮን ማህበር ኩባንያዎች በተመለከተ መሆኑ ሌላው ልብ የሚባል ጉደይ ነው።

የሆልዲን ኩባንያ ጥቅሞች

የንግድ ማህበራት ቡድን በመፍጠር ወይም የእናት እና ተቀጥላ የንግድ ማህበር ግንኙነት በመመስረት የአደረጃጀት እና የአስተዳደር ውጤታማነትን ለማምጣት እና ስጋት (risk) ለመቀነስ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል። ከዚህ አንፃር የንግድ እንቅስቃሴው በጣም ሰፊና በርካታ የማይገናኙ ዘርፎች ያሉት ሲሆን አደረጃጀቶችን በመፍጠር ሊደራጅ ይችላል። ለምሳሌ አንድ ስኳር ፋብሪካ የአገዳ ማምረት እርሻ ስራውን በአንድ ንግድ ማህበር፣ የፋብሪካ ምርት ሂደቱን በሌላ ኩባንያ፣ የሽያጭ ስርጭት ስራውን በሌላ ኩባንያ አድርጎ አደረጃጀቶችን በንግደ ማህበራት በመፍጠር ውጤታማነቱን በየሙያውና በየዘርፉ ከፋፍሎ ሊሰራ ይችላል። ከአስተዳደርም አንፃር እነዚህን ሁሉ ሰፊ የንግድ ተግባራት በአንድ ንግድ ማህበር ለመስራት በመሞከር የአስተዳደር ችግር ውስጥ ከመግባት ስራዎቹን በዘርፍ ከፋፍሎ አስተዳደሩን በማቃለል

ውጤታማነቱን ለማሳደግ ሊመርጥ ይችላል። በተጨማሪም ከግዙፍ ድርጅቶች አንፃር በርካታ የንግድ ዘርፍ ስራዎችን በአንድ ላይ ሲከወን በአንዱ ዘርፍ የሚኖር ኪሳራ ወደ ሌላው ዘርፍ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅእኖ ለመገደብ ንግድ ስራዎቹን በዘርፍ ከፍሎ ማደራጀቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል አንድ ባለሀብት በተለያዩ የማይገናኙ የንግድ ዘርፎች ለምሳሌ በተሽከርካሪ መገጣጠም፣ በሆቴል፣ በሰሊጥ እርሻ ወዘተ ቢሳተፍ እነዚህን ተግባራት በተለያዩ የንግድ ማህበራት እያደራጀ እህት ኩባንያዎች ሊኖሩት ይችላሉ። ይህም ማለት የድርጅቶቹ ባለቤቶች ወይም ባለአክሲዮኖች ተመሳሳይ ሲሆኑ ድርጅቶቹ እህትማማች ይባላሉ። እዚህ ላይ የሚታየው የእህት አቻ ኩባንያ ግንኙነት እንጂ የእናት እና ተቀጥላ ንግድ ኩባንያ ግንኙነት አይታይም። ሆኖም እነዚህን እህት ኩባንያዎች አስተዳደር (የሚያስተዳድር) ወይም ደግሞ ካፒታላቸውን (አክሲዮናቸውን) በትልቅ ደረጃ (ድርሻ) የሚይዝ እናት ኩባንያ በመመስረት ሊያደራጅ ይችላል። እዚህ ላይ ልብ የሚባለው የእናት እና ተቀጥላ ኩባንያ ወይም የሆልዲንግ ኩባንያ አለ የሚባለው እናት የሚሆነው ግለሰብ ሳይሆን ድርጅት ወይም ኩባንያ መሆኑ እና ይህ ድርጅት የሌላ ድርጅት አክሲዮን ባለቤት ሲሆን እና ይህም የድርሻ መጠን በተቀጥላው ኩባንያ ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት (አመራርና ዳይሬክተሮች ለመሾም ወይም የፋይናንስ ውሳኔዎች ለመስጠት) የሚያስችለው ደረጃ ያለው ሲሆን ነው።

በዚህ መልኩ የሚኖር የንግድ ማህበራት መቧደን ወይም የሚደራጁ የእናት እና የተቀጥላ ኩባንያ ግንኙነት ወይም የንግድ ማህበር ግንኙነት በቀድሞው የንግድ ህግ ግልፅና ፈቃጅ ድንጋጌዎች አልነበሩትም። ሆኖም እንዲህ ያሉ አደረጃጀቶች ከሚኖራቸው የአደረጃጀት እና የአስተዳደር ውጤታማነትን ለማምጣት እና የንግድ ማህበራትን ስጋት (risk) ለመቀነስ ከሚኖረው ጠቀሜታ አንፃር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍትሀዊ የንግድ ውድድር፣ የህዝብን ወይም የሸማቾችን ጥቅም ለመጠበቅ፣ የሌሎች ባለአክሲዮኖችን መብት ለማስጠበቅ፣ የተቀጥላ ንግድ ማህበራቱን ህልውና ለመጠበቅ እና በሌሎች መሰል አላማዎች አዲሱ የተሻሻለው የንግድ ህጋችን ስርአትን አበጅቶ ፈቃጅ ሆኖ ተደንግጓል።

የማህበራቱ ግንኙነት የሚመራበት ስርአት

ይህን የመሰለ የንግድ ማህብራት ዝምድና እና ግንኙነት ባለበት ሁኔት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ማየት አስፈላጊ ይሆናል። የአንድ የንግድ ማህበር እና ከማህበሩ ጋር ቅርበት ባላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች መካከል የንግድ ውል ስምምነት የጥቅም ግጭትን ለማስቀረት በቅድሚያ በዳይሬክተሮች ቦርድ መፈቀድ ያለበት መሆኑን በንግድ ህጉ አንቀፅ 306 ተመልክቶ እናገኛለን። ይህም እናት ወይም ተቀጥላ የሆነ የንግድ ማህበር እንዲሁም እርስ በእርስ አክሲዮን የተገዛዙ ማህበራት መካከል የሚኖር ስምምነትን ይመለከታል። ከዚህ

በተጨማሪም በህጉ አንቀፅ 307 መሰረት አንድ ኩባንያ በጠቅላላ ጉባኤው ተፈቅዶ ካልሆነ በስተቀር ለሆልዲንግ ኩባንያ ብድር ዋስትና ለመስጠት አይፈቀድለትም።

ተቀጥላ ኩባንያ በእናት ኩባንያ ውስጥ ምንም አክሲዮን መያዝ አይችልም። በሌሎች ሁኔታዎችም ቢሆን አንድ የንግድ ማህበር በሌላ የንግድ ማህበር ውስጥ ከ5% ወይም በላይ አክሲዮን ድርሻ ካለው ለንግድ ሚኒስቴር የማሳወቅ ግዴታ እና ድርሻውን ከ5% በታች እስኪሆን ድረስ የመቀነስ ግዴታ እንዳለበት አንቀፅ 555 ይደነግጋል። በንግድ ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤትም የንግድ መዝገብ አክሲዮኖቹ በማን እንደተያዙ የሚያሳይ መረጃ መያዝ ግዴታ እንዳለበት አንቀፅ 313 ያመለክታል።

በህጉ አንቀፅ 556 እና 557 ላይ እንደተገለፀው እናት ኩባንያ ለተቀጥላ ኩባንያ በጠቅላላ ጉባኤ ወቅት አመራር ወይም ትእዛዝ ለመስጠት የሚችልና መረጃዎችን ለማግኘት መብት ይኖረዋል። የተቀጥላ ንግድ ማህበር ሂሳብ መግለጫ በሆልዲንግ የንግድ ማህበር አመታዊ ጉባኤ ወቅት እንዲቀርብ መደረግ እንዳለበት ህጉ ይጠብቃል፣ ይህም አንቀፅ 431 ስር ተገልፆል። የአንድ የንግድ ማህበር ሂሳብ በኦዲተር ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ወይም በንግድ ሚኒስቴር አጣሪዎች ቁጥጥር በሚደረግበት ጊዜ የተቀጥላ ማህበሩን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ካስፈለገ ኦዲት ለማድረግ እንደሚቻል ህጉ የሚፈቅድ መሆኑን አንቀፅ 353 እና 355 ያሳያሉ።

ከእዚህ ላይ ልብ ሊበል የሚገባው ሌላው ነጥብ እናት ኩባንያ በተቀጥላው ኩባንያ አነስተኛ ባለአክሲዮኖች ወይም ለተቀጥላው ኩባንያ ህልውና ወይም ለሌሎች ተወዳዳሪዎች እና ለመንግስት ከግብር ስወራ አንፃር የሚኖርበት ተጠያቂነት ነው። እናት ኩባንያው የመቆጣጠር መብቱን በመጠቀም በተቀጥላው እና በራሱ መካከል የሚኖር የንግድ ግንኙነትን ለራሱ ባልተገባ በሚጠቅም መልኩ እንዲሆን ወይም ተቀጥላው ድርጅት ምርቱን ከፍ ባለ ወይም ዝቅ ባለ ዋጋ እንዲሸጥ ወይም ጥሬ እቃዎችን እናት ኩባንያውን ያላግባብ ከሚጠቅም ድርጅት ከፍ ባለ ወይም ዝቅ ባለ ዋጋ እንዲገዛ የሚያደርግ እርምጃ ቢወስድ ሊኖርበት የሚችለው ተጠያቂነት ሊታይ የሚገባው ነው። እናት ኩባንያዎች ከዚህ አንፃር የንግድ ስነ ምግባር፣ የውድድር ህጎች እና ሌሎች የፍትሀብሔር ሀላፊነቶች አንፃር ያሉበትን ግዴታዎች ታሳቢ በማድረግ በጥንቀቄ ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል።

በአጠቃላይ ሲታይ አዲሱ የንግድ ህግ ከቀድሞው በተለየ መልኩ የሆልዲንግ ኩባንያ አደረጃጀትን እውቅና የሚሰጥ ነው። በሆልዲግ ኩባንያ አደረጃጀት መሰረት አንድ እናት ኩባንያ የውሳኔ ሰጪነት ሚና ያለው የአክሰዮን ድርሻ በተቀጥላ ኩባንያ ወይም ኩባንያዎች ውስጥ ሲይዝ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህም

አደረጃጀት ለውጤታማነት፣ ቅልጥፍና እና ስጋትን በተሻለ ለማስተዳደር ጥቅም ይሰጣል። የንግድ እንቅስቃሴዎቻችንም ዘመናዊ እንዲሆኑ እና በተግባር ያሉ የተለያዩ የንግድ አማራጮችን፣ የስራ ፈጠራን ለማካተት ያስችላል። እንዲህ ያሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችም በእናት ኩባንያዎች በጥንቃቄ ህግን ተከትለው ሊተገበሩ እና ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

## የዳይሬክተሮች እና የተቆጣጣሪ ቦርድ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት በአዲሱ የንግድ ሕግ

*መግቢያ*

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 1243/ 2013) የንግድ ማኅበራት ማለት ሰዎች መዋጮ አዋጥተው በኅብረት በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመሰማራት ከሚገኘው ትርፍ ተከፋይ ለመሆን በስምምነት የሚያቋቁሟቸዉ ማኅበራት እንደሆኑ ተደንግጓል። ሕጉ ሁለት የንግድ ማሕበራት በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲመሩ የፈቀደ ሲሆን እነሀም የአክሲዮን ማኅበር /Share Company/ እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር/ Praivate Limited Company/ ናቸው። የንግድ ማኅበር ዳይሬክተሮች ማኅበሩን ለማስተዳደር የሚያስችላቸዉ ሰፊ ሥልጣን አላቸዉ። ማኅበሩም ከዳይሬክተሮች ጥሩ አገልግሎት ማግኘት የሚችለዉ ዳይሬክተሮቹ በተናጠል ሲሰሩ ሳይሆን እዉቀታቸዉንና ጥረታቸዉን አንድ ላይ አስተባበረዉ ሲሰሩ ነዉ። በመሆኑም ዳይሬክተሮች ሥራቸዉን የሚያከናዉኑት እየተሰበሰቡ ወሳኔ በማሳለፍ ነዉ። በዚህ አጭር ጽሁፍ የዳይሬክተሮች ቦርድ ትርጉም፣ የዳይሬክተሮችና የተቆጣጣሪ ቦርድ አወቃቀር፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ግዴታ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሚሉትን እንመለከታለን።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ትርጉም

የንግድ ማኅበራት የተፈጥሮ ሰዎች ባይሆኑም ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ አካላት ናቸዉ። የንግድ ማኅበራት በራሳቸዉ ተግባሮችን ማከናወን ስለማይችሉ የማኅበሩን ሀሳብና ተግባር የሚያከናዉኑላቸዉ እና ንግዱን የሚመሩላቸዉ የተፈጥሮ ሰዎች ያስፈልጓቸዋል። እነዚህ ሰዎች የማኅበሩ የአስተዳደር የዳይሬክተሮች ቦርድ ይባላሉ። ይህ የተቆጣጣሪ ቦርድንም ይጨምራል። የማኅበሩ ዳይሬክተሮች ለማኅበሩ ስኬት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ማኅበሩ ጥሩ ካፒታልና ጥሩ ዓላማ ቢኖረዉም በጥሩ አስተዳደር ካልተመራ አጥጋቢ ዉጤት አያስገኝም።

የዳይሬክተሮችና የተቆጣጣሪ ቦርድ አወቃቀር

አዲሱ የንግድ ሕግ የዳይሬክተሮች ቦርድን በተመለከተ በአንቀጽ 296 የደነገገው ቀድሞ ከነበረው ዘርዝር ያለ ሲሆን፣ ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። የአክሲዮን ማኅበር በባለ አክስዮኖች የሚመረጡ ቁጥራቸው ከሦስት እስከ አስራ ሦስት በሚደርሱ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚተዳደር መሆኑ (የዳይሬክተሮች ቦርድ አባለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ)፣ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ 2/3 ኛ በማኅበሩ የዕለት ተዕለት ሥራ አመራር ወስጥ የሥራ አስፈፃሚነት / Executive/ ሚና የሌላቸዉ መሆኑ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርም በአስገዳጅነት ባይሆንም በፈቃዱ ከሦስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት ያሉት ቦርድ ሊኖረው እንደ ሚችል በሕጉ 513 ስር ተደንግጎ ይገኛል ። እንዲሁም በአንቀጽ 331 መሰረት የአክሲዮን ማኅበር በአስገዳጅነት ሳይሆን በፈቃዱ ቁጥራቸው ከከሦስት እስከ አምስት የሆነ ባለአክሲዮን የሆኑ ሰዎችን ብቻ የሚይዝ ተቆጣጣሪ ቦርድ ሊኖረው ይችላል። የዚህ ቦርድ ዓላማ ስሙ እንደሚያመለክተው በማኅበሩ ላይም ሆነ በሥራ አመራሩ ላይ ቁጥጥር ማድረግና እርምጃ እንዲወስድ ለማኅበሩ ጠቅላ ጉባዔ ማቅረብ ወይም የሚታረም ከሆነ ለቦርዱ ሀሳብ ማቅረብ ብቻ ነው። ከቀድሞው ሕግ በተለየ ቁጥራቸውን ከ 1/3 ያልበለጡ ባለአክሲዮኖች ያልሆኑ ሰዎች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ። ይህም ማኅበሩ የልዩ ዕውቀት ባለቤት የሆኑ የማኅበሩ አባል ያልሆኑ ሰዎችን በሥራ አመራሩ ለማሳተፍ ያስችለዋል።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ግዴታ

የንግድ ማኅበር ዳይሬክተሮች ማኅበሩን ወክለዉ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር እና የመምራት ስልጣን አላቸዉ። ይህንን ሥልጣናቸዉን በመጠቀም የንግድ ማኅበሩ እንዲያከናዉን የተፈቀደለትን ተግባር ይፈጽማሉ። ሥልጣናቸዉ መጠን እና ዝርዝር የሚገለጸዉ፡- በህግ፣ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና በባለአክስዮኖች ጉባዔ በሚተላለፉ ዉሳኔዎች (ቃለ-ጉባዔዎች) ነዉ።

በንግድ ሕግ አንቀጽ 315 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም ጠቅላላ ጉባዔ የተሰጡትን ውሳኔዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን የማኅበሩን ፋይናስ በአግባቡ ማስተዳደር፣ ማኅበሩን ለአደጋ ተጋላጭ እንዳይሆን ተገቢውን አሠራር መዘርጋት፣ የማኅበሩ አስፈላጊ የሆኑ የሒሳብና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ማስተዳደርና እንዲያዙ ማድረግ፣ የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ማዘጋጀትና መጥራት ማኅበሩ 3/4 ካፒታሉን ሲያጣ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት እና ማኅበሩ እዳውን የመክፈል አቅሙ ሲቀንስ መልሶ የማደራጀት ሥራ ወይም የኪሳራ ሥነ ሥርዓት እንዲጀምር የማድረግ ተግባርና ግዴታ አለባቸው። ለማኅበሩ ተገቢ ስትራቴጂካዊ የሆነ አመራር በመስጠት ኩባንያውን ውጤታማና አቅም ያለው

ማድረግ የቦርዱ ዋና ኃላፊነት ነው። የዳይሬክተሮች ቦርድ በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሁፍና ሕግ መሠረት በአንድነት ሥራቸውን የሚያካሄዱና የማኅበሩ እንደራሴ ሆነው በማኅበሩ ስም የማኅበሩን ጉዳይ የመፈጸም መብት አለባቸው።

የቦርድ አባላት ለማኅበሩ የመታመን ግዴታ (Duty of Loyalty) ያለባቸው ሲሆን ማኅበሩን የበለጠ ስኬታማ ያደርጋል ብለው ያመኑበትን በቅን ልቦና መተግበር አለባቸው። ይህንን ተግባራዊ ሲያደርጉም የመላው ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩና የማኅበሩን የረዥም ጊዜ ጥቅም፣ የሠራተኞች ጥቅም፣ የባለገንዘቦችን ጥቅም፣ ሥራውን በማኅበረሰቡና በአካባቢው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 316 ሥር ተመልክቷል። ይህ ድንጋጌ በርካታ ግዴታዎችን የያዘና የቦርድ ዳይሬክተሮች ኃላፊነት ምን ያህል የከበደ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው ኃላፊነቱ በሚወጣበት ጊዜ በነፃነትና በመሰለው (Independent Judgment) መንገድ መወሰን አለበት። የመወሰን ነፃነቱን ግን አስቀድሞ በመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም ከኩባያው ጋር በተገባ ስምምነት የተወሰነ ከሆነ ግን ገደቡ የተጠበቀ እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 317 (2) ተመልክቷል። ዳይሬክተሩ በነፃነትና ይወስናል ማለት ግን የማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ፣ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ወይም ሕግ በመጣስ ይወስናል ማለት አይደለም። በነፃነትና በመሰለው የሚወሰነው በሕጉ ወይም በማኅበሩ ሕገ ደንብ ማዕቀፍ ሆኖ ፍቅደ ሥልጣኑን (Discretion) በሚጠቀምበት ጊዜ ነው።

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው ሌላው ግዴታ ኃላፊነቱን በጥንቃቄ በብልህነትና በትጋት (Duty to Exercise Reasonable Skill, Care and Diligence) መወጣት እንደሆነ በንግድ ሕጉ በአንቀጽ 318 ላይ ተመልክቷል። ጥንቃቄ፣ ትጋት ወይም ብልህነት እንዴት ይለካል የሚለው አከራካሪ ቢሆንም የንግድ ሕግ፣ ኃላፊነቱ በምክንያታዊ ደረጃ ትጉህ የሆነ የቦርድ አባል ሊኖረው ከሚገባው ጠቅላላ ዕውቀት ብልኃትና ጥንቃቄ አንፃር የሚለካ እንደሆነ ይገልጻል። ይህም አንፃራዊ (Subjective Standard) መለኪያ ነው።

ሌላው በቦርድ አባላት ላይ የተጣለው ግዴታ የጥቅም ግጭትን የማራቅ (Duty to Avoid Conflict of Interest) ነው። ማኅበሩ ሊጠቀምባቸው ቢችልም ባይችልም ዳይሬክተሩ የማኅበሩን ንብረት፣መረጃ ወይም የንግድ ዕድል ለግል ጥቅሙ እና ለሌላ ሰው ማዋል እንደማይችል በአንቀጽ 320 (1) (2) ሥር ተደንግጓል። የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ግን ክልከላውን በማንሳት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል። በቦርድ አባሉና በማኅበሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ካለ ወይም ሊደረግ

የታሰበው ወይም የተደረገ ውል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቦርድ አባሉን ጥቅም ጋር የሚገናኝ ከሆነ ሁኔታውን በዝርዝር ለተቀሩት ዳይሬክተሮች በተሟላ መልኩ ሊገለጽላቸው ይገባል።

በማኅበሩና ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት በቅድሚያ በቦርዱ መፈቀድ እንዳለበት የጥቅም ግጭት ያለበት የቦርድ አባልም ድምፅ መስጠት እንደማይችል በአንቀጽ 306 ሥር ተመልክቷል።

ዳይሬክተሮችን የሚመለከት ብድር ወይም ዋስትና በቅድሚያ በጠቅላላ ጉባዔ መፈቀድ ይገባዋል። ዳይሬክተሮችን ይህንን የማክበር ግዴታ አለባቸው። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር በራሳቸው ወይም በሦስተኛ ወገኖች ስም ከማኅበሩ ጋር መወዳደር ወይም ተወዳዳሪ የሆኑ የንግድ ማኅበራት ውስጥ አባል መሆን እንደማይችሉ በንግድ ሕግ ቁጥር 319 ሥር ግዴታ ተጥሎባቸዋል።

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው ያለ ቦርዱ ፈቃድ ከሦስተኛ ወገን ስጦታም ሆነ ሌላ ዓይነት ጥቅም መቀበል እንደማይችል በንግድ ሕግ ቁጥር 322 ላይ ተደንግጓል። ዳይሬክተሮች ማኅበሩን በሥራው ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ እንዳለባቸውና ዕዳውን መክፈል እንደማይችሉ እያወቁ ሥራውን መቀጠል (Reckless Trading) እንደሌለባቸው በንግድ ሕጉ ተመልክቷል።

በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና ቃለ ጉባዔ ለዳይሬክተሮች የሚሰጠዉ የተግባር ግዴታ እንዳለ ሆኖ በህግ ከተሰጣቸዉ ግዴታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ።

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ ፣ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ዉሳኔ የሚሰጥ ሥልጣን ይኖረዋል።

2. የማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነት ሥራቸዉን የሚያካሂዱና ለማኅበሩ እንደራሴ መሆናቸዉን ወይም ከእነርሱ ዉስጥ አንዱ ለዚህ ተግባር በተለይ ስልጣን ያለዉ መሆኑን መለየት አለበት።

3. ለማኅበሩ እንደራሴ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸዉ ዳይሬክተሮች በማኅበሩ ስም የማኅበሩን ጉዳይ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ሥራዎች ሁሉ በእንደራሴነት የመሰራት መብት አላቸዉ በማለት አዲሱ የንግድ ሕግ በአንቀጽ 324 ላይ አስፍሯል።

የአክስዮን ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ እነዚህ የተሰጡትን ሥልጣኖች መሰረት በማድረግ ዉሳኔዎችን የሚያስተላልፈዉ በቦርድ ስብሰባዎች ነዉ።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የአክሰዮን አባል ቢሆኑም ባይሆኑም በአስተዳዳሪነት ሥራቸዉ ለሚያደርሱት ጥፋት ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለባቸዉ ሲሆን እነዚህም የፍትሐብሔር ኃላፊነት እና የወንጀል ተጠያቂነት ናቸዉ። የወንጀል ተጠያቂነት ማለትም በወንጀል ተከሶ የገንዘብ ቅጣትና እስር ሊወሰንባቸዉ ይችላል።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግና በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሁፍ ውስጥ የተመለከቱ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ወይም ከጣሱ በኃላፊነት ይጠየቃሉ።

ለማኅበሩ ያለባቸዉ ኃላፊነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በህግ፣በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔ ዉሳኔዎች የተሰጠቸዉን የአስተዳደር የሥልጣን ወሰን ሳያልፉ ተግባሮቻቸዉን በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸዉ።በቅን ልቦና( ህሊና) እና በጥንቃቄ ባለመስራታቸዉ በማኅበሩ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ካደረጉ ለደረሰዉ ጉዳት ማኅበሩን ለመካስ በአንድነት ኃላፊዎች ይሆናሉ። ይህም በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 325 ተድግጎ ይገኛል። የቦርድ አካላት በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት ስለማስረዳታቸው የማስረዳት ሸክም አለባቸው። ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ላይ ክስ ማቅረብ የሚችለው ግን የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን ብቻ ነው። የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ወስኖ ማኅበሩ ክስ ያልመሠረተ እንደሆነ የማኅበሩን ካፒታል አሥር በመቶ የያዙ ባለአክሲዮኖች በማኅበሩ ስም በዳይሬክሮች ላይ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው። ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ላይ የሚያቀርበዉን ክስ ለመተዉ ወይም በግልግል ለመጨረስ ይችላል። ሆኖም ክሱን ለመተዉና በግልግል ለመጨረስ የሚቻለዉ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አሥር በመቶ ድርሻ ያላቸዉ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዉ ክስ ለመተዉ ወይም በግልግል ለመጨረስ የሰጠዉን ዉሳኔ ያልተቃወሙት እንደሆነ ነዉ በማለት በሕጉ አንቀጽ 328 ተደንግጓል።

ለባለአክስዮኖች ያለባቸዉ ኃላፊነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በፈጸሙት ጥፋት የተነሳ በአንድ /በተወሰኑ ባለአክስዮኖች ላይ በቀጥታ ጉዳት ካደረሱ ጉዳቱን ለደረሰበት (ለደረሰባቸዉ) ባለአክስዮኖች ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል። በኢትዮጵያ የንግድ ህግ ይህ መብት ለባለአክስዮኖች የተሰጠዉ በቁጥር 355 ነዉ። ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አሥር በመቶ ድርሻ ባላቸዉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ በሚደረግ ምርመራ የሚደረግ ነዉ። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥፋት

ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ባለአክስዮን በዳይሬክተሮች ላይ በቀጥታ ክስ ለማቅረብ በጠቅላላ ጉባዔ ካልተፈቀደለት በአማራጩ የንግድ ማኅበሩን የመክሰስ መብት ይኖረዋል።

ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች (ሦስተኛ ወገኖች) ያለባቸዉ ኃላፊነት

ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ተጠያቂነት ያለባቸዉ ሲሆን ዳይሬክተሮች የማኅበሩ ገንዘብ በሙሉ እንዲጠበቅ የማድረግ ግዴታቸዉን በጥንቃቄ መወጣት አለባቸዉ። ይህንን አስተዳደራዊ ጥንቃቄ በሚገባ ባለማድረጋቸዉ የተነሳ ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች ከማኅበሩ ላይ የሚጠይቁትን ገንዘብ ሳያገኙ ቢቀሩ (ለምሳሌ በማኅበሩ አንቀጾች እንዲቀመጥ የታዘዘዉን መጠባበቂያ ገንዘብ በአግባቡ እንዲቀመጥ ሳያደርጉ ቢቀሩ) ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች በኃላፊነት ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

ሦስተኛ ወገኖች ከማኅበሩ የሚጠይቁትን ገንዘብ ከማኅበሩ ንብረት ላይ ነዉ የሚወስዱት ። ነገርግን የማኅበሩ ንብረት የማኅበሩን ዕዳ ለመሸፈን ካልበቃ እና ላለመብቃቱ የዳይሬክተሮች ጥፋት ካለበት ገንዘብ ጠያቂዉ በዳይሬክተሮች አባላት ላይ በግል ክስ የማቅረብ መብት አላቸዉ። ዳይሬክተሮችን በግል ከሚያስጠይቁ ጉዳዮች መካከል ለማኅበሩ ጉዳይ በራሳቸዉ ስም ተዋዉሎ መገኘት፣ማኅበሩ ከሰጣቸዉ ሥልጣን ዉጪ በማኅበሩ ስም ቢሆንም ተግባሮችን ፈጽሞ መገኘት እና ለ 3 ኛ ወገኖች የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ መግለጫ (ማስረጃ) መስጠት የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ላይ የሚያቀርበዉን ክስ ለመተዉ ቢወስን ከማኅበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች በዳይሬክተሮች ላይ ክስ ለማቅረብ ያላቸዉን መብት አያስቀርም።( አዲሱ የንግድ ሕግ 329 ይመለከቷል)።

የዳይሬክቶች ቦርድ አባላት የወንጀል ተጠያቂነት

የንግድ ማኅበር ዳይሬክተሮች የተሰጣቸዉን ኃላፊነት በአግባቡ ሳይወጡ ሲቀሩ ወይም የማኅበሩን ጥቅም በሚፃረር እና በሚጎዳ ሁኔታ ቢሰሩ ከሚኖርባቸዉ ፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት በተጨማሪ የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል። ሥራዉን እንዲመራ በሕግ ወይም በዉል ግዴታ የተቀበለ ሰዉ (የንግድ ማኅበር አስተዳዳሪ) በተሰጠዉ ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል ወይም የተጣለበትን ግዴታ ባለመፈጸም በሚጠብቀዉ (በሚያስተዳድረዉ) የንብረት ጥቅም ላይ ወይም በድርጅት አገልግሎት ላይ አስቦ ጉዳት ካደረሰ እንደነገሩ ክብደት በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 702 ስር ተደንግጎ ይገኛል። አስተዳዳሪዉ ጥፋቱን የፈፀመዉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ከሆነ በመቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል። አስተዳዳሪዉ ጥፋቱን የፈፀመዉ የንብረት ጥቅም ለራሱ ወይም

ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስቦ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ቀላል እስራት ሆኖ ከብር ከብር ሰላሳ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ በተጨማሪ ይወሰንበታል፡፡ እንደሁኔታዉ የቅጣቱ መጠን ከዚህም ከፍ ሊል እንደሚችል በወንጀል ሕግ በዝርዝር ተገልጧል፡፡ ጥፋቱ ከወንጀል ሕጉ በተጨማሪ ከነገሩ ጋር አግባብነት ባላቸዉ ሌሎች አዋጆችም ሊታይ ይችላል፡፡

በማኅበሩ ውስጥ የማታለል ድርጊት ተፈጽሞ ከሆነ የተወሰኑ ባለአክሲዮኖችን መብት የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞ ከሆነ ሕገወጥ የሆነ ወይም የማታለል ድርጊት ያለበት አሠራር በማኅበሩ ውስጥ ያለ እንደሆነ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ ከሆነ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ወይም ሌላ ሥልጣን ያለው አካል ምርመራ ሊያደርግና የአስተዳደር ወይም የወንጀል ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግም በሕግ ወይም በውል ሥራ እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ኃላፊነቱን ሳይወጣ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ 50,000 ብር በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ አዲሱ የንግድ ሕግ ውስጥ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት በእጅጉ የገዘፈና ኃላፊነቱም የግል ሀብትና ንብረት ድረስ የሚመጣ፣ ለእስራት የሚዳርግ ስለሆነ ኃላፊነቱን የሚወስዱ ሰዎች ዝርዝር ጉዳዩን አውቀው ወደ ሥራው እንዲገቡ እናስገነዝባለን፡፡

**የንግድ ሥራ የመስራት መብት**

---------------------------

1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ዉስጥ ግለሰብ ነጋዴዎችም ሆኑ የንግድ ማኅበራት ማንኛዉንም የንግድ ሥራ ለማካሄድ ተመዝግበዉና የንግድ ሥራ ፈቃድ ወስደዉ መሆን እንዳለበት በህግ ተደንጓል (አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓ.ም ከነ ማሻሻያ አዋጁ 1150/2011 ዓ.ም)፡፡ በተጨማሪም የንግድ ስም ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ሌሎች የንግድ የንግድ ሥራ ለመስራት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ተሟልተዉ መሆን አለበት፡፡ ይህ አጭር ጽሁፍ የንግድ ሥራ የመስራት መብት በመያየዝ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለማስጨበጥ የሚሞከርበት ሲሆን እነርሱም የንግድ ሥራ በጠቅላላዉ፤ የንግድ ሥራ ምንነት፣የንግድ ሥራ የመስራት መብት ከህገ መንግስቱ እና ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር፣የንግድ ሥራን የመስራት ነፃነትና መብት እና መሰረታዊ የንግድ ሥነ-ምግባር መርሆች ላይ ይሆናሉ፡፡

2. የንግድ ሥራ በጠቅላላዉ

ግለሰብ ወይም ግለሰቦች በተናጠልም ሆነ በመደራጀት ኑሮን ለማሸነፍ፣ ሀብት ለማካበት፣ ለመበልጸግና ደስተኛ ሆኖ ለመኖር የተለያዩ የንግድ ድርጅቶችን በማቋቋም የንግድ ሥራ ይሰራሉ። ስኬታማ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የንግድ ሥራ በመጀመሩ ብቻ ሳይሆን የተፈጠረዉ ስራ የሚገዛበትን፣ የሚመራበትን መሠረታዊ የሆኑ የንግድ መስፈርቶች / Elements / የንግድ ህግንና የንግድ ሥነ-ምግባርን ማወቅ ወይም መረዳት ሲቻል ነዉ። የንግድ ሥራ ከሀገሮች ዕድገት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነዉ። የትስስሩ ሰንሰለት የሚጀምረዉ በግለሰብ ደረጃ ንግድን ከማካሄድ ሲሆን በተደራጀ መልክ እስከ ማስኬድ ድረስ ነዉ። ይህ አሁን ላሉት በግለሰብ ብቻ ሳይሆን በንግድ ማኅበራትና ኩባንያዎችን ለመስራትም መሠረት ነዉ። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አዲሱ የንግድ ህግ ዉስጥ በርከት ያሉ ስራዎችን በማቀፍና ካፒታል በማሰባሰብ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በባለአክስዮኖች በሚመሰረቱ የንግድ ማኅበራት የወደደዉና የፈቀደዉን የንግድ ሥራ የመስራት መብት አለዉ። ማንኛዉም ሰዉ ግለሰብ ወይም ድርጅት (ማኅበር) በህግ ካልተከለከለ ወይም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ሥራ በስተቀር የመረጠዉን ሕጋዊ የሆነዉን ማንኛዉንም የንግድ ሥራ የመስራት መብት አለዉ። አዲሱ የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀጽ 22 ላይ በተገለፀዉ መሰረት ሀሳቡን ያጠናክረዋል።

3. የንግድ ሥራ ምንነት

ንግድ ማለት ትርፍ ለማግኘት ሲባል የሚንቀሳቀሱም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ነገሮችን አምርቶ ወይም ገዝቶ የመሸጥና የመለወጥ ሂደት ነዉ። የተለያዩ የቴክኒካል አገልገሎቶችን እና ሙያዊ አገልግሎቶችን ለአገልግሎት ፈላጊዎች የመስጠት ሂደትንም ይጨምራል። ይሁን እንጂ ማንኛዉም ግዥና ሽያጭ ንግድ አይደለም። የንግድ ስራ ተከናዉኗል ለማለት ሽያጭ እና ግዢዉ በቋሚነት እና በድግግሞሽ የሚከናወን መሆን አለበት። ከዚህ ላይ ንግድ እና ነጋዴ ሚለዉን ማየቱ ተገቢ ነዉ። ንግድ ማለት የሰዉ ልጅ ፍላጎትና ምኞትን ለማሟላት፣የኑሮ ደረጃዉን ከፍ ለማድረግና ከንግድ እንቅስቀሴዉም ትርፍ ለማግኘት፣ ምርት ለማቅረብና አገልግሎት ለመስጠት የሚደረግ ማንኛዉም እንቅስቃሴ ነዉ። ከዚህ የምንረዳዉ የንግድ ሥራ ትርፍ ለማግኘት ሲባል የተለያዩ ምርቶችን ወይም ዕቃዎችን የመግዛትና የመሸጥ ወይም የተለያዩ የሙያ አገልግሎቶችን የመስጠት ሂደት መሆኑን ነዉ። በመሆኑም የንግድ ሥራ ማለት ነጋዴ የሚሰራዉ ማንኛዉንም ሥራ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓ.ም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ተደንግገ ይገኛል። ለንግድ ዓላማ እየተዘጋጁ የሚሸጡ ማናቸዉም ዕቀዎችም ሆኑ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለአገልግሎት ፈላጊዎች የሚሰጡ ቴክኒካዊ (ሙያዊ) አገልግሎቶች በሕግና በንግድ ሥነ-ምግባር መግዛት አለባቸዉ። ለዚህም ዋናዉ ነጋዴዉ ነዉ። የንግድ ምዝገባና ሥራ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ን ለማሻሻል ተደንግገ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1150/2011

ዓ.ም ነጋዴ ማለት ንግድን የሙያ ሥራዉ አድርጎ ተገቢ ጥቅም ለማግኘት በንግድ ህጉ እና በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ የተዘረዘሩትን ማንኛዉንም ስራዎች የሚሰራ የሚል ነዉ። በአዲሱ የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243 /2013 ዓ.ም አንቀጽ 5 ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሰራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ሥራ ነዉ ተብሎ በሕግ የተደነገገዉን ሥራ የሚሰራ ማንኛዉም ሰዉ ነዉ ተብሎ ተተርጉሟል። በአደጉ ሀገራት ያሉት የንግድ መህበረሰቦች ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን የመሸጥ ሥራን እንደ መሠረታዊ የንግድ እንቀስቀሴአቸዉ ያደርጉታል። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ 2001 ብቻ በአሜሪካ 10 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ያላቸዉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተሸጠዋል። በሌሎች ያደጉና በማደግ ላይ በሚገኙ የዓለማችን አገራትም ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንደዚሁ ይሸጣሉ።

4. የንግድ ሥራ የመስራት መብት ከህገ መንግስቱ እና ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር

ማንም ሰዉ ሥራ የመስራት፣ሥራዉን በነፃነት የመምረጥ፣በትክክለኛና በአመቺ የሥራ ሁኔታ ዉስጥ የመሥራትና ከሥራ አጥነት የመዳን መብት ያለዉ መሆኑን የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ (1948) አንቀጽ 23 (1) ላይ ተደንግጎ ይገኛል። በተጨማሪም የኢኮኖሚ፣የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (1966) በክፍል ሶስት አንቀጽ 6 የመሥራት መብት ማንኛዉም ሰዉ በነፃ ፈቃዱ የመረጠዉን ወይም የተቀበለዉን ሥራ ሰርቶ ሕይወቱን ለመምራት እንዲችል ዕድል መስጠትን ይጨምራል በማለት አስፍሯል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 41 ላይ ግልጽ በሆነ በማያሻማ ሁኔታ የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች በሚለዉ ስር፦

- ማንኛዉም ኢትጵያዊ በሀገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ስራ የመሥራት መብት አለዉ በሚል እና
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያዉን ሥራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ በማለት ተደንግጎ ይገኛል።

በመሆኑም የንግድ ሥራ እንደሌሎች ሥራዎች ሁሉ የንግድ ሥራ ለመስራት የፈለገ እና ለንግድ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በማሟላት ለሕግና ለሞራል የማይቃረኑ የንግድ ሥራዎች በመሰመራት የሚሰራ ሥራ መሆኑ በዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ህጎች መሰረት ያለዉ ነዉ።

5. የንግድ ሥራን የመስራት ነፃነትና መብት

በህግ ተለይተዉ የተከለከሉ ነገሮች ወይም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድርን የሚመለከቱ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛዉም ሰዉ ማንኛዉንም የንግድ ሥራ የመስራት ነፃነት እንዳለዉ በአዲሱ የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 21 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ይህ የተሰጠዉ ለሀገር ዉስጥ ነጋዴዎች ነዉ። በዉጭ ሀገር ስለተቋቋመ ወይም በዉጭ ሀገር ስለሚሰራ ማኅበርና ሀገር ዉስጥ ተመስርቶ በዉጭ ሀገር ስለሚቋቋም ቅርንጫፍ በአዲሱ ንግድ ሕግ አንቀጽ 579 ላይ የዉጭ ሀገር የግል ድርጅት፣ የንግድ ማኅበር ወይም ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ኢትዮጵያ ዉስጥ ቅርንጫፍ ከፍቶ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዉስጥ የመሳተፍ መብት አላቸዉ። ሆኖም መጀመሪያ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በሌላ አግባብ ያለዉ የባለስልጣን መስሪያቤት በሚያዘዉ የንግድ መዝገብ ዉስጥ መመዝገብ ያለበት መሆኑም ተገልጿል።

6. መሰረታዊ የንግድ ሥነ-ምግባር መርሆች

መርህ / Principle / ማለት የሰዎች ድርጊቶችን የሚገዛ ሰዎች የተለያዩ የንግድም ሆነ ማንኛዉም ድርጊቶች በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚመሩበትና ሚያከብሩት ደንብ ነዉ። ንግድ ሰፊና መሠረታዊ የወቅቱ የሰዉ ልጅ እንቅስቃሴ አካል፣ የኢኮኖሚ ዘርፍና የጎሊና ጉዳይም እየሆነ የመጣ እንቅስቃሴ በመሆኑ በንግድ ሥነ-ምግባር መገዛት አለበት። የንግድ ሥነ-ምግባር መርሆች የሚባሉት ፡-

1ኛ. ልዩነቶችን የማስወገድ መርህ፣

2ኛ. የደንበኞች ፍላጎትን የመጠበቅ መርህ፣

3ኛ. በንግድ እንቀስቃሴ ግልፅነትን የማበሰር መርህ፣

4ኛ. የምርቶች ደህንነትን የመጠበቅ መርህ

5ኛ. የአገልግሎት ደኅንነት መርህ፣

6ኛ. ሙስናን የማስወገድ መርህ

7ኛ. የዉጭ ኢንቨስተሮችን የመሳብ መርህ

8ኛ. አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የማብሰር መርህ

9ኛ. የአከባቢ ደኅንነት የመጠበቅ መርህ

10ኛ. አግባቢነት ያለዉ ንግድ ዉድድርን የማብሰር መርህ የሚሉት ናቸዉ።

በአጠቃላይ በህግ ያልተከለከሉና የተፈቀዱ የንግድ ሥራዎችን የሚሰራ ሰዉ ነጋዴ የሚባልና የነጋዴ መብቶች ያሉት ሲሆን ጎን ለጎን ደግሞ የነጋዴ ግዴታዎችንም ማክበር ይኖርበታል። ንግድ ሶስት ሰዎችን በቤተሰብነት አቅፎ ይዟል። እነዚህም የንግዱ ማኅበረሰብ፣ የንግዱ ተጠቃሚ ማኅበረሰብና መንግስት ናቸዉ። ስለዚህ የንግዱ

ማኅበረሰብ (ነጋዴዎች) ንግዳቸዉን ለማካሄድና ስኬታማ መሆን የሚችሉት የደንበኞችንና የመንግስት ፍላጎትና ጥቅምን ማክበር ሲችሉ ነዉ።

## በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ስለአክሲዮን ማህበር የተካከተቱ መሰረታዊ ነጥቦች

*መግቢያ*

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ መሆኑ ይታወቃል። ሻል ያለ ደረጃ ላይ የሚገኙት ጥቂቶችም ቢሆኑ ትርጉም ያለው ተቀማጭ ገንዘብ የላቸውም ሊባል ይችላል። በመሆኑም አገራችን ሥራ ላይ ሊውል (ኢንቨስት ሊደርግ) የሚችል ካፒታል ከፍተኛ እጥረት አለባት። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚገኝ አገር ውስጥ እድገት ለማምጣት ዜጎች በተናጠል ያላቸውን እጅግ ውስን ሀብት አስተባብሮ ወደ ሥራ ማስገባት የግድ ይላል። ይህ እንዲሳካ ደግሞ ዜጎች የቆጠቡትን ትንሽ ገንዘብ በንግድ ማኅበር ውስጥ ካስገቡ በኋላ ለምዝበራ እና ጭቆና እንዳይዳረጉ የሚከላከል ሕግ መኖር አለበት።

የ 1952 ቱ ንግድ ህግ በኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ይዘው የሚገቡትን ባለሃብቶች ከዘረፋ፣ ካልተገባ ጭቆና ወይም በደል ለመታደግ ያለሙ ድንጋጌዎች በበቂ ሁኔታ አላካተተም። በዚህም የተነሳ ኢኮኖሚው ያፈራውን አነስተኛ ካፒታል አሟጦ በተደራጀ መልክ ሥራ ላይ ማዋል አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። አልፎ ተርፎም ይህ ክፍተት አገሮች ለንግድ ምን ያህል አመቺ እንደሆኑ በሚለካው በዓለም ባንክ የሚደረግ ምዘና ኢትዮጵያ በየዓመቱ በጣም ዝቅተኛ ውጤት እንድታገኝ አድርጓል። በዚህም የተነሳ አገራችን የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በምታደርገው ጥረት ላይ ዕንቅፋት ሆኖ ቆይቷል።በመሆኑም አዲሱ የንግድ ህግ ከቀድሞው የንግድ ህግ በተሻለ ሁኔታ የማህበር አባላትን መብት በሚያስጠብቅ ሁኔታ የህግ ድንጋጌዎችን አካቶ በስራ ላይ ውሏል።

የአክሲዮን ማህበር በቀድሞው እና በአዲሱ የንግድ ህግ ከተካተቱ የንግድ ማህበራት አይነቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ማህበሩ የመጠሪያ ስም ኖሮት ከስሙ መጨረሻ ላይ "የአክሲዮን ማህበር" የሚል ሀረግ በመጨመር በንግድ መዝገብ እንደተመዘገቡ የሕግ ሰውነት እንደሚያገኝ በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀፅ 174፣175፤246 ተመልክቷል።በዚህ አጭር የንቃተ ህግ ፅሁፍ በአዲሱ የንግዱ ህግ ስለአክሲዮን ማህበር የተካተቱ አንዳንድ ነጥቦችን በወፍ በረር ለማየት ይሞከራል።

የአክሲዮን ማህበር ትርጉም

የአክሲዮን ማህበር ማለት ዋና ገንዘቡ ወይም ካፒታሉ አስቀድሞ ተወስኖ በአክሲዮን የተከፋፈለና ኃላፊነቱ በማህበሩ ሀብት ብቻ የተወሰነ ማህበር ሲሆን የአባላት ቁጥር ከአምስት ባለአክሲዮኖች በታች መሆን

የሌለበት የንግድ ማህበር አይነት ነው። የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት ለማህበሩ ቃል የገቡትን መዋጮ በመክፈል የተወሰነ ሆኖ በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የማህበሩ ዋና ገንዘብ ወይም ካፒታል ከሃምሳ ሺህ የኢትዮጵያ ብር ያነሰ ሊሆን እንደማይችል እና እያንዳንደ አክሲዮን ላይ የሚጻፈው ዋጋ ከአንድ መቶ ብር በታች ሊሆን እንደማይችል በንግድ ህጉ አንቀፅ 245/1/ እና 2 ስር ሰፍሯል።

የአክሲዮን ማህበር አባላት ሃላፊነት የተወሰነ ነው ማለት ማህበሩ ከሦስተኛ ወገኖች ማለትም ከአበዳሪዎች፣ከደንበኞቹ እና ከሠራተኞቹ ወ.ዘ.ተ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ጉዳት ቢደርስ የማህበሩ አባላት (ባለአክሲዮኖች) ሃላፊነት እስከ ምን ድረስ ነው? የሚለውን ይመለከታል። ይኸውም የማህበሩ አባላት ሃላፊነት ለማህበሩ ካፒታል ባዋጡት ወይም በሚያዋጡት መጠን ብቻ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ከንግድ ህጉ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል።:: ይህም ማለት አባላቱ ማህበሩ ሲመሠረት ወይም ከተመሰረተ በኋላ ለሽያጭ ከቀረበው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ በገዙት የአክሲዮን መጠን ብቻ ተጠያቂ የሚሆኑ ሲሆን አባሉ የሚጠበቅበትን መዋጮ ያልከፈለ እንደሆነ አክሲዮን ማህበሩ በእዳ ሲያዝ እንዲከፍል ይገደዳል። የአክሲዮን ማህበሩ ሃብት ጉዳቱን ለመካስ በቂ ሆኖ ባይገኝ ወደ ባለአክሲዮኖቹ ንብረት መሄድ አይቻልም ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአባላቱ የግል እዳ ከኩባንያው ሃብት አይከፈልም።

- የአክሲዮን ማህበር ጥቅም/ አስፈላጊነት

የአክሲዮን ማህበራት በሃገራችን መበራከት ሀገራዊ እና ግለሰባዊ ፋይዳ አለው። ሀገራዊ ፋይዳውን ስናይ አክሲዮን ማህበር ትልልቅና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁ የንግድ ዘርፎች(ለምሳሌ ባንክ፣መድን ድርጅት፣በግብርና ዘርፍ፣በቤቶች ግንባታ ወዘተ ) ላይ ለመሰማራት የሚረዳ የማህበር አይነት በመሆኑ የእነዚህ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች በሃገራችን መፈጠር ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ እያደረገች ያለውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ያግዛል። በሌላ በኩል የግለሰቦችን ስራ ፈጣሪነት ያበረታታል። ይህ ሲባል ግለሰቦች የሀገርን ኢኮኖሚ እድገት ሊያፋጥን የሚችል የንግድ ሃሳብ አመንጭተው ካፒታል ከህዝቡ በመሰብሰብ ለመስራት የሚያስችል በመሆኑ ሙያዊ ብቃታቸውን ተጠቅመው የሚሰሩ ስራ ፈጣሪዎች ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኙ የሚያበረታታ ሲሆን ለማህበሩ መፈጠር የደም ስር የሆነውን ካፒታል ያዋጡ ሰዎች ደግሞ ወደ ፊት ማህበሩ የሚያስገኘውን ትርፍ የድርሻቸውን በመውሰድ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ያስችላል።በአጠቃላይ አክሲዮን ማህበር ባለሀብቱን (capitalist) ከስራ ፈጣሪ (entrepreneur) ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው ።

- የአክሲዮን ማህበራት አቋቋም

የአክሲዮን ማህበራት በሁለት አይነት መንገድ ሊቋቋሙ ይችላሉ። እነዚህም፡-

1. ለህዝብ ክፍት የሆነ የአክስዮን ማህበር ፡- በአደራጅ አማካኝነት የሚቋቋም ሲሆን አደራጁ ለሕዝብ ክፍት የሆነ ማህበር ምስረታን ያነሳሳል፤ መግለጫ አዘጋጅቶ ሰዎች ማህበሩን እንዲቀላቀሉ ይጋብዛል ወይም በአጠቃላይ የማህበሩን ምስረታ ዓላማ አድርጎ ይህንኑ ለማስፈጸም በመንቀሳቀስ ማህበሩ የማይመሰረት ከሆነ ባለመመስረቱ ምክንያት ለሚመጣ ጉዳት ኃላፊነት ይወስዳል። የአክሲዮን ማህበራት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች ወይም ሕጋዊ ሰውነት ባላቸው ሰዎች ሊደራጁ የሚችል ሆኖ የአክሲዮን ማህበር አባላት ቁጥር ከአምስት ባለአክሲዮኖች በታች መሆን የለበትም።

አደራጆቹ ለህዝብ አክሲዮን በመሸጥ አክሲዮን ማህበራት ሲያቋቁሙ ሊከተሏቸው ወይም መፈፀም ያለባቸውን ድርጊቶች እና ሊያሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች በንግድ ህጉ አንቀጽ 249፣ 250 እና 251 ስር ተመልክቷል።በአጠቃላይ በዚህ አይነት መንገድ የሚቋቋም አክሲዮን የንግድ ሀሳቡ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ ከሆነ ገንዘቡን ትንሽ ሠዎችን በማሣመን መሰብሰብ ስለሚያስቸግር ለሕዝብ አክሲዮን በመሸጥ አክሲዮን ማህበሩን ማቋቋም ይችላሉ።

2. በመሥራቾች መካከል የሚደረግ መቋቋም

ይኸኛው የአክስዮን ማህበር አይነት ምስረታ የሚደረገው የተወሰኑ ሰዎች ለሕዝብ ጥሪ ሳያደርጉ የአክሲዮን ማህበር ምስረታን የተመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎችን በማሟላት በመካከላቸው የአክሲዮን ማህበር የሚያቋቁሙበት ነው።በተመሳሳይ በሌላ ህግ የተለየ ቁጥር ካልተወሰነ በስተቀር የአክሲዮን ማህበር መሥራቾች ቢያንስ አምስት መሆን እንዳለባቸው በንግድ ህጉ አንቀፅ 252 ስር ተደንግጓል።

- የማህበሩ አመሰራረት

ለአክሲዮን ማህበር ምስረታ ከሚያስፈልጉ ጠቅላላ ሁኔታዎች ውስጥ የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ ለማዋጣት መፈረም ፤እና ለጥሬ ገንዘብ በተሠጡ አክሲዮኖች ላይ ከተፃፈው ዋጋ ውስጥ ቢያንስ አንድ አራተኛው በመመስረት ላይ ባለው ማህበር ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሒሳብ መቀመጥ ያለበት መሆኑ ይገኙበታል። የተቀመጠውን ገንዘብ ማህበሩ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብ ከተቀመጠበት ሒሳብ ማውጣት አይቻልም።

በሌላ በኩል የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ባንክ መቀመጥ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በንግድ ህጉ አንቀጽ 259 መሠረት በሚቀርበው የማህበሩ መግለጫ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማህበሩን ማስመዝገብ ካልተቻለ በማህበሩ አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ ፈራሚዎች ገንዘባቸው ከባንክ ወለድ ጋር እንዲመለስላቸው መጠየቅ ይችላሉ።ገንዘቡ እንዲመለስ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ አደራጆች በንግድ ማህበር

መዝጋቢው አካል መዋጮው እንዲመለስ ማሳወቅ አለባቸው። መዝጋቢው አካልም ለጥያቄ አቅራቢው ፈራሚ መዋጮው እንዲመለስለት የሚመለከተውን ባንክ ማሳወቅ ይኖርበታል። ሆኖም የማህበሩ ምስረታ በቀሪዎቹ ፈራሚዎች ሊቀጥል ይችላሉ።

- የማህበሩ በንግድ መዝገብ መመዝገብ

የአክሲዮን ማህበሩ የተቋቋመው በምንም ዓይነት ቢሆንም በንግድ መዝገብ መግባት ያለበት ሲሆን ማህበሩ የሕግ ሰውነት የሚያገኘው በምዝገባ ይሆናል። ከምዝገባው ማመልከቻ ጋር በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ ማህበሩ ለሕዝብ ክፍት የሆነ እንደሆነ የማህበሩ መግለጫ፣ የዓይነት መዋጮዎች እና የምስረታ ኦዲት ሪፖርቶች እንዲሁም የፈራሚዎች ጉባዔ ቃለጉባዔ ተያይዞ መቅረብ አለበት። የአክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖችን መዝገብ በወረቀት ወይም ለረጅም ዘመን በሚቆይ የኤላክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል።

አክሲዮኖች የሚወጡበት ዘዴ በማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ ወይም ማሻሻያው ሊወሰን የሚችል ሆኖ በወረቀት ወይም በግዑዝ አልባ ማለትም ይህንን ስራ እንዲሰራ በህግ ሥልጣን በተሰጠው ተቋም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተፈጥሮ በኤለክትሮኒክ የአክሲዮን ሂሳብ የሚያዝ አክሲዮን ሊሆን ይችላል።መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ዜግነት፣ የአክሲዮኖችን ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠንና ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት።

የአክሲዮኖች አይነት

አክሲዮኖች በሚገዙበት ሁኔታ ላይ መሰረት በማድረግ በጥሬ ገንዘብ የሚገዙ አክሲዮኖች እና በአይነት መዋጮ የሚደረጉ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ከንግድ ህጉ አንቀፅ 281 እና 282 መገንዘብ ይቻላል።

በጥሬ ገንዘብ የሚገዙ አክሲዮኖች በተፈረሙ ጊዜ እጅግ ቢያንስ ከተጻፈባቸው ዋጋ አንድ አራተኛ ወይም በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ከፍ ያለ መጠን ተወስኖ ከሆነ ይኸው ዋጋ በሙሉ መከፈል አለበት።በመመስረቻ ጽሁፍ ያነሰ ጊዜ ካልተወሰነ በስተቀር፤ ያልተከፈለው የአክሲዮኖች ዋጋ ማህበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት መከፈል አለበት።

በዓይነት መዋጮ የተደረገ እንደሆነ የአይነት ማዋጮ የከፈለ ፈራሚ የባለሙያ ግምት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።የግምት ሪፖርቱ መዋጮ የተደረጉትን ንብረቶች፣ የእያንዳንዱን የዋጋ ግምት እና የአገማመቱን ዘዴ በዝርዝር መገለፅ ያለበት ሆኖ ሪፖርቱም ከመመስረቻ ጽሁፍ ጋር መያያዝ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል ከሚያስገኙት ጥቅም አንፃር የአክሲዮን ማህበራትን በሁለት ክፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን እነዚህም ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖች እና ትርፍ ብቻ የሚያስገኙ አክሲዮኖች ናቸው። ልዩ መብት የሚያስገኙ አክሲዮኖች የሚሰጡት ልዩ ጥቅም ወደ ፊት የሚወጡትን አክሲዮኖች በቅድሚያ የመግዛትን፣ ከትርፍ በቅድሚያ የመከፈልን ወይም የማህበሩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ መዋጮ ሲመለስ ወይም ተራፊ ሀብት ሲከፋፈል በቅድሚያ ክፍያ የማግኘትንና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል። ትርፍ ብቻ የሚያስገኙ አክስዮኖች ደግሞ ማህበሩ ዋናው ገንዘቡን ሳይቀንስ ካገኘው ትርፍ ወይም ካስቀመጠው መጠባበቂያ ገንዘብ ለባለአክሲዮኖች በአክሲዮኖቻቸው ላይ የተጻፈውን ዋጋ የሚመለስበት ነው።

በተጨማሪም በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 267 እንደተገለጸዉ በሚወጡበት መንገድ ላይ መሰረት በማድረግ በባለአክሲዮን ስም የሚወጡ የአክስዮን አይነቶች በባለአክሲዮን ስም የሚመዘገቡ ሲሆን ላምጪው የሚል አክሲዮኖች ሌላኞቹ የአክሲዮን አይነቶች ናቸው። ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን አዲሱ የንግድ ሕግ ከመውጣቱ በፊት ላምጪው የሚል አክሲዮኖች በሚገኙባቸው ማህበሮች ለአምጪው በሚል የወጡ አክሲዮኖች ባለቤት የሆነ ማንኛውም ሰው አክሲዮኖቹ በስም በሚመዘገብ እንዲለወጡለት ማህበሩ ዘንድ በመቅረብ ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ውስጥ ማመልከት አለበት።

- የማህበሩ ስራ አመራር

የአክሲዮን ማህበራት የስራ አመራር የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ተቆጣጣሪ ቦርድ ይኖራቸዋል።የአክሲዮን ማህበር በባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ቢያንስ ሦስት ቢበዛ አስራ ሦስት ዳይሬክተሮች እንደሚኖሩት እና ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከሦስት ሁለት እጅ (2/3ኛ) በማህበሩ የዕለት ተዕለት ሥራ አመራር ውስጥ የሥራ አስፈጻሚነት (ኤክስኪዩቲቭ) ሚና የሌላቸው መሆን እንዳለባቸው በንግድ ህጉ አንቀፅ 296 ስር ተደንግጓል። በተጨማሪ የማኅበር አባል ያልሆነ ሰዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል። እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚሰጥ ሀላፊነት እና ሥልጣን ይኖረዋል።ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ህጉ ዝርዝር ሀላፊነቶች እና ስልጣን ተካቶ ይገኛል። በተጨማሪም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚደርሰው ጉዳት ለማህበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ እንደሚሆኑ በንግድ ህጉ አንቀፅ 325 እና ተከታዮቹ ተመልክቷል።

በሌላ በኩል የአክሲዮን ማህበራት ተቆጣጣሪ ቦርድ በጠቅላላ ጉባዔ የሚሾሙ ቁጥራቸው ከሦስት ያላነሱ ከአምስት ያልበለጡ አባላት ሊኖሩት የሚችል ሲሆን ጠቅላላ ጉባዔው የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላትን በማንኛውም ጊዜ ሊሽራቸው ይችላል።

የተቆጣጣሪ ቦርድ አባል ሆነው መመረጥ የሚችሉት ባለአክሲዮኖች ብቻ ሲሆኑ የተቆጣጣሪ ቦርዱ ተጠሪነት ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል።የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት ስልጣን ፣ ተግባር እና ሀላፊነቶች በንግድ ህጉ አንቀፅ 332 እና ተከታዮቹ ተዘርዝሮ የሚገኝ ሲሆን ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን የማስቀረብ እና የመመርመር አንዱ ተግባር ነው ።

ስለማህበሩ መፍረስ እና ማህበሩ የሚፈርስባቸው ምክንያቶች

የአክሲዮን ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡--

የባለአክሲዮኖች ቁጥር በሕግ ከተፈቀደው ዝቅ ሲልና በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ አባል መተካት ባለመቻሉ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው በቀረበ ማመልከቻ መሠረት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤የአስተዳደር አካላት የሌሉት በመሆኑ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማህበሩ እንደፈርስ ሲወስን እና ማህበሩ የዋና ገንዘቡን ሦስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣ ናቸው።እንዲሁም በንግድ ህጉ እንቀፅ 181 የተዘረዘሩ የአጠቃላይ የንግድ ማህበራት መፍረስ ምክንያቶች ለአክሲዮን ማህበር መፍረስ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

በንግድ ሕጉ መሠረት ማህበሩ እንዲፈርስ በማህበሩ የተወሰነ እንደሆነ የመፍረሱ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ ማህበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰኑ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣና በማህበሩ ድረ ገጽ በይፋ መገለጽ ያለበት ሲሆን ማስታወቂያውም “በመጣራት ላይ ያለ” የሚል ሀረግ ተጨምሮበት የማህበሩን ስም፣ የዋና ገንዘቡን መጠን፣ የፈረሰበትን ምክንያት፣ የሂሳብ አጣሪውን ስምና አድራሻ እንዲሁም የሥልጣን ወሰን መያዝ አለበት። እንዲሁም ማህበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ እና በውሳኔው መሠረት ሒሳብ አጣሪ መሾሙን የሚያመለክቱ ሰነዶች በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት መቀመጥ እንዲሁም በንግድ መዝገብ መመዝገብ አለባቸው።

## የሕብረት ሽርክና ማሕበር በአዲሱ የንግድ ሕግ

*መግቢያ፡-*

ሕግ የሕብረተሰብን ባሕሪ የሚገዛ ሁነኛ መሳሪያ ነው። በመሆኑም አንድ ሕግ ሲወጣ የሀገሪቱን እና የሕዘቡን ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ማለትም የኢኮኖሚ፣ የንግድ ልማድ፣ ተቋማት እና ባህል ወዘተ ያገናዘበ መሆን

ይገባዋል። ከሁን በፊት የነበረን የንግድ ሕግ በ 1952 ዓ/ም የወጣ (ከ 60 ዓመት በላይ ያገለገለ) በመሆኑ በነዚህ ዘመናት ደግሞ ብዙ ነገሮች የተለዋወጡ በመሆኑ ሕጉ ያልሸፈናቸው በርካታ መስተጋብሮች መኖራቸው ግልፅ ነው። በመሆኑም ነባሩ የንግድ ሕግ አብዛኛው ክፍሉ በ 2013 ዓ/ም በወጣው አዲሱ የንግድ ሕግ (በአዋጅ ቁጥር 1243/13) ተሽሯል። በዚህ አጭር ፅሑፍ የአዲሱ የንግድ ሕግ አካል የሆነውን የሕብረት ሽርክና ማሕበርን የሚገዙ ድንጋጌዎችን ለማየት እንሞክራለን።

የሕብረት ሽርክና ማሕበር ምንነት፡-

የሕብረት ሽርክና ማሕበር ምን ማለት እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 183 ላይ የሚከተለው ትርጉም ተሰጥቶታል። “የኅብረት ሽርክና ማኅበር ማለት እያንዳንዱ ማህበርተኛ ለማኅበሩ ግዴታዎች ከማሕበሩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ የሚሆንበት የንግድ ማኅበር ነው፤ ማንኛውም ተቃራኒ ስምምነት ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።” ከዚህ ትርጓሜ የሚከተሉት ፍሬ-ነገሮች እናገኛለን፡-

“እያንዳንዱ ማሕበርተኛ”፡- በትርጓሜው ውስጥ “እያንዳንዱ ማሕበርተኛ ...” ማለቱ ሲታይ የሕብረት ሽርክና ማሕበር የሚመሰረተው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መሆኑን እና “ሽርክና” የሚለው ቃል የሚያሳያው አንድ ሰው ከሌላው ጋር በመሆን የሚፈጥረው ግንኙነት ወይም ማሕበር እንጂ የህብረት ሽርክና ማሕበር በአንድ ግለሰብ ብቻ የሚመሰረት አለመሆኑን ነው።

“ለማሕበሩ ግዴታዎች”፡- አንድ የንግድ ማሕበር በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት (legal personality) ስለሚያገኝ (አን.175) በስማቸው ውል መዋዋል፣ ንብረት ማፍራትና ባለቤት መሆን፣ በፍርድ ቤት መክሰስም ሆነ መከሰስ እናም ሌሎች መብቶችና ግዴታዎች ይኖሯቸዋል ማለት ነው።

“ከማሕበሩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ የሚሆኑበት”፡- ሲል ደግሞ የማሕበሩ አባላት ከማሕበሩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን በተለይም ማሕበሩ ሊወጣቸው የሚገቡት ግዴታዎችን በተመለከተ የአባላቱ ኃላፊነት እስከምን ድረስ መሆኑን ያስረዳል። በመሆኑም በድንጋጌው መሰረት የማሕበሩ አባላት “በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው” ሲል ማሕበሩ ላለበት ግዴታ የማሕበሩ አባል የሆነ ሰው ከማሕበሩ እና/ወይም ከሌላ ማሕበርተኛ ጋር በጋራ ወይም ብቻውን የመወጣት ወይም የመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን ያሳያል።

የሕብረት ሽርክና ማሕበር አመሰራረት (አንቀፅ 185)፡-

አንድ የሕብረት ሽርክና ማሕበር ለመመስረት በቅድሚያ የመመስረቻ ፅሑፍ እንዲኖረው ያስፈልጋል። የመመስረቻ ፅሑፉ በአንቀፅ 185 ስር በሰፈረው አኳኋን በርካታ ዝርዝር ነገሮችን አካቶ መያዝ አለበት።

ከነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች መካከል የሚከተሉትን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡- የማኅበሩን ስም፣ የማኅበሩን ዋና መሥሪያ ቤትና እንዲሁም ቅርንጫፎችን፣ የእያንዳንዱን ሽሪክ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፣ ማኅበሩ የተመሠረተበትን ዓላማ፣ እያንዳንዱ ሽሪክ ያዋጣውን የገንዘብ መጠን፤ የተከፈለው የዓይነት መዋጮ ከሆነ የገንዘብ ግምቱን እና የአገማመት ዘዴ ወዘተ የሚሉትን ማካተት ይኖርበታል።

የመዋጮ ዓይነትና መጠን (አንቀፅ 186)፡-

የንግድ ማሕበራት ሰዎች መዋጮ አዋጥተው በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመሰማራት ከሚገኘው ትርፍ ተካፋይ ለመሆን በመመስረቻ ጽሑፍ አማካኝነት የሚያቋቋሟቸው ድርጅቶች ስለመሆናቸው ከአንቀፅ 172 መረዳት ይቻላል። የሕብረት ሽርክና አባል ከሚከተሉት አንዱን በማዋጣት ሽሪክ መሆን እንደሚችል በሕጉ ተቀምጧል። በዚህም መሰረት ጥሬ ገንዘብ፣ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ የሞያ አገልግሎት፣ የንግድ ምልክት፣ መልካም ስም፣ ፓተንት፣ ኮፒ ራይት፣ የሊዝ መብት፣ የአላባ ጥቅም ወይም ሌላ የዓይነት መዋጮ መክፈል ያለበት ሲሆን መዋጮው የማኅበሩ ሃብት እንዲሆን ወይም ማኅበሩ እንዲጠቀምበት ሆኖ ሊከፈል ይችላል። ሽሪኮች ለማኅበሩ የሚያስገቡት መዋጮ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስፈልገው ዓይነትና መጠን እንዲሁም ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መጠኑ እኩል መሆን አለበት እና የዓይነት መዋጮ ግምት በሽሪኮች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል።

የማሕበሩ ሽሪኮች መብቶችና ግዴታዎች (አንቀፅ 190-191)፡-

የማሕበሩ አባላት በመብቶቻቸው በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዲሁም ግዴታዎቻቸውንም በአግባቡ መወጣት አለባቸው። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ መብቶቹና ግዴታዎቹ የሕግ ድጋፍ ያላቸውና በዝርዝር ተለይተው መታወቅ አለባቸው። በመሆኑም የአባላቱ መብቶችና ግዴታዎች እንደሚከለው በንግድ ሕጉ ተቀምጠዋል፡-

የማኅበሩ ሽሪኮች መብቶች፡- እያንዳንዱ የማኅበሩ ሽሪክ በማኅበሩ ስብሰባዎች የመሳተፍና ድምጽ የመስጠት፣ ከማኅበሩ ትርፍ ድርሻውን የመካፈል፣ ስለማኅበሩ አሰራር ጥያቄ የማቅረብ፣ የሒሳብ መግለጫዎችን እና ሰነዶችን የማየት፤ ማስታወሻ የመውሰድ፣ የማኅበሩ ቆይታ ከአንድ ዓመት በላይ ሲሆን በየዓመቱ መጨረሻ የሥራ ክንውን ሪፖርት እንዲቀርብ የመጠየቅ፣ ማኅበሩ ሲፈርስ ከማኅበሩ ሃብት ድርሻውን የመካፈል፣ እና ሌሎች ከማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም ከማኅበር ሽሪክነት የሚመነጩ መብቶችንና ጥቅሞችን የማግኘት መብቶች አሉት።

የማኅበሩ ሸሪኮች ግዴታዎች፡- እያንዳንዱ የማኅበሩ ሸሪክ የማኅበሩን መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፣ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት በትጋትና በጥንቃቄ የመሥራት፣ ለግልም ሆነ ለሦስተኛ ወገን ጥቅም የማኅበሩን ጥቅም የሚጎዳ ተግባር አለመሥራት፣ ለማኅበሩ ዕዳዎች በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ የመሆን፣ ሌሎች ከመመስረቻ ጽሑፍና ከማኅበሩ ሸሪክነት የሚመነጩ ግዴታዎችን የመወጣት ግዴታዎች አሉበት።

የሕብረት ሽርክና ማሕበር ሥራ አመራር (አን. 198-203)፡-

የሕብረት ሽርክና ማሕበር ከአባላቱ ውስጥ ወይም ሸሪክ ያልሆኑ የራሱ አመራሮች የሚኖሩት ሲሆን የአመራሮቹ ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ የስራ ድርሻቸው በፅሑፍ መገለፅ ይኖርበታል። የማሕበሩ ሥራ አስኪያጅ የማሕበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ማንኛውም ሥራዎች በማሕበሩ ስም ያከናውናል። የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን የሚገድቡ ስምምነቶች ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ የሚሆኑት በንግድ መዝገብ የተመዘገቡ ወይም ሦስተኛ ወገኖች የሥራ ኃላፊነቱን የሚያዉቁ መሆናቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።ሥራ አስኪያጁ በማኅበሩ ስም ለግል ጥቅሙ የሰራ እንደሆነ በቅን ልቦና ከሥራ አስኪያጁ ጋር ግንኙነት ላደረጉ ሦስተኛ ወገኖች ማኅበሩ ኃላፊነት ይኖርበታል። ሆኖም ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩን ስም ያላግባብ መገልገሉን የሚያውቁ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ኃላፊነቱ የሥራ አስኪያጁ ብቻ ይሆናል። በተለይም የማኅበሩን ስም ሳይጠቅስ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ስምምነት ካደረገ ለግል ጉዳዩ እንዳደረገው ይቆጠራል፤ ሆኖም ሥራ አስኪያጁ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ያደረገው ስምምነት ለማኅሩ ጥቅም የሆነ እንደሆነ ማኅበሩ ኃላፊ የሚሆን ይሆናል።

የሕብረት ሽርክና ማሕበር መፍረስ (አን. 205-206)፡-

የሕብረት ሽርክና ማሕበር በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈርስ የሚችል ሲሆን የሚከተሉት ምክንያቶች ለመፍረስ ያሚያበቁ ናቸው ተብለው በሕጉ ተቀምጠዋል፡- ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ከማኅበሩ ሸሪክ በአንዱ እድሜ ልክ ድረስ ከሆነ ወይም በመመስረቻ ጽሁፉ ውስጥ የማፍረስ መብት ተጠቅሶ እንደሆነ ማንኛውም ሸሪክ በቅን ልቦና የስድስት ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲፈርስ ሲጠይቅ፣ ከማኅበሩ ሸሪኮች አንዱ በአካል ጉዳት ወይም በሕመም ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የማኅበሩን ሥራ ለማከናወን ያልቻለ እንደሆነ፣ በማኅበሩ ሸሪኮች መካከል አብሮ ለመሥራት የማያስችል አለመግባባት ሲፈጠር፣ ከማኅበሩ ሸሪኮች አንዱ ሲሞት ወይም የማህበርተኛው መክሰር በፍርድ ሲወሰን ወይም ሸሪክ ለመሆን ችሎታ ሲያጣ፣ ከማኅበሩ ሸሪክ የግል ገንዘብ ጠያቂዎች ያለውን ድርሻ በሙሉ ሲወስዱ ወይም በቀሪው ድርሻ እንዲቀጥል ሌሎች የማኅበሩ ሸሪኮች የማይስማሙ ከሆነ ማሕበሩ ሊፈርስ ይችላል።

ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ቢኖርም ቀጥሎ በተጠቀሱት ምክንያቶች ማኅበሩ ሳይፈርስ ሊቀጥል ይችላል፡- ከሸሪኮች አንዱ ማኅበሩ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲያቀርብና ቀሪዎቹ ሸሪኮች የሸሪኩን ድርሻ ከፍለው ማኅበሩ እንዲቀጥል ሲስማሙ፤ ወይም ለሞተው ሸሪክ ወራሾች ወይም ችሎታ ላጣው ሸሪክ ሞግዚት ወይም ለከሰረው ሸሪክ ንብረት ጠባቂ የሚችን ወይም ችሎታ ያጣውን ሸሪክ ወይም የከሰረውን ሸሪክ ድርሻ በመክፈል ማኅበሩ እንዲቀጥል ስምምነት ሲደረግ ማሕበሩ ሊቀጥል ይችላል።

**ሒሳብ ስለማጣራት** (አን. 207-209)፡-

በማሕበሩ የመመስረቻ ፅሑፍ፣ በሸሪኮች ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት የሒሳብ አጣሪ እስከሚመደብ ድረስ ሥራ አስኪያጆች የነበራቸውን ስልጣን እንደያዙ የሚቆዩ ሲሆን ለሒሳብ አጣሪዎች የማህበሩን ንብረትና ማንኛውንም አስፈላጊ ሰነድ ማስረከብና እስከ ርክክቡ ቀን ድረስ ያከናወኑትን ሥራ ማስረዳት አለባቸው። ሒሳብ አጣሪዎች የማኅበሩ የመጨረሻ ሂሳብ እንዲጣራ አስፈረላጊ የሆኑትን ተግባሮች ሁሉ ይፈጽማሉ። በዚህም መሰረት ተጀምረው የነበሩ ሥራዎችን የማገባደድ፣ የማኅበሩን የሃብትና ዕዳ መግለጫ የማዘጋጀት፣ የማኅበሩን ሃብት የመሰብሰብ፤ የማኅበሩን ንብረት የመሸጥ፤ የማኅበሩን ዕዳ ከማኅበሩ ሃብት ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከሸሪኮች ሌላ ገንዘብ ሰብስቦ ለገንዘብ ጠያቂዎች የመክፈል፣ በማኅበሩ ስም በፍርድ ቤት፣ በአስተዳደር አካላት ወይም በግልግል ዳኝነት የመከራከርና ጉዳዮችን የማስፈጸም፣ የማኅበሩን ሃብት ለሸሪኮች የማከፋፈል፣ ማኅበሩን ለማፍረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን ሥልጣን አላቸው። የሥራ አስኪያጆችን ተጠያቂነት የሚመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች በሒሳብ አጣሪዎች ላይም ተፈጻሚነት አላቸው።

ስለ ክፍፍል (አን. 211-212)፡-

የማኅበሩ ዕዳዎች ከተከፈሉና እያንዳንዱ ሸሪክ የከፈለው መዋጮ ከተመለሰ በኋላ ትርፍ ካለ በአባለቱ መካከልየሚከፋፈል ይሆናል። የማኅበሩ ገንዘብ ለሸሪኮች የሚመለሰውን መዋጮ ለመክፈል የማይበቃ ከሆነ ኪሳራው በሸሪኮች መካከል ይከፋፈላል። በመመስረቻ ጽሑፉ ሌላ የአከፋፈል ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ትርፍና ኪሳራው በሸሪኮች መካከል እኩል ይከፋፈላል።

**በአዲሱ የንግድ ሕግ ውስጥ የተካተቱ የንግድ ማህበር አይነቶች**

1. የንግድ ሕግና የንግድ ማኅበር ምንነት

ሕግ በዋናነት የሕዝብ ሕግ / Public Law / እና የግል ሕግ /Praivate Law/ በሚል የሚታወቅ ሲሆን የንግድ ሕግ የግል ሕግ ከሚባሉት ዉስጥ አንዱ ነዉ። ይህ ሕግ የንግድ ግንኙነቶችን እና

እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠሩ ሕጎችና መመሪያዎች ስብስብ ነዉ። የንግድ ሕግ መነሻዉ ወይም ለዘመናዊዉ ኅብረተሰብ የመጀመሪያ ማጣቃሻ የፈረንሳይ የንግድ ሕግ ነበር። እያንዳንዱ ሀገር አሁን ካለዉ የሕግ ማዕቀፍ ጋር የሚስማማ የራሱ የንግድ ሕግ አለዉ። ለዚህምነዉ ለሀገራችንም አዲስ የንግድ ሕግ ያስፈለገዉ።

የንግድ ማኅበር ማለት ሰዎች መዋጮ አዉጥተዉ በሕብረት በኢኮኖሚያዊ እንቀስቃሴ በመሰማራት ከሚገኘዉ ትርፍ ተካፋይ ለመሆን በመመስረቻ ጽሁፍ አማካኝነት የሚያቋቁሙት ማኅበር ነዉ። የንግድ ማህበራት አንድና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን አዋጥተው በጋራ ለመስራት ተስማምተው የሚመሰርቱት የንግድ ድርጅት አይነት ነው። ነገርግን የእሽሙር ማኅበር የሚቋቋመዉ ማኅበርተኞች በመካከላቸዉ በሚያደርጉት በ 3 ኛ ወገኖች በማይታወቅ ዉል አማካኝነት ነዉ። በሌላ በኩል ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የንግድ ማኅበር ነዉ።

## 2. የንግድ ማኅበራት ዓላማ

አንድ የንግድ ማኅበር በዕለት ተዕለት የንግድ እንቅስቃሴው ከተለያዩ አካላት ጋር የውል እና ከውል ውጪ የሆኑ ግንኙነቶችን ይኖረዋል። ማኅበሩ ከባለሀብቶቹ የተለየ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ማኅበር በመሆኑ ከማኅበርተኞቹ ጭምር ግንኙነት ይኖረዋል። ከላይ ከተገለጹት የንግድ ድርጅት ከሚፈጥራቸው ዘርፈ ብዙ ግንኙነት አኳያ የንግድ ማህበራት ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች፦

- አንደኛው ዋና ዓላማ አንድ የንግድ ድርጅት ከላይ በተመለከትናቸው ውስብስብ ግንኙነቶች ውስጥ ተንቀሳቅሶ ሀብት ማፍራት እና አትራፊ እንዲሆን በሚያስችል የንግድ ሥራ መሰማራት፣
- ሁለተኛው ደግሞ ከላይ ለተጠቀሱት ከአንድ የንግድ ድርጅት ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች ለሚፈጥሩት አካላት መብቶች እና ቅቡልነት ያላቸው ፍላጎቶች ተገቢውን የሕግ ጥበቃ ማግኘት የሚሉ ዓላማዎች ሲሆኑ ሌሎች ዓላማዎች አሏቸዉ።

## 3. የንግድ መኅበራት በጠቅላላዉ

የንግድ ማህበራት ዕድገት ከሀገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው። የትሳሰሩ ሰንሰለት የሚጀምረው በግለሰብ ደረጃ ንግድን ከማካሄድ ሲሆን በተደራጀ መልክ እስከ ማስኬድ የሚዘልቅ ነው። ይህ የተለያየ ደረጃዎችን እያለፈ አሁን ወዳለንበት ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች (Transnational corporations) ዘመን ግለባላይዘሽን ደርሷል። በኢትዮጵያ የድንበር ተሻጋሪ ኩባንዎች ማሳያ የሆነው የፈረንሳይ-ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩባንያ “Franco - Ethiopian Rail way company” በ 1884 ዓ.ም ወደ ሀገራችን የገባ ቢሆንም እስከተጠቀሰው ጊዜ ኢትዮጵያ ኩባንያ የሚባልም ሆነ የንግድ

ማህበራት ህግ እንዳልነበራት ከታሪክ ፀሀፍት መገንዘብ ይቻላል። ሁለተኛው ኩባንያ በ1905 የተከፈተው አብሲኒያ ባንክ ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ ሳይሆን የግብፅ ብሄራዊ ባንክ ቅርንጫፍ በመሆን የተከፈተ ነበር። ለመጀመርያ ጊዜ በኢትዮጵያ የተከፈተው የኢትዮጵያ ባንክ (Bank of Ethiopia) በ1931 ዓ.ም ሲሆን ቀጥሎ የኢትዮጵያ እርሻና ንግድ ልማት ኩባንያ በጥቂት የገዢ መደብ መስራችነት ሊቋቋም ችሏል። በአገራችን የንግድ ማህበራት ህግ ለመጀመርያ ጊዜ የወጣውም በ1933 ዓ.ም ነበር። በተደራጀ መንገድ የንግድ ስራን የማከናወን መብት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና ይህን መሰረት በማድረግ ከወጡት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች አንፃር ስንመለከተውም የንግድ ማህበር ሰዎች በግላቸው ከመነገድ ይልቅ ለአንድ የኢኮኖሚያዊ ዓላማ በመደራጀት በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት የሚያስችላቸው የገንዘብ አቅምንና የገበያ ማስፋፋትን መሰረት በማድረግ በተሻለ የንግድ ስራ የተሻለ ገቢ ለማግኘት አቅደው የሚመሰርቱት ነው። ይህ የመደራጀት መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 31 ላይ “ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ በማለት ስለተደነገገ “ማንኛውም ሰው” የሚለው የህገ-መንግስቱ ኃይለ ቃል የሚያመለክተው የተፈጥሮ ሰውንና በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው የንግድ ማህበራት መደራጀትን ሲገልፅ “ለማንኛውም ዓላማ” የሚለው ደግሞ ለንግድ ስራም ጭምር በንግድ ማህበር የመደራጀትን መብት የሚፈቅድ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ይህ በንግድ ማህበራት የመደራጀት መብት በህገመንግስቱ አንቀፅ 41(2) “ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደርያውን ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው” ከሚለው ህገ-መንግስታዊ መብት አንፃር ያየነው እንደሆነም ዜጎች አዋጪ ነው ባሉት የንግድ ማህበር መርጠው እንደመተዳደርያ ስራቸው ሊወስዱት የሚያስችል ህገመንግስታዊ መብት ያላቸው መሆኑን እንድንረዳ የሚያስችለን ነው። ዜጎች በተናጠል ቢሰሩዋቸው የማዋዕለ ንዋይ እና የማስተዳደር ዓቅማቸውን የሚፈታተኑ የንግድ ስራዎች ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማና የወደፊት በዘርፉ ተስማርተው በመስራት የመበልፀግ ራዕይ ካላቸው ሰዎች ጋር ተደራጅተው በተለያየ የኢኮኖሚ ዘርፍ በመስራት ራሳቸውን ጠቅመው በአገራዊ ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ማረጋገጥ ሂደት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ስለሆነ በስፋት ልንሰራበት የሚያስችለን የአደረጃጀት ስርዓት ነው። አገራችን ወደ ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲና እስትራተጂ ትግበራ ከገባች ወዲህ በንግድ ህጉ ባሉ ድንጋጌዎችና የገበያ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በወጡ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና የባንክና ኢንሹራንስ

አሰራሮች ታግዘው እጅግ በርከታ አክስዮን ማህበራትና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት ተመስርተው በመስራት ላይ ናቸዉ።

4. የንግድ ማህበራት አይነቶች

በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 174 መሰረት በእኛ ሀገር ሰባት ዓይነት የንግድ ማኅበራት አሉ። እነሱም፦

- የኀብረት ሽርክና ማኅበር / General Partnership/
- ሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር /Limited Partnership/
- ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር /Limited Liability Partnership/
- የአሽሙር ማህበር /Joint Ventur/
- የአክሲዮን ማህበር /Share Company/
- ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /Private Limited Company/ እና
- ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር / One Person private limited Company/ ናቸው።

እነዚህን የንግድ ማህበራት በግለሰብ ከሚመሰረቱ የንግድ ድርጅቶች የሚለዩት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁና አንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች የሚተዳደር መሆኑ ሲሆን ትላልቅና ዘርፈ ብዙ ተግባራት ያላቸውን የንግድ ድርጅቶች ለመመስረት ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው። የንግድ ማህበራት እንደ ግለሰብ ነጋዴ ሁሉ ጠቀሜታና ጉዳት ይኖራቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ ስለ እነዚህ ማህበራት በሰፋት እንመለከታለን።

♣ የኀብረት ሽርክና ማህበር

የህብረት ሽርክና ማህበር በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 283 መሰረት ማኅበርተኞች እያንዳንዳቸው ባንድነትና ሳይከፋፈል እርስ በርሳቸውና ለማህበሩ ግዴታዎች አላፊዎች የሚሆኑበት ማኅበር ነው። ይህም ማለት ማህበሩ ለሚያጋጥመው አደጋ ወይም እዳ ሁሉ እያንዳንዱ አባል በግሉ፣ ወይም ሁሉም በአንድነት ወይም ከሁሉም የተወሰኑት ብቻ በተናጥል ለእዳው ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው። ማንኛዉም ተቃራኒ ስምምነት ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም። የህብረት ሽርክና ማህበር የተቋቋመው ለንግድ ዓላማ ከሆነም ማህበርተኞቹ እንደነጋዴ ይቆጠራሉ። ይህ አይነቱ ማህበር ሲመሰረት በንግድ መዝገብ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ማህበሩ ሙብት የማግኘት፣ የግዴታ ውል የመግባት እና በማህበሩ ስም በፍርድ ቤቶች መክሰስ ወይም መከሰስ ይችላል። በንግድ ህጉ መሰረት የዚህ አይነቱ ማህበር የማህበር ስም የሚኖረው ሲሆን በማህበሩ ስም ላይ የማህበርተኞቹ ስም ሁሉ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ቢያንስ የሁለት ሰዎች ስም ተጽፎ ከስማቸው

ቀጥሎ “የህብረት ሽርክና ማህበር፡ ተብሎ መፃፍ አለበት። በስሙ ላይ ከማህበርተኞቹ ስም በቀር ሌላ ስም ሊገባበት አይችልም። ስሙ በማህበሩ ስም ላይ የተገለጸ ሽሪክ ከማኅበሩ የወጣ እንደሆነ የማኅበሩ ስም መለወጥ አለበት። የማኅበሩ ሽሪክ ያልሆነ ሰዉ እያወቀ ስሙ በማኅበሩ ስም ዉስጥ ሲፃፍ ያልተቃወመ እንደሆነ እንደሌሎች አባላት ለማኅበሩ ግዴታዎች ኃላፊ ይሆናል። የህብረት ሽርክና ማህበር ከሌሎች የሽርክና ማህበራት ሁሉ በብዛት የተለመደና በርካታ የንግድ ሰዎች የሚመርጡት የሽርክና አይነት ነው።

♣ ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር

ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር ከስሙ እንደምንረዳው የማኅበርተኞቹ ኃላፊነት የተለያየ የሆነበት ማኅበር ነዉ። የዚህ ዓይነቱ ማህበር ስም የሚያስፈልገው ሲሆን ስሙም ቢያንስ የሁለት ኃላፊነታቸዉ ያልተወሰነ ሽሪኮች ስም በመያዝ ከስሙ ቀጥሎ “ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማህበር” ተብሎ መፃፍ አለበት። ማኅበሩ ሁለት ዓይነት ሽሪኮች ወይም ማኅበርተኞች አሉት። እነሱም ኃላፊነታቸዉ ያልተወሰነ ሽሪኮችና ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ ሽሪኮች ናቸው። በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 212 መሰረት ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ ሽሪኮች የሚባሉት ለማኅበሩ ግዴታዎች በሙሉ ከማኅበሩ ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት ያለባቸዉ ሲሆን ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ ሽሪኮች ደግሞ መዋጮ ለማድረግ ቃል በገቡት መጠን ብቻ ለማኅበሩ ግዴታች ኃላፊ የሚሆኑ ናቸዉ። ኃላፊነታቸው የተወሰነ ሽሪኮች በወክልናም ሆነ በሌላ በማንኛዉም ሁኔታ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ መሆን አይችሉም። ክልከላዉን የተላለፈ ኃላፊነቱ የተወሰነ የማኅበሩ ሽሪክ በሥራዉ ምክንያት ለሚመጡ ግዴታዎች ኃላፊነታቸዉ ካልተወሰነዉ ሽሪኮች ጋር በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናል። ኃላፊነታቸው የተወሰነ የማኅበሩ ሽሪኮች በአንቀጽ 218 ንዑስ አንቀጽ 4 ስር ተዘረዘሩትን ተግባራት ቢያከናዉኑ የሥራ አስኪያጅነት ሥራ እንደሰሩ አይቆጠርም።

♣ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሙያ ሽርክና ማኅበራት

በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ከተካተቱ ጉልህ ለውጦች መካከል አንዱ የሆነው ይህ አዲስ የሽርክና ማህበር አይነት፣ ሰዎች በተለይም የሙያ ስራዎችን ለመስራት በሙያ ከሚመስሏቸው ሌሎች ሰዎችና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ አጋሮቻቸው ጋር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው የሚያቋቁሙት እና ኃላፊነቱም በሽርክና ማኅበሩ ሃብት ላይ ብቻ የተወሰነ የንግድ ማኅበር ነው። ከቀደመው ሕግ በተቃራኒው አዲስ የጸደቀው አዋጅ ግለሰቦች በሙያቸው ተደራጅተው እንዲሠሩ በግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል። እያንዳንዱ ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ይዘው ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ የሽርክና የሙያ ማኅበራት እንዲስፋፉ ያስችላል።

በሌላ በኩል የቀድሞው ሕግ የአክስዮን ማኅበራት የዳይሬክተሮች የቦርድ አባላት ሁሉም የአክሲዮን ባለድርሻ እንዲሆኑ ግዴታ የጣለ ነበር። ነገር ግን በአዲሱ ሕግ ባለድርሻ መሆን ሳይጠበቅባቸው፤ ባለ ድርሻ ያልሆኑ ሰዎች በሙያቸው እስከ አንድ ሦስተኛ ድረስ የሚሆነውን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ቦታን እንዲይዙ ይፈቅዳል። ይህ አይነቱ የሽርክና ማኅበር የህግ አገልግሎትን፣ የሂሳብ መዝገብና ኦዲት ወይም ሌላ አይነት ቴክኒካዊ እውቀትን በሚጠይቁና የሙያ ፈቃድ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የስራ ዘርፎች ላይ በቅንጅት መስራት ለሚሹ ሙያተኞች አይነተኛ ምርጫ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

♣ የአሽሙር ማህበር

የአሽሙር ማህበር ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በመካከላቸዉ በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት የሚያቋቁሙት ሲሆን ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በጽሁፍ መረጋገጥና በሌሎች የንግድ ማህበሮች የተደነገጉ የማስመዝገብ ሰርዓቶች የማይፈፀሙበት፣ የሕግ ሰዉነት የሌለውና በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ የማይታወቅ መሆኑ ሲሆን ከታወቀ ግን እንደ ሕብረት ሽርክና ማህበር እንደሚቆጠር ሊታወቅ ይገባል።

♣ የአክሲዮን ማህበር

የአክሲዮን ማህበር ማለት በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 245 መሰረት ዋናው ገንዘቡ ወይም ካፒታሉ አስቀድሞ ተወስኖ በአክስዮን የተከፋፈለና ኃላፊነቱ በማኅበሩ ሀብት ብቻ የተወሰነ (ለዕዳው ንብረቱ ብቻ ዋስ የሆነ) ማኅበር ነው። ይህም ማለት አባላት አስቀድሞ ተወስኖ የተከፋፈለ አክሲዮን በመግዛት የንግድ ማህበሩ ባለቤት የሚሆኑበት ሲሆን ማህበሩ በሚያጋጥመው ማናቸውም አይነት ዕዳ እያንዳንዱ አባል ኃላፊነት ሊወስድ የሚችለው በማህበሩ ላይ ባለው ካፒታል መጠን ብቻ ነው ማለት ነው። የአክስዮን ማኅበሩ የሚጠራበት ስም ይኖረዋል። ከሌላ ነጋዴ ወይም ማኅበር ጥቅም ጋር የሚጋጭ እስካልሆነና የሌሎች 3ኛ ወገኖች መብት እስካልተነካ ድረስ የማኅበሩ መጠሪያ በማኅበርተኞች ስምምነት ይወሰናል። ከስሙ መጨረሻ ላይ “የአክስዮን ማኅበር" የሚል ሐረግ መጨመር ይኖርበታል። የአክሲዮን ማህበር አባላት ቢያንስ አምስት መሆን ያለባቸው ሲሆን በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ወይም ካፒታል ከሃምሳ ሺህ ብር በታች መሆን እንደሌለበት እና የማህበሩ የአንድ አክሲዮን ዋጋ ከብር አንድ መቶ ብር ማነስ እንደሌለበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 247 ላይ ተመልክቷል። መስራች አባላት ለሶስተኛ ወገኖች ለማህበሩ መቋቋም ለገቡባቸው ግዴታዎች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸዉ። የማኅበሩም መቋቋም የሰዎች ወይም የአባላት ማንነት ላይ ሳይሆን በኩባንያው ውስጥ የሚገባውን ገንዘብ ከግምት በማስገባት ነው።

♣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 495 መሰረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማለት ዋና ገንዘቡ በሙሉ አስቀድሞ የተከፈለ፣ በአክስዮን የተከፈለ እና ባለአክስዮኖች መዋጮቸዉን ገቢ እስካደረጉ ድረስ ለማኅበሩ ዕዳ ኃላፊ የማይሆኑበት የንግድ ማኅበር ነዉ። ማናቸውም ማህበርተኛ ካስገባው መዋጮ በላይ አላፊ የማይሆንበት ማህበር ማለት ነው። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ዓላማዉን የሚገልጽ ስም ይኖረዋል። ከማኅበሩ ስም ቀጥሎ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" የሚል ሐረግ መፃፍ አለበት። የማኅበሩን አክስዮኖች ለሕዝብ ክፍት በሆነ ገበያ መሸጥ አይቻልም። የዚህ አይነቱ ማኅበር ባለአክስዮኖች ቁጥር ከሁለት ማነስ ከሃምሳ ሰዎች መብለጥ አይችልም። የባለአክስዮኖቹ ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለ እና በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ሌላ ሰዉ ካልገባ ማኅበሩ ይፈርሳል። ይህ ካልሆነ የባለአክስዮኖቹ ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ካለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ዉስጥ የመመስረቻ ጽሁፋን በማሻሻል ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አድርጎ ማስመዝገብ ይቻላል። ማኅበሩ የሚተላለፉ የግዴታ ወረቀቶችን ማዉጣት አይችልም። የማኅበሩ አነስተኛ ዋና ገንዘብ ከአስራ አምስት ሺህ ብር ያነሰ መሆን አይችልም። እያንዳንዱ አክስዮን ላይ የሚፃፈዉ ዋጋ ከአንድ መቶ ብር በታች መሆን አይችልም፣ በሁሉም አክስዮኖች ላይ የተፃፈ ዋጋ እኩል መሆን አለበት።

♣ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማለት አንድ ሰዉ በግሉ በሚሰጠዉ መግለጫ መሰረት የተቋቋመ የንግድ ማኅበር ነዉ። ማኅበሩ ከአባሉ የተለየና የተነጠለ የራሱ የሕግ ሰዉነት አለዉ። አባሉ የራሱን መወጮ ሙሉ በሙሉ እስከ ከፈለ ድረስ ማኅበሩ ላይ ለሚፈለገዉ ዕዳ በግሉ አይጠየቅም። የማኅበሩ ዝቅተኛ ዋና ገንዘብ ከ ብር አስራ አምስት ሺህ ማነስ የለበትም። ማኅበሩን ለማቋቋም አባሉ የሚሰጠዉ መግለጫ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግ አለበት። መግለጫዉም በንግድ መዝገብ ዉስጥ መግባት አለበት። ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ሥራዉን ወደ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርነት መለወጥ ይችላል። ሆኖም ግን ግለሰብ ነጋዴዉ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግለሰብ ማኅበር ከመመስረቱ በፊት ለገባበት ዕዳ ሁሉ ከማኅበሩ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊ ነዉ።

በአጠቃላይ የንግድ ማህበራት ገፅታን ስንመለከት የራሳቸው የሆነ ህጋዊ አደረጃጀት ያላቸው ሆነው ህጋዊ ሰውነት ለማግኘትና ወደ ገበያው ለመግባት የምዝገባ፣ ፈቃድና ማስታወቅ ስራዎችን የሚጠይቁ ጠንካራ የአገር ኢኮኖሚ በመገንባት ሂደት የተበታተነን መዋዕለ ንዋይ አሰባስቦ በተደራጀ መልክ የልማት ስራን ለማከናወን የሚያስችሉ መሳሪያዎች ሲሆኑ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተደራጅቶ የንግድ ስራ የማከናወን መብት በሕገ-መንግስቱና ከዚያ በታች ባሉ ህጎች የተረጋገጠ መብት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

የንግድ መዝገብ በአዲሱ የንግድ ህግ

-----------------------------------

የንግድ መዝገብ (commercial register) በተለያዩ አለም ሀገራት የተለመደ አሰራር ነው። በሀገራችንም በ 1952 ዓ.ም በወጣው የንግድ ህግ የተካተተ ሲሆን የንግድ ህጉ ከወጣበት 1950 ቹ በኋላ በሀገራችን በርካታ ነገሮች የተቀየሩ ከመሆኑ አንፃር 2008 ዓ.ም በወጣው የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በማሻሻያው 1150/2011 በጊዜ ሂደት መካተት የነበረባቸውን ሁኔታዎች ለማሟላት ተሞክሮ ነበር። ሆኖም የንግድ ህጉ ሀገራችን አሁን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ማካተት እንደሚገባው ስለታመነበት የቀደመው የንግድ ህግ በአዲሱ የንግድ ህግ እንዲተካ ተደርጓል። በዚህ አጭር ፅሁፍ የንግድ መዝገብ ምንነት፣ በውስጡ የሚያካትታቸውን ዝርዝር ነገሮች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን እንመለከታለን።

የንግድ መዝገብ (commercial register) ምንነት

የንግድ መዝገብ (commercial register) በአዲሱም ሆነ በቀድሞ የንግድ ህግ ትርጉም አልተሰጠውም። በንግድ ምዝገባ እና ፋቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀፅ 2(20) ንግድ ምዝገባ ማለት በንግድ ህጉ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የሚደረግ ምዝገባ ነው በሚል ትርጉም የሰጠ ቢሆንም የንግድ መዝገብን ምንነት በግልፅ አላስቀመጠም። ሆኖም በተለያዩ ሀገራት ካለው ግንዛቤ እና በእኛም ሀገር ህግ የንግድ መዝገብን አስመልክቶ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች አንፃር የንግድ መዝገብ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ የሚያዝበት የመረጃ መመዝገቢያ ሥርአት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ንግድ መዝገብን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለው ህግ

የንግድ ምዝገባን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በንግድ መዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እንዲሁም በንግድ ህጉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ እንደመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው ህግ የቱ ነው የሚል ጥያቄ መነሳቱ የሚጠበቅ ነው። ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በአዲሱ ንግድ ህግ ረቂቅ ማብራሪያ ላይ ምላሽ ተሰጥቶበታል። ይኸውም የንግድ ምዝገባን የሚመለከቱ በየጊዜው የማይለዋወጡ መሰረታዊ መርሆዎች በንግድ ህጉ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉ በመሆኑ በሁለቱም ላይ የተገለፁ ጉዳዮችን ቢሆኑ እንኳን ገዢ የሚሆነው የንግድ ህጉ

ይሆናል። ሌሎች ተለዋዋጭነት ያላቸው ከዕለት ተዕለት ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች በተመለከተ ግን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ ከነማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1150/2011 ተፈፃሚ ይሆናል ማለት ነው።

የንግድ መዝገብ አደረጃጀት

በአዲሱ የንግድ ህግ የንግድ መዝገብ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋም ሲሆን ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የንግድ መዝገብ ሊያቋቁሙ ይችላሉ። በፌደራል ደረጃ የሚቋቋመውን የንግድ መዝገብ እንዲያቋቁም ሀላፊነት የተሰጠው ለንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር የነበረ ሲሆን በአዲሱ የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም መሰረት ይህ ተግባር የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር ይሆናል። ሚኒስቴሩ በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያለው ንግድ መዝገብ አቋቁሞ የማስተዳደር ሀላፊነት የተጣለበት ሲሆን በዚህ መልኩ በሚያቋቁመው መዝገብም ነጋዴዎችንና የንግድ ማህበራትን መመዝብ ይጠበቅበታል። ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመመዝገብ ሃላፊነቱን በከፊል ለሌላ የፌደራል ተቋም በውክልና ማስተላለፍ ይችላል። ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ራሳቸው በሚያወጡት ህግ የንግድ መዝገብ አቋቁመው የንግድ መዝገቡን አስተዳደርና የመመዝገብ ስልጣን ያለውን አካል እንዲሁም ሀላፊነቱን መወሰን የሚችሉ ቢሆንም ምዝገባውን ማከናወን ያለባቸው ግን የንግድ ህጉን በጥብቅ በመከተል መሆን አለበት።

በሌላ በኩል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያለው ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ ቋት ማደራጀትና ማስተዳደር ሀላፊነት ተጥሎበታል። ይህ ማዕከላዊ የንግድ መዝገብ መረጃ ቋት በፌደራል፣ በክልል እንዲሁም በአዲስ አበባ እና ድሬድዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚኖሩ የንግድ መዛግብት የሚሰፍሩ መረጃዎች ተጠቃለው የሚገቡበት ቋት ነው። ሚኒስቴሩ ቋቱን ከማደራጀትና ከማስተዳደር በተጨማሪ በየክልሉ ባሉ ልዩ ልዩ መዛግብት የተፃፉትን እያንዳንዱን የተመዘገበውን ሰው የሚመለከቱ መረጃዎች በሙሉ በመቀበል ወደ ቋት ማስገባት፣ የንግድ ማህበራትን የሚመለከቱ ፅሁፎችን፣ ሰነዶችን፣ ማስታወቂያዎችን ተቀብሎ ቋት ውስጥ ማስገባት እና ስለ ንግድ መዛግብት የወጡ ህጎችና ደንቦች በትክክል መፈፀማቸውን የመከታተል እና የመቆጣጠር ሀላፊነት ተጥሎበታል። በአንፃሩም የንግድ ምዝገባ ያከናወነ የፌደራልም ሆነ የክልል ተቋም የመዘገባቸውን የእያንዳንዱን ነጋዴ ወይም ንግድ ማህበር መረጃዎችና ሰነዶች ምዝገባውን እንዳከናወነ ለሚኒስቴሩ የማስተላለፍ ሀላፊነት ተጥሎበታል። በዚህ መልኩ የሚደራጀው የንግድ መዝገብም ለህዝብ ክፍት መሆን አለበት።

በንግድ መዝገብ የሚገቡ ነገሮች

ተመዝጋቢው የሚያደርገው ዋና ምዝገባ፣ በተጨማሪ ወይም በማሚያ የሚደረጉ ምዝገባዎች፣

የተለወጡ ወይም የተሰረዙ ጉዳዮች በንግድ መዝገብ ሊገቡ ይገባል።

ዋና ምዝገባ

ከስሙ እንደምንረዳው ዋና ምዝገባ ነጋዴው በዋናነት በመጀመሪያ የሚመዘገብበት ምዝገባ ነው። በዚህ ምዝገባ የነጋዴው ሙሉ ሥም፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ ዜግነት፣ የግል አድራሻ፣ ያገባ ከሆነ ጋብቻው የተፈፀመበት ቀንና ቦታ፣ ጋብቻ ውል መኖር አለመኖሩ፣ ካለ የተቀመጠበት ቦታ ወይም የያዘው ሰው ሥም፣ ሚስት ወይም ባል ስለ ንግድ ሥራው ያቀረበው ተቃውሞ ካለ ያቀረቡት መቃወሚያ፣ መቃወሚያው ቀሪ ከሆነም ቀሪ የሆነበት፣ ጋብቻው እንዲፈርስ ተወስኖ ከሆነ የመፍረስ ውሳኔው፣ የንግዱ ሥም፣ የንግዱ ምልክት፣ የንግዱ አላማ፣ የንግድ መደብሩ አድራሻ፣ ንግዱን ያቋቋመው ወይም የገዛ ወይም የተከራየ ስለመሆኑ እና ተከራይቶ ከሆነ የአከራይ ሥምና አስፈላጊ ሰነዶች፣ በተመዘገበበት ቦታ ወይም ሌላ ቦታ ሌሎች መደብሮች፣ ቅርንጫፎች ወይም መኪሎች ያሉት ከሆነ አድራሻቸው፣ በቅርንጫፎቹ ሥራ አስኪያጆች ያሉ ከሆነ ሥልጣናቸው ቅርንጫፉን በማስተዳደር ብቻ የተወሰነ መሆኑ፣ ያለው ከሆነ ለመነገድ የንግድ ፈቃድ ተሰጠበት ቀን፣ አካለ መጠን ያልደረሰ ከሆነ የንግድ ሥራ እንዲሰራ ለሞግዚቱ የተፈቀደበት ቀን፣ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት የተከለከለ ከሆነ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሁም አዲስ ሥራ አስኪያጅ ከተሾመ ስለመሾሙ የተመለከቱ መረጃዎች ይካተታሉ።

ተመዝጋቢዎቹ የንግድ ማህበራት በሚሆኑ ጊዜም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የመልሶ ማደራጀት ሥነ ሥርአት፣ የመክሰር ሥነ ሥርአት፣ ቀላል የመክሰር ሥነ ሥርአት ወይም ከዕዳ ነፃ መደረግ ሥነ ሥርአት ውሳኔዎች ካሉ መመዝገብ ይገባቸዋል። ነጋዴው አካለ መጠን አለመድረስ፣ የነጋዴው ችሎታ ማጣት፣ ነጋዴው ማግባቱ ወይም ጋብቻው መፍረሱ፣ የጋብቻ ውል መኖር፣ የሥራ አስኪያጅ መሻር ወይም ከሥራ መሰናበት፣ የሥራ አስኪያጅ ስልጣን አንድ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ጽ/ቤት በማስተዳደር ብቻ የተወሰነ መሆኑ እንዲሁም በአንቀፅ 15 መሰረት ባለው ወይም ሚስት የንግድ ሥራው የጋራ አለመሆኑን አስመልክቶ የሚያቀርቡት መቃወሚያ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር ቅን ልቦና ባላቸው ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊነሳ አይችልም።

ሌላው ከዋና ምዝገባ ጋር በተያዘ ልብ ሊባል የሚገባው አንድ ነጋዴ ዋና ምዝገባ ሊመዘገብ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን በተለያየ የንግድ ሥራዎች የሚሰራ እንኳን ቢሆን በዋናነት በንግድ መዝገብ መመዝገብ

የሚችለው በአንድ ቦታ ብቻ መሆኑ ነው። በሌሎች ክልሎች የሚነግድ ወይም የተለያዩ ቅርንጫፎች ወይም ወኪል መ/ቤቶች ካሉ ዋና መዝገቡ እየተጠቀሰ በአጭር ቃል በየክልሎቹ መመዝገብ አለበት። ከዋና ምዝገባ በኋላ የሚከሰቱ ለውጦች ካሉም ለውጦቹ በንግድ መዝገብ መግባት ይጠበቅባቸዋል።

በንግድ መዝገብ የመግባት ሥነ ሥርአት

በሀገራችን ግዛት ውስጥ የንግድ ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው (ኢትዮጵያዊ ወይም የውጪ ዜጋ) ወይም የህግ ሰውነት ያለው የንግድ ማህበር የመመዝገብ ግዴታ አለበት። የሚመዘገበውም ተመዝጋቢው ዋና መስሪያ ቤቱ በሚገኝበት ቦታ መዝገብ ለመያዝ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ በፅሁፍ በሚሰጠው መግለጫ መሰረት ነው። ነጋዴዎች ንግድ ከመጀመራቸው በፊት በነጋዴነት እንዲመዘገቡ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ማመልከቻውን ያላቀረበ በነጋዴነት ሊመዘገብ አይችልም። ማመልከቻውን ሲያቀርብም መዝጋቢው ተመዝጋቢው የሚያቀርበውን ማመልከቻ ትክክለኛነት፣ በህግ የታዘዙ ነገሮች በመግለጫው ውስጥ መካተታቸውን፣ ለመግለጫው ደጋፊ የሆኑ የፅሁፍ ማስረጃዎች ከመግለጫው ጋር መጣጣማቸውን እና አመልካቹ ምዝገባ የጠየቀበትን የንግድ ሥራ ለመስራት የሚያስችለውን ህጋዊ መመዘኛ ማሟላቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። መዝጋቢው አካል ተጨማሪ ሰነዶችና መረጃዎች አስፈላጊ ሆነው ባገኘ ጊዜ እንዲቀርቡ መጠየቅ ይችላል። በዚህ ሂደት የተከናወነ ምዝገባ ከተደረገበት ቀን ቀጥሎ ከሚኖረው ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል። ከዚህ በኋላ የተመዘገቡ ነጋዴዎችም በሚሰሩባቸው ወረቀቶች ላይ ሁሉ የተመዘገቡበትን ቦታ እና የምዝገባ ቁጥራቸውን መግለፅ ይጠበቅባቸዋል። ምዝገባውን በተመለከተ በመዝጋቢው እና በአመልካቹ መካከል የሚፈጠሩ ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚወሰኑ ሲሆን ምዝገባውን የሚያከናውነው አካል እና ሰራተኞቹ ከምዝገባ ጋር በተያያዘ ለሚደርሱ ጉዳቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂነት አለባቸው። መመዝገብ የሚገባው ሆኖ ሳይመዘገብ የቀረ ነጋዴ ደግሞ እንደ ነጋዴ ተቆጥሮ ሀላፊ ይሆናል።

በመዝገብ የመግባት ውጤት

ከላይ በተገለፀው መልኩ የሚደረግ ምዝገባ በተመዝጋቢው እንዲሁም በሚመዘገበው መረጃ ረገድ የራሱ ውጤት የሚያስከትል ነው። ተመዝጋቢውን በተመለከተ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ማንኛውም በመዝገብ የገባ ሰው ነጋዴ እንደሆነ ግምት ይወሰዳል። ሆኖም በነጋዴነት የተመዘገበው ሰው ወይም ማህበር ግን ነጋዴ አይደለሁም ሲል ማስረጃ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም። በዚህም ነጋዴ መሆኑ የሚያስከትለው ሀላፊነት ሁሉ ይኖርበታል።

ከተመዘገበው ጉዳይ አንፃር ማንኛውም ሰው በመዝገብ እንዲገባ ያደረገው መረጃ ትክክል ሳይሆን ቢቀር የተመዘገበው መረጃ ትክክል እንደሆነ በመቀበል በሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጠረውን ስህተት በመቃወሚያነት እንዲያቀርብ አይፈቀድም፡፡ ሶስተኛ ወገኖችም በንግድ መዝገብ የገባውን ጉዳይ አላውቅም ነበር ብለው ማስረጃ እንዲያቀርቡ አይፈቀድላቸውም፡፡

ከመዝገብ መሰረዝ

በንግድ መዝገብ የተመዘገበ ነጋዴ በዋናነት በሶስት ምክንያቶች ከንግድ መዝግብ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

¬ ነጋዴው ከሞተ፡- የተመዘገበው ነጋዴ የሞተ እንደሆነ ከንግድ መዝገብ የሚሰረዝ ሲሆን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካልገጠማቸው በስተቀር የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም ወራሾች ነጋዴው በሞተ በ 60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ምዝገባው እንዲሰረዝ ማመልከት ይጠበቅባቸዋል፡፡

¬ መነገድ መተው፡- በንግድ ሥራ የተሰማራ ነጋዴ በተለያየ ምክንያት የንግድ ሥራውን ሊተው ወይም መደብሩን ሊያከራይ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሥራውን ከተወበት ወይም መደብሩን ካከራየበት ጊዜ ጀምሮ በ 60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ማመልከት ይጠበቅበታል፡፡

¬ በትዕዛዝ ስለመሰረዝ፡- ይህ በመዝጋቢው አካል የሚፈፀም ነው፡፡ ይኸውም ነጋዴው የንግድ ሥራውን ማቆሙን እና የንግድ ሥራውን ለመስራት ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት እንደተወሰነበት ባወቀ ጊዜ ወይም በሌላ ህግ ለምዝገባ መሰረዝ በቂ ምክንያት ናቸው ተብለው የተደተደነገጉ ሁኔታዎች ከተሟሉ በራሱ አነሳሽነት ነጋዴውን ከመዝገብ መሰረዝ ሃፊነት አለበት፡፡ እዚህ ላይ በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 አንቀፅ 18 የተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ መዝጋቢው አካል የመሰረዝ ውሳኔ ሲሰጥ ለነጋዴው ለእራሱ እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

ከንግድ መዝገብ ጋር በተያያዘ የወንጀል ተጠያቂነት

ከንግድ መዝገብ ጋር በተያያዘ በንግድ ህጉ መሰረት መመዝገብ እያለበት ሳይመዘገብ የቀረ ወይም መመዝገብ ያለበትን ነገር ሳያስመዘግብ የቀረ እንዲሁም ስለሚመዘገበው ጉዳይ ሆን ብሎ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የሰጠ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚኖርበት ተደንግጓል፡፡ አግባብነት ያለው ህግ የሚባለው በዋናነት በልዩ ሁኔታ ንግድ ነክ ተግባራትን የሚመለከተው የንግድ መዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ሲሆን በወንጀል የሚስቀጡ ተግባራትንና ቅጣታቸውን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ለአብነት ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ በንግድ ምዝገባ የተመዘገበ ወይም የንግድ ሥሙን ያስመዘገበ ወይም የሞከረ ሰው ያለአግባብ ያገኘው ጥቅም መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ስልሳ ሺ እስከ ብር መቶ ሀያ ሺ በሚደርስ

የገንዘብ መቀጮ እና ከሰባት አመት እስከ አስራ ሁለት አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ የአዋጁ አንቀፅ 49(3) ደንግጎ ይገኛል። ሌሎች ከምዝገባ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች በአዋጁ አንቀፅ 49 ሥር የተዘረዘሩ በመሆኑ ህጉን በሚጥሱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት ነው።

በአጠቃላይ የንግድ መዝግብ በንግድ ህጉ መሰረት በንግድ ሥራ ላይ የሚሳተፉ ነጋዴዎችና ማህበራት መረጃ የሚመዘገቡበት የመረጃ ሥርአት መሆኑ ታውቆ ሁሉም መመዝገብ ያለበት ነጋዴ ወይም ማህበር ተገቢውን የምዝገባ ስርአት እንዲከተል እንመክራለን።

በንቃተ ህግ፣ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት

በአዲሱ የንግድ ሕግ የተካተቱ አዳዲስ ጉዳዮች

1. መግቢያ

በሥራ ላይ የነበረዉ የንግድ ሕግ (1952 ዓ.ም) አገሪቷ ከደረሰችበት የንግድ እንቅስቃሴና ዘርፉ ከሚፈለገዉ ዕድገት አንፃር ብዙ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ እና የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የንግድ ሕጉን መፈተሽ እና ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ አዲሱ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2014 ሆኖ ታትሞ ሥራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል። አዲሱ የንግድ ሕግ ከዚህ በፊት ከነበረው አንጻር በርካታ ለውጦች ተደርገዉበታል። የሕጉ መውጣት የኢትዮጵያን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴን በአወንታዊ መንገድ ለመቀየር ከፍተኛ አስተዋጾ አለዉ። በዚህ አጭር ጽሁፍ የንግድ ሕጉን ዓላማዎች፣የንግድ ሕጉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት፣የንግድ ሕጉ ማሻሻል ያለዉ ጠቀሜታ እና አዳዲስ የተካተቱ ጉዳዮች የምንመለከት ይሆናል።

2. የንግድ ሕግ ዓላማዎች

አንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር በዕለት ተዕለት የንግድ እንቅስቃሴው ከተለያዩ አካላት ጋር የውል እና ከውል ውጪ የሆኑ ግንኙነቶችን ይፈጥራል።

ለምሳሌ፦ አንድ የንግድ ድርጅት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ከሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ ምርቶቹን እና አገልግሎቶቹን ከሚገዙት ደንበኞች ወይም ሸማቾች፣ ለድርጅቱ ብድር ከሰጡ ወይም በሌላ ምክንያት ከድርጅቱ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ካላቸው ሰዎች፣ ከንግድ ተወዳዳሪዎቹ፣ ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ከድርጅቱ ሠራተኞችና ሥራ አመራሮች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል፤ ድርጅቱ ከባለሀብቶቹ የተለየ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ማኅበር ሲሆን ደግሞ ከማኅበርተኞቹ ጭምር ግንኙነት ይኖረዋል። ከላይ ከተገለጹት የንግድ ድርጅት ከሚፈጥራቸው ዘርፈ ብዙ

ግንኙነት አኳያ የንግድ ሕጎች ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች አሏቸው፦ አንደኛው ዓላማ አንድ የንግድ ድርጅት ከላይ በተመለከትናቸው ውስብስብ ግንኙነቶች ውስጥ ተንቀሳቅሶ ሀብት እንዲያፈራ እና አትራፊ እንዲሆን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማበጀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከላይ ለተጠቀሱት ከአንድ የንግድ ድርጅት ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች ለሚፈጥሩት አካላት መብቶች እና ቅቡልነት ያላቸው ፍላጎቶች ተገቢውን የሕግ ጥበቃ ማድረግ ነው። የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) እነዚህን ሁለት አንኳር ዓላማዎች ይጋራል። ይህ ሲባል ግን የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) ሁሉንም ከላይ የተመለከትናቸውን ግንኙነቶች አሟልቶ ይገዛል ማለት አይደለም።

3. የንግድ ሕጉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት እና ጠቀሜታ

የንግድ ህጉ አሁን ያለውን ዘመናዊውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሊመልስ በሚችል መልኩ ካልተቀረፀ ወይም ካልተዘጋጀ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና የሚኖረው በመሆኑ የንግድ ህግ ዘመናዊ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም አሁን የሚመጡ አዳዲስ ዕድገቶችን ታሳቢ ተደርጎ መረቀቅ እና በተጨባጭ ያንን ሊመልስ በሚችል መልኩ መሰራት አለበት። የእኛ ሀገር የንግድ ህግ ከብዙ ዓመታት በፊት የተዘጋጀ በመሆኑ አሁን ያለውን አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በንግድ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች ሊመልስ የማይችልባቸው ምክንያቶች አሉ። ከነዛ መካከል አንዱ በንግድ ህጉ የተካተቱ በርካታ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ባለመሆናቸው፣የሚፈፀሙትም ቢሆን አሁን ካለው አጠቃላይ የንግድ እና ኢኮኖሚ እንቅሳሴ ጋር የማይሄዱ በመሆናቸው፣ በተለይም በሀገራችን ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ያለው ከማህበራት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍተቶች ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ቀደም የነበረው የንግድ ህግ ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎችን መመለስ ባለመቻሉ የመጣ ችግር ነው። በመሆኑም ክፍተቶቹን በመፈተሽ አሁን ካለው እና ዘመኑ ከሚጠይቀው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ዘመናዊ የንግድ ህግ ማደራጀት በማስፈለጉ የንግድ ህጉ እንደገና እንዲወጣ ተደርጓል።

በዚህ ሕግ መሰረት የትኛውም እንቅስቃሴ ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ የንግድ ማህበራት የሚቆጣጠራቸው ሕጉ ነው። የንግድ ምዝገባ ለማድረግም መነሻ ህጋቸው ይህ ህግ ነው። የዚህ ሕግ ዘመናዊ ሆኖ መደራጀቱ ለነጋዴው፣ ለንግድ ማህበራት፣ ለ 3ኛ ወገኖች እና ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ መደራጀታቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ከዚህም በተጨማሪ ዘመኑ የሚጠይቀው ሕግ ተደንግጎ የወጣ፣ አሁን ካለው የስራ እንቅስቃሴ ጋር አብሮ የሚሄድ እና ለነጋዴው ግልፅ የሆነ የንግድ ሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ለልማታዊ ባለሀብቶች የሚያመች ሁኔታ በመፍጠር ረገድ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል።

## 4. አዳዲስ የተካተቱ ጉዳዮች

ነባሩ የንግድ ህግ ጥራዝ በስድስት መጽሀፍት የተደራጀ ሲሆን፣ በአንደኛ መጽሀፍ ስለንግድ ስራና ነጋዴዎች፣ በሁለተኛ መጽሁፍ ስለንግድ ማኅበራት፣በሶስተኛ መጽሀፍ ስለኢንሹራንስና የማጓጓዣ አገልግሎት፣በአራተኛ መጽሀፍ ስለባንክና ተላላፊ ሰነዶች (የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች)፣በአምስተኛ መጽሀፉ ስለኪሳራ ህግ ፣ በስድስተኛ መጽሀፍ መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ሆኖ ዝርዝር ጉዳዮችን አካትቶ የተሰነደ ነው። በተደረገዉ ጥናት መጽሐፍት 3 እና 4 የንግድ ሕግ አካል ሳይሆኑ ራሳቸዉን ችለዉ የፋይናንስ አገልግሎት መድብል / Code / እንዲሆኑ እና መጽሀፍ አንድ፣ሁለት እና አምስት የንግድ ሕግ ተብሎ እንዲሻሻል ተደርጎ በአዲሱ የንግድ ሕግ ወጥቷል። በአዲሱ አዋጅ ያልተካተቱት የባንክ፣ የኢንሹራንስና፣ የማጓጓዣ ዘርፎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በቀድሞው አሠራር መሠረት የሚቀጥሉ ሲሆን አዲሱ የንግድ ሕግ በርካታ ማሻሻያዎችን እና አዳዲስ አሰራሮችን የያዘ ሆኖ ወጥቷል። ከእነዚህ ጥቂቶቹን እንመልከት።

ϖ አንድ ግለሰብ ለብቻው ኩባንያ መክፈት እንዲችል ተፈቅዷል

አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 534 እንደሚያሳየዉ አንድ ግለሰብ ብቻውን ኩባንያን መመስረት እንዲችል ተፈቅዷል። ይህም ሰዎች በቀላሉ ወደ ሥራ እንዲገቡ ያግዛቸዋል ።

ϖ የንግድ ትርጓሜን መቀየር

በተሻረው ሕግ የተዘረዘሩት የንግድ አይነቶች 21 ብቻ ናቸው። ከነዚህ ውጪ ያሉት ንግድ አይደሉም ተብለው እንደሚገመቱ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። አሁን ግን በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 5 መሰረት የንግድ አይነቶችን ወደ 37 አድገዋል። በዚሁ ሕግ የንግድ ትርጉም ክፍት ነው። በግልፅ ካልተከለከለ በስተቀር ያተርፋል ብሎ እንደሙያ የያዘውን ሥራ አስመዝግቦ መቀጠል ይችላል። ይህ መሆኑ ደግሞ አዳዲስ የንግድ አይነቶችንና የፈጠራ ሐሳቦችን ያበርታታል ።

ϖ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሙያ ሽርክና ማኅበራት (አንቀፅ 221)

በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ከተካተቱ ጉልህ ለውጦች መካከል አንዱ የሆነው ይህ አዲስ የሽርክና ማህበር አይነት፣ ሰዎች በተለይም የሙያ ስራዎችን ለመስራት በሙያ ከሚመስሏቸው ሌሎች ሰዎችና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ አጋሮቻቸው ጋር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው የሚያቋቁሙት፣ ኃላፊነቱም በሽርክና ማኅበሩ ሃብት ላይ ብቻ የተወሰነ የንግድ ማኅበር ነው በሚል በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 221 ላይ ተደንግጓል። ከቀደመው ሕግ በተቃራኒው አዲስ የጸደቀው አዋጅ ግለሰቦች በሙያቸው ተደራጅተው

እንዲሠሩ በግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል። እያንዳንዱ ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ይዘው ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ የሽርክና የሙያ ማኅበራት እንዲስፋፉ ያስችላል።

በሌላ በኩል የቀድሞው ሕግ የአክስዮን ማኅበራት የዳይሬክተሮች የቦርድ አባላት ሁሉም የአክሲዮን ባለድርሻ እንዲሆኑ ግዴታ የጣለ ነበር። ነገር ግን በአዲሱ ሕግ ባለድርሻ መሆን ሳይጠበቅባቸው፤ ባለ ድርሻ ያልሆኑ ሰዎች በሙያቸው እስከ አንድ ሦስተኛ ድረስ የሚሆነውን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ቦታን እንዲይዙ ይፈቃዳል። ይህ አይነቱ የሽርክና ማኅበር የህግ አገልግሎትን፣ የሂሳብ መዝገትና ኦዲት ወይም ሌላ አይነት ቴክኒካዊ እውቀትን በሚጠይቁና የሙያ ፈቃድ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የስራ ዘርፎች ላይ በቅንጅት መስራት ለሚሹ ሙያተኞች አይነተኛ ምርጫ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

ϖ የሆልዲንግ ካምፓኒ ስለ መፈቀዱ

በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 5 ስር በተመለከቱት ሥራዎች ላይ በመሰማራት በቀጥታ ራሱ ምርትና አገልግሎት ባያቀርብም በዚህ ተግባር በተሰማሩ ሌሎች የንግድ ማኅበራት ዉስጥ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ድርሻ የሚይዝ ኩባንያ ወይም ሆልዲንግ ካምፓኒ እንደ ነጋዴ እንደሚቆጥር አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 9 ያመለክታል። በተጨማሪም ሆልዲንግ ካምፓኒ በቀጥታ ምርትና አገልግሎት ማቅረብ ይችላል።

ϖ ተራ የሽርክና ማህበርን የሚመለከተው የህጉ ክፍል ስለመቅረቱ፦

ነባሩ የንግድ ህግ ስለንግድ ተቋማት በሚዘረዝርበት ሁለተኛ መጽሀፉ ተራ የሽርክና ማህበርን ሰፊ ሽፋን የሰጠው ሲሆን በትንታኔው ግን ይህ አይነቱ ማኅበር በንግድ ስራ ውስጥ መሳተፍ እንደማይችል በግልፅ አስቀምጧል። እንግዲህ የንግድ ስራ ውስጥ መሳተፍ አይችልም የተባለ የሰዎች ስብስብ፣ በንግድ ህግ ጥራዝ ውስጥ እንደ ንግድ ተቋም መቀመጡ የህግ አመክንዮ የማይገኝለት በመሆኑ ውሳኔው ትክክለኛነቱ አያጠያይቅም።

ϖ አክስዮን ማኅበርን በሚመለከተው የህጉ ክፍል አክሲዮኑ ለህዝብ ክፍት ስለሚሆን ማሕበር ሰፊ ሽፋን ስለመሰጠቱ፦

ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ከሚሰራባቸው የንግድ ተቋማት አይነቶች ውስጥ ዋናውን ስፍራ የሚወስደው አክስዮን ማኅበር መሆኑ ይታወቃል። የባንክ እና የኢንሹራንስ ስራን የመሳሰሉ የፋይናንስ አገልግሎት ስራዎችን ለመስራት የተፈቀደለት ብቸኛው የንግድ ተቋም ፎርም አክስዮን ማኅበር ነው። በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 248 ላይ እንደተመለከተዉ የአክስዮን ማህበር ለህዝብ ክፍት በሆነ የአክስዮን ሽያጭ የሚመሰረትበትን

ሁኔታ አስቀምጧል። ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህን መሰሉን ማህበር ለማቋቋም በሚሰሩት አደራጆች መብትና ግዴታ እንዲሁም ሀላፊነት ዙሪያ የተብራሩ ድንጋጌዎችን አካቷል።

ϖ በንግድ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠርን ዝምድና (Affiliation) ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚሆን የህግ ክፍል ስለመካተቱ

የንግድ ማኅበራትን በሚመለከተው መጽሀፍ ሁለት ውስጥ በርዕስ ዘጠኝ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተካተተው የኩባንያዎች መዛመድ ጽንሰ-ሀሳብ ሰፋ ያለ ዳሰሳና ጥናት የሚጠይቅ ጉዳይ ቢሆንም በዚህ የንግድ ህግ መካተቱ ምን አይነት ለውጦች ሊያስከትል እንደሚችል ልናነሳ ይገባል። አንድ ኩባንያ የሌላኛውን ኩባንያ አክስዮን የገዛ ከሆነ፣ ወይም እርስ በእርስ አክስዮኖች የተገዛዙ ከሆነ፣ ወይም በኩባንያዎቹ መካከል የሆልዲንግና ሰብሲዲየሪ (ተቀጽላ) ግንኙነት ካለ ወይም የአንድ ቡድን ኩባንያ (Group Company) አባላት ከሆኑ የተዛመዱ (Affiliated) ኩባንያዎች ይባላሉ። አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 550 የኩባንያዎችን ዝምድና በመተንተን ሂደትም አንድን ኩባንያ የሆልዲንግ ኩባንያ አቋም የሚያሰጡት ሁኔታዎችና የአክሲዮንና የድምጽ መብቶች መጠን፣ ሆልዲንግ ኩባንያ በተቀጥላ (Subsidiary) ላይ ስለሚኖረው ልዩ ልዩ መብትና ስልጣን እንዲሁም ሆልዲንግ ኩባንያ ከዘጠና በመቶ በላይ የድምጽ መብት በሚኖረው ጊዜ ሌሎች የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ስለሚኖራቸው አማራጭ እና በተቀጥላ ኩባንያ ውስጥ ስላሉት የስራ አመራር አባላት ተጠያቂነት በዝርዝር ያስቀምጣል።

ϖ የኪሳራ ህግን በሚመለከተው መጽሀፍ ውስጥ ዕዳን እንደገና ስለማደራጀት የሚመለከት ተጨማሪ ጽንሰ-ሀሳብ ስለመካተቱ፦

ማንኛውም ነጋዴ ይብዛም ይነስም በንግድ እንቅስቃሴ ላይ ሲሰማራና ገንዘብና ጊዜውን ሲመድብ ይሳካልኛል የሚል ብርቱ እምነት ቢኖረውም ቅሉ፣ ጥቂት የማይባሉ ነጋዴዎች ግን እንዳሰቡት ሳይሳካላቸው ይቀርና ወደኪሳራ ያመራሉ። ነባሩ የኪሳራ ህግ፣ አንድ ነጋዴ ያሉበትን ዕዳዎች መክፈል ማቋረጡን እንደዋና ምክንያት በመያዝ፣ የአበዳሪዎችንና ሌሎች መብት ጠያቂዎችን ጥቅም ለማስከበር ሲባል የመክሰር ውሳኔ ሊተላለፍ እንደሚችል ያትታል። አዲሱ የንግድ ህግ በዚህ ረገድ አዲስና እጅግ ጠቃሚ የሚባል ዕዳን እንደገና ስለማደራጀት የሚገልፅ ክፍል በመክሰር ሂደት ውስጥ እንዲካተት አድርጓል። ለማሻሻያው ዋና መነሻ የሚሆነው የህጉ አላማ በጊዜያዊ የገንዘብ ችግር ምክንያት ዕዳ መክፈል ያቋረጡ ወይም ለማቋረጥ የተቃረቡ ነጋዴዎች እንደገና ተደራጅተው እንዲያገግሙ እድል መስጠት ነው። እዳን እንደገና ማደራጀት የሚባለው ባለዕዳው ያለበትን የዕዳ መጠን፣ አይነት እና የአከፋፈል ሁኔታዎች በሌላ የዕዳ ወይም የመብት አይነት፣

መጠንና የአከፋፈል ሁኔታዎች በፍርድ ሲለወጡ ነው። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ዕዳን እንደገና የማደራጀት ተግባር የመክሰር ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም ከተሰጠ በኋላ ሊከናወን የሚችል ሲሆን በዋነኝነትም የገንዘብ መብት ጠያቂዎች ፍላጎትና የፍርድ ቤት ውሳኔ እንደቅድመሁኔታ የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው።

በአጠቃላይ አዲሱ የንግድ ህግ በይዘትም ሆነ በቅርፅ መሰረታዊ የሚባሉ ለውጦችን የያዘ ሰነድ ሲሆን አንዳንድ ማሻሻያዎቹ የሌሎች ሀገራት የንግድ ህግጋትን መነሻ ተጨማሪ ጽንሰ ሀሳቦችን ያካተተ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም ከተሻረው ሕግ በተቃራኒ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የሚከስሩ የንግድ ሰዎች ነጻ የሚሆኑበትን መንገድ አመቻችቷል። እነዚህን ጨምሮ ለንግድ እንቅስቃሴው የማይመቹ ሕጎችን ያሻሻለው የአዲሱ አዋጅ መውጣት በሀገር ውስጥ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ ያሳልጣል።